# ኮቪድ-19
# በኢትዮጵያ

## ምላሾች፣ ተፅዕኖዎች እና
## የወደፊት የፖሊሲ አቅጣጫዎች


አርታዒ

ዘሪሁን መሐመድ



መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ

Good Governance Africa (GGA)

# ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ

## ምላሾች፣ ተፅዕኖዎች እና የወደፊት የፖሊሲ አቅጣጫዎች

አርታዒ

ዘሪሁን መሐመድ

መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ

Good Governance Africa (GGA)

© 2013 ዓ.ም መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ

አዲስ አበባ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ
ፖ.ሣ.ቁ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል፡ info.easternafrica@gga.org

ድረ-ገጽ፡ https://gga.org/centres-coverage/east-africa/

በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች በሙሉ የፀሀፊያኑ ሲሆኑ የመልካም አስተዳደር አፍሪካን፣ የመልካም አስተዳደር አፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን እንዲሁም የድርጅቱን አጋሮች አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቁ ይችላሉ።

# ማውጫ


መግቢያ ..................................................................................... I

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ላይ ያደረሳቸው ተፅዕኖዎች፣ የተሰጡ ምላሾችና የወደፊት የፖሊሲ ዕርምጃዎች ............... 1

አየለ ዘውዴ

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ፡ ከዘገምተኛ ስርጭት እስከ አሳሳቢ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ምልከታ ................................................ 41

አሉላ ፓንክረስት

የኮቪድ 19 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ........................ 59

አለማየሁ ገዳ

ኮቪድ-19 እና መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ ...................................... 81

አስናቀ ከፋለ

# መግቢያ

በቅርብ ጊዜ ውስጥ በዓለም ላይ ካጋጠሙ እጅግ የከፉ ተላላፊ የጤና ችግሮች መካከል አንዱ ኮቪድ-19 (SARS-COV2) መሆኑ ይታወቃል፡፡ ቫይረሱ በታህሳስ 2012 በቻይና ዉሀን ግዛት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሁሉም የዓለም ሀገሮች በፍጥነት ተዛምቷል፡፡ እስከ ግንቦት አጋማሽ 2013 ድረስ 215 አገራት ከ162 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በኮሮና በሽታ መያዛቸውንና ወደ 440 ሺህ የሚጠጉ ደግሞ በበሽታው ህይወታቸው ማለፉን የዓለም የጤና ድርጅት የመረጃ ምንጮች ያመለክታሉ፡፡

በአፍሪካ ውስጥ የኮቪድ-19 መስፋፋት በወረርሽኙ በመጀመሪያዎቹ ወራቶች እንደታየው በጣም ዘገምተኛ አልነበረም፡፡ በእርግጥም የዓለም የጤና ድርጅት መጋቢት 2 ቀን 2012 ኮቪድ-19ን ‹‹ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ›› ብሎ ባወጀ በሦስት ሳምንታት ውስጥ 46 የአፍሪካ አገራት በድምሩ ወደ 5,000 የሚጠጉ ተጠቂዎችን ይፋ አድርገዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙት 54ቱም አገራት ኮቪድ-19 በየአገራቸው መከሰቱን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን እስከ ግንቦት 9 ቀን 2013 ባለው ጊዜ ውስጥ 3,356,562 ሰዎች በኮቪድ-19 መያዛቸውንና 84,504 ሰዎች ደግሞ በወረርሽኙ ሳቢያ ሕይወታቸው ማለፉን የዓለም የጤና ድርጅት አመልክቷል፡፡

በቅርብ ጊዜ ከተከሰቱ ሌሎች ተመሳሳይ ወረርሽኞች አንጻር ሲታይ ኮቪድ-19 የበለጠ የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የፖለቲካ ተግዳሮቶችን አድርሷል፤ በማድረስም ላይ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን ወረርሽኙ በንፅፅር አነስተኛ የሞት መጠን እንዳለው ቢዘገብም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ MERS እና SARS ካሉ ሌሎች ወረርሽኞች የበለጠ ገዳይ መሆኑ ታይቷል፡፡ የኮቪድ-19 ተፅዕኖ በሁሉም አህጉራት

በግልፅ ቢታይም ችግሩ በአፍሪካ (በተለይም በኢኮኖሚ ደካማ በሆኑት ከሠሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች) በጣም የከፋ እንደሆነ ተረጋግጧል። አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት ለወረርሽኙ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ያደረጉት ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም፣ በተለያዩ የአቅም፣ የመሠረተ-ልማት እና የአስተዳደር ማነቆዎች ሳቢያ የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር አልቻሉም። በቂ የፋይናንስ አቅም የሌላቸው የጤና ሥርዓቶች፣ ደካማ የመሠረተ ልማቶች፣ የኮቪድ-19ን ተፅዕኖ መቋቋም የማይችል ዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ደካማ የአስተዳደር ሥርዓቶች በአፍሪካ ሀገሮች ከነዚህ ማነቆዎች መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው።

የምሥራቃዊ አፍሪካ ሁኔታን ስመለከት ምንም እንኳን ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው እንደ ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ዑጋንዳ ያሉ አገራት ከፍተኛ የኮቪድ ተጠቂና የሟች ብዛት ቢያስመዘግቡም፤ አነስተኛ የሕዝብ መጠን ያላቸው እንደ ጅቡቲ፣ ኤርትራ እና ሶማሊያ ያሉ አገራት ካላቸው የሕዝብ መጠን አኳያ በአንፃራዊ ከፍተኛ የተጠቂ መጠን ሪፖርት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ባለው ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የሕዝብ ብዛቷ ከአንድ ሚሊዮን ብዙም ከፍ ያላለው ጅቡቲ 11,577 የኮቪድ-19 ተጠቂ ስታስመዘግብ፤ ወደ 16.3 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ ያላት ሶማሊያም ከአንድ ሚሊዮን ሠዎች መካከል 8,874 ተጠቂዎችን በማስመዝገብ በአንፃራዊነት ከፍተኛ የኮቪድ መስፋፋት ያለባት አገር መሆኗን አሳይታለች። ይሁን እንጂ በአገራቱ እስካሁን ድረስ እምብዛም ባልተሻሻለው ዝቅተኛ የምርመራ ደረጃና አቅም እንዲሁም የክትትል ማነስ ሳቢያ በየአገራቱና በክፍለ-አህጉሩ ያለውን የኮቪድ ስርጭት በኢፊሴል ከሚገለጹት አኃዞች እጅግ የላቀ እንደሚሆን ይገመታል።

የኮቪድ-19 ዜና ከተሰማበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ መንግስት የተለያዩ ዕርምጃዎችን በመውሰድ ለተከሰተው ወረርሽኝ እና ሊያደርስ

የሚችለውን ጉዳት ምላሽ ለመስጠት ዝግጅቶች ሲያደርግ እንደነበር ይታወቃል። በአገሪቱ ውስጥ የመጀመሪያው የኮቪድ-19 ተጠቂ ሪፖርት የተደረገው በመጋቢት 4 ቀን 2012 ሲሆን ግለሰቡም ከቡርኪናፋሶ የመጣ የጃፓን ዜጋ ነበር። የሁኔታውን አሳሳቢነት በማየት መንግስት ለተፈጠረው ወረርሽኝ ምላሽ የመስጠት አቅሙን ለማሳደግ መጋቢት 30 ቀን 2012 ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል።

በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መንግስት የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተለያዩ ዕርምጃዎችን ወስዷል። ከነዚህም መካከል የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና ዩኒቨርስቲዎችን መዝጋት፣ ከባህር ማዶ የሚመጡ ተጓዦችን ለ14 ቀናት በለይቶ ማቆያ እንዲቆዩ ማድረግ፣ መሠረታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ የመንግሥት ሠራተኞች ከቤታቸው እንዲሠሩ መፍቀድ፣ በሁሉም ዓለም አቀፍ ድንበሮች የሁሉም ሰዎችን እንቅስቃሴ መገደብ፣ ማንኛውንም አይነት ሰፊ ሕዝባዊና እና ኃይማኖታዊ ስብሰባዎችን ማገድ ይገኙበታል።

መንግሥት የጤና ስርዓቱ ወረርሽኙን እንዲገታ ለማድረግ ሌሎች ዕርምጃዎችንም ወስዷል። ከነዚህም መካከል ለኮቪድ-19 ተጠቂዎች ልዩ ሆስፒታሎችን ማዘጋጀት፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የኮቪድ-19 የላብራቶሪ ማዕከላትን ማቋቋም፣ ለጤና ባለሙያዎች ስለ ወረርሽኙ ልዩ ስልጠና መስጠት፣ የህክምና ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን ማስመጣት እና ማሰራጨት እና የክልሎችን ወረርሽኙን የመቋቋም አቅም ማጎልበት ይገኙበታል።

በኢኮኖሚው መስክ መንግሥት ኮቪድ-19ን እንደ ዋና የኢኮኖሚ እና የምግብ ዋስትና ሥጋት የተመለከተው ሲሆን የወረርሽኙን ኢኮኖሚያዊ

ጉዳት ለማቃለል የተለያዩ የፖሊሲ ዕርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡

- የግል ባንኮች ደንበኞቻቸውን በተለይም በኮቪድ-19 የተጎዱ የንግድ ተቋማትን እንዲደግፉ 15 ቢሊዮን ብር ድጋፍ መስጠቱ፤
- በወረርሽኙ ይበልጥ የሚጎዳውን የቱሪዝም ዘርፍ ከሚገጥመው ተግዳሮች ለመታደግና ለማሳደግ የ3.3 ቢሊዮን ብር ምደባ መደረጉ፤
- ከውጭ የሚገቡ የወረርሽኙን መስፋፋት ለመግታት የሚረዱ ተዛማጅ ምርቶችን ለማስገባት የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ መመደብና ምርቶቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ማድረግ፤
- ለንግድ ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ገንዘብን በተፋጠነ ሂደት መመለስን ያካትታል፡፡

በተጨማሪም የሞባይል ክፍያ ስርዓትን ማስፋፋት፣ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር በፍጥነት እንዲያገኙ ማመቻቸትና በኮቪድ-19 ለተጎዱ የንግድ ድርጅቶች የታክስ እፎይታዎችን መስጠት ተጨማሪ ዕርምጃዎች ነበሩ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የወረርሽኙን ማኅበራዊ ተፅዕኖች ለመቀነስ መንግሥት የማኅበራዊ ደህንነት መረቦችን ለማስፋት ጥረት ከማድረጉ ባሻገር በየአካባቢው የግልና የመንግሥት ዘርፍ ኢንቨስትመንትን አበረታቷል፡፡ በዋና ከተሞች ውስጥ የምግብ ባንኮች የተቋቋሙ ሲሆን ‹‹ማዕድ ማጋራት››[1] በተሠኘው መርኃ-ግብር ህዝቡ በወረርሽኙ ሳቢያ

[1]ይህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ “ማዕድ ማጋራት” ሲሉ የሰየሙት አንድ ቤተሰብ ለሌላ አንድ ቤተሰብ በቀን አንድ ምግብ ለማካፈል የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርግ ሚያዝያ 12 ቀን 2012 ባደረጉት ጥሪ መሠረት የተወጠነ መርኃ-ግብር ነው፡፡

የኢኮኖሚ ጉዳት ለደረሰባቸው ድጋፍ እንዲያደርግ ከፍተኛ ቅስቀሳና ማስተባበር ተደርጓል፤ አበረታች ውጤቶችም ታይተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ዕርምጃዎች ቢወሰዱም አሁንም ኢትዮጵያ ከኮቪድ-19 የሚመነጩ የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የፖለቲካዊ አለመረጋጋቶች ተጋርጠውባታል፡፡ በጤናው ረገድ የኮቪድ-19 ስርጭት አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ከመገኘቱ በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመስፋፋት መጠኑ እየጨመረ ይገኛል፡፡ አለም ዓቀፍ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የመጀመሪያው ተጠቂ ከተገኘበት ከመጋቢት ወር 2012 መጀመሪያ አንስቶ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ድረስ ባሉት 15 ወራት ውስጥ በአጠቃላይ 276,681 ሰዎች በወረርሽኙ ሲጠቁ የ4,338 ሰዎች ህይወት በበሽታው አልፏል፡፡ በዚህም በኮቪድ ወረርሽና ሞት አገሪቱ ከደቡብ አፍሪካ፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ እና ግብፅ በመቀጠል ከአፍሪካ አገራት በአምስተኛ ደረጃ ላይ እንድትቀመጥ አድርጓታል፡፡

የኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ወረርሽኙ ከተከሠተ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ የታየ ነው፡፡ ወረርሽኙ በከተሞች አካባቢ ለብዙ ሰዎች የኑሮ ምሰሶ የሆነውን መደበኛ ያልሆነ ኢኮኖሚ (informal economy) በከፍtኛ ደረጃ ያጠቃ ሲሆን በዚህም ሳቢያ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራቶች ውስጥ ብዙ አነስተኛና መካከለኛ ንግዶች ለመዘጋት ተገድደዋል፡፡ በማክሮ ኢኮኖሚ ደረጃም ኮቪድ-19 ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ማነቆ በመሆን ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አምጥቷል፡፡ በወረርሽኙ የመጀመሪያ ወራት አካባቢ በመስኩ ያሉ ባለሙያዎች ኮቪድ-19 በማክሮ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚያስከትላቸውን ሦስት ፈታኝ ችግሮችን ለይተዋል፡፡ እነዚህም 1ኛ) አገሪቱ ያለባትን ከፍተኛ የውጭ ብድር ለመክፈል የምታደርገውን ጥረት መገደቡ[2] 2ኛ) በወረርሽኙ

[2] ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ብዙ የዕዳ ጫናዎች ያሉባት ሲሆን የውጭ እና የሀገር ውስጥ ብድር በቅደም ተከተል ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት 30% እና 27% እንደሆነ ይታሰባል፡፡

የተነሳ አየር መንገድንና ቱሪዝምን ጨምሮ አንዳንድ ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ዝቅተኛ አፈፃፀም በመኖሩ ሳቢያ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት መከሠት እና 3ኛ) በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በወረርሽኙ ሳቢያ በሚደርስባቸው የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ሳቢያ ወደ አገር ቤት የሚልኩት ገንዘብ መቀነሱና አገሪቱም በመስኩ ታገኝ የነበረው የውጭ ምንዛሬ መቀነሱ ናቸው[3]።

**መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ** ኮቪድ-19 በአገራችን በተከሰተ የመጀመሪያ ወራት ውስጥ መንግስት የሰጠውን ምላሽ እና ወረርሽኙ ወደፊት በአገሪቱ ልማት እና አስተዳደር ላይ ሊያሳድር የሚችላቸውን ተፅዕኖዎች ላይ የሚወያይ ‹‹*ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ፥ ምላሾች ፣ ተጽዕኖዎች እና የወደፊት የፖሊሲ አቅጣጫዎች*›› የሚል ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀቱና ማካሄዱ ይታወሳል። በመድረኮቹም በየመስኩ ያሉ ባለሙያዎች የውይይት መነሻ ጥናታዊ ጽሑፎችን ያቀረቡ ሲሆን በመድረኮቹ ላይም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መ/ቤቶች ተወካዮች፣ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት መምህራንና በዘርፉ ያሉ ተመራማሪዎች፣ የሚዲያ ባለሙያዎችና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ተገኝተው በውይይቶቹ ተሳትፈዋል።

የውይይት መድረኮቹ በአራት የተመረጡ ተያያዥ ርዕሶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን እነዚህም 1ኛ) ‹‹ኮቪድ-19 እና የኢትዮጵያ የጤና ምላሽ፣ ተግዳሮቶች እና የወደፊት አቅጣጫዎች››፣ 2ኛ) ‹‹የኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖና የወደፊት አቅጣጫ በኢትዮጵያ››፣ 3ኛ) ‹‹የኮቪድ-

[3]ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2019 ወደ 5.7 ቢሊዮን ዶላር ያህል ከውጭ የተላከ ገቢ ማግኘቷ ተዘግቧል። ነገር ግን ስደተኞቹ ባሉባቸው አገሮች በተከሰተው የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል ሳቢያ ይህ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚቀንስ ይጠበቃል።

19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ እና ማኅበራዊ አንድምታው›› እና 4ኛ) ‹‹ኮቪድ-19 እና አስተዳደር በኢትዮጵያ›› የሚሉ ነበሩ።

ነሐሴ 12 ቀን 2012 በአዲስ አበባ ኢንተር ኮንትኔንታል ሆቴል በተካሄደው የውይይት መድረክ ላይ ኮቪድ-19 በአገራችን እያደረሰ ያለውን የጤና እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችና የተሰጡ ምላሾችን የሚመለከቱ ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። በዚህ መሠረት *‹‹የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ላይ ያደረሳቸው ተፅዕኖዎች፣ የተሰጡ ምላሾችና የወደፊት የፖሊሲ ዕርምጃዎች››* በሚል ርዕስ በዶ/ር አየለ ዘውዴ (ከአዲስ አህጉራዊ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት) ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቧል። ዶ/ር አየለ በጽሁፋቸው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሁኔታን በኢትዮጵያ ከዳሰሱ በኋላ ወረርሽኙ በጤናና በጤና-ሥርዓቱ ላይ ያስከተላቸውን አሉታዊ እና አዎንታዊ ተፅዕኖዎች አመልክተዋል። በማስከተልም በኢትዮጵያ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተሰጠውን ምላሽ በዝርዝር ከተነተኑ በኋላ በማጠቃለያቸው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከሚያስከትላቸው ሁለንታዊ ተግዳሮቶች አንፃር በጤና ሚኒስቴር ላይ ብቻ የሚተው ስራ እንዳልሆነ እና የሌሎች መ/ቤቶችና ሴክተሮችንም ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን ያሳስባሉ።

*‹‹የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ፡ ከዘገምተኛ ስርጭት እስከ አሳሳቢ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ምልከታ››* በሚል ርዕስ በዶ/ር አሉላ ፓንክረስት (ያንግ ላይቭስ ኢትዮጵያ) የቀረበው ሁለተኛ ጥናታዊ ጽሁፍ ወረርሽኙ በአገራችን ያስከተለውን ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችና ወደፊት ሊደረግ ይገባዋል የሚሉትን ጉዳዮች ይዳስሳል። ዶ/ር አሉላ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት በኢትዮጵያ በመጀመሪያ ወራቶች በተፈራው ፍጥነት ያልተስፋፋው ለምንድነው? የሚል ጥያቄ በማንሳት የተለያዩ መላምቶችን ይተነትናሉ። ወረርሽኙ ይበልጥ ተጋላጭና ተጠቂ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ እያደረሰ ያለውን ማኅበራዊ ጫና

በማሳየት በማጠቃለያቸው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ እየተባባሰ ያለ ችግር እንደሆነ እና ቫይረሱ ከሰዎች ጋር መቆየቱ አይቀሬ መሆኑን አመልክተው ክትባቱ እስኪገኝ እና በበቂ ሁኔታ እስኪዳረስ ድረስ ያለው አንድ አማራጭ የወረርሽኙን ባሕሪና ተላላፊነት በሚገባ በመረዳት በመላመድ ተቋቁሞ የመኖር አቅምን ማጠናከር የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በነሐሴ 22 ቀን 2012 በተካሄደው ሁለተኛው የውይይት መድረክ ላይ ‹‹*የኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ በኢትዮጵያ*›› በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገዳ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) የኢትዮጵያን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ በመግቢያነት በመዳሰስ ኮቪድ-19 እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ በአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት እና በዘርፎች ዕድገት ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ፤ እንዲሁም እንደ ዓለም አቀፍ ንግድና ፋይናንስ ያሉ የውጪ ዘርፎች ላይ ያደረሰውን ጉዳት አኃዞችን በመጥቀስ ያመለክታሉ። አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ወረርሽኙ ሊያስከትላቸው የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖዎች ከተለያዩ ‹‹ቢሆኔዎች›› (senarios) በመነሳት ይተነትናሉ። በማጠቃለያቸውም ቀድሞውንም ጠንካራ ያልሆነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በወረርሽኙ እና ተያያዥ በሚመጡ ችግሮች እንደሚጎዳ በመገንዘብ ችግሩን ሊያቃልል በተለይ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሊጠብቅ የሚችል ዕርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ያሳስባሉ።

በመጨረሻም ‹‹*ኮቪድ-19 እና መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ*›› በሚል ርዕስ ዶ/ር አስናቀ ከፋለ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) የጥናት ጽሁፋቸውን ያቀረቡ ሲሆን በጽሁፋቸውም የወረርሽኝ በሽታዎች ከመልካም አስተዳደር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና ወረርሽኞች የመንግስትን ሁለንተናዊ አቅም የመፈታተን ባሕሪ እንዳላቸው በተለያዩ ጊዜያት

በዓለምና በአገራችን የደረሱ ወረርሽኞችን በመጥቀስ ይተነትናሉ፡፡ በኢትዮጵያ የኮቪድ-19 መከሰትና መስፋፋት በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ካለው ፖለቲካዊ ለውጥ ጋር መገጣጠሙ ችግሩን ይበልጥ እንዳወሳሰበው በመጥቀስ በነሀሴ ወር 2012 ሊካሄድ ታቅዶ የነበረው ስድስተኛው አገራዊ ምርጫ መራዘምን፤ የትግራይ ክልል የተናጠል ምርጫ ለማካሄድ መወሰንን እና በዚህ ሳቢያ የተፈጠረውን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ክስረት በማሳያነት ይጠቅሳሉ፡፡ በመደምደሚያቸው ፖለቲካዊ ትኩረትና መረጋጋት ወረርሽኙን ለመከላከልና ጉዳቱን ለመቀነስ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ መንግስትም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለዚህ መሳካት በትጋት መስራት እንደሚገባቸው ያሳስባሉ፡፡

ጥናታዊ ጽሑፎቹ የተዘጋጁትም ሆነ የውይይት መድረኮቹ የተካሄዱት ከአስር ወራት በፊትና ስለወረርሽኙ ያለው ግንዛቤ በአገር ውስጥም ሆነ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ውስን በነበረበት ወቅት በመሆኑ በጥናታዊ ወረቀቶቹ የተመለከቱ አንዳንድ አኃዞችና ትንታኔዎች ከዚህ ውስን መረጃ አንፃር እንዲታዩ እያሳሰብን፤ መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ ወደፊትም በተመሳሳይ አገራዊ እና አለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያደርገው ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

አርታዒው

# የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ላይ ያደረሳቸው ተፅዕኖዎች፣ የተሰጡ ምላሾችና የወደፊት የፖሊሲ ዕርምጃዎች

አየለ ዘውዴ

## 1 መግቢያ

የኮሮና ቫይረስ በመባል የሚታወቁት ጥቃቅን በሽታ አምጪ ህዋሳት ዝርያ ቀላልና መካከለኛ የሆነ እንደ ጉንፋን ያለ የላይኛው የመተንፈሻ ክፍልን የሚያጠቃ በሽታ በማምጣት ይታወቃሉ። መጀመሪያ በደምብ ተዘርዝረው ከታወቁበት ከእ.ኤ.አ 1960ዎቹ ጀምሮ እስካሁን በዓለማችን በመቶዎች የሚቆጠሩ የኮሮና ቫይረስ ዝርያዎች መኖራቸውና አብዛኞቹም እንደ አሳማ፣ ግመል፣ የሌሊት ወፍና ድመት በመሣሠሉ እንስሳት ውስጥ እንደሚኖሩ ይታወቃል። አንዳንድ ጊዜም እነዚህ ቫይረሶች ወደ ሰው ሊተላለፉና በሽታ ሊያመጡ ይችላሉ። ይህም "ሞልቶ የመፍሰስ ክስተት[1]" ተብሎ ይታወቃል። በዚህ ክስተት ከሚታወቁት ሰባት የኮሮና ቫይረሶች መካከል አራቱ በሰው ልጅ ላይ ቀላልና መካከለኛ የሆነ በሽታ በማምጣት ሲታወቁ፤ የቀሩት ሦስቱ ግን የከፋና ለሞትም ሊያደርስ የሚችል በሽታ እንደሚያስከትሉ ይታወቃል። እነዚህ አደገኛ የኮሮና ቫይረስ ዝርያዎችም የሚከተሉት ናቸው።

1. **የሳርስ ኮሮና ቫይረስ (SARS-CoV) -** ይህ ቫይረስ በህዳር 1994 በቻይና ጉዋንጁ ግዛት የተከሰተና ከባድና አጣዳፊ የሆነ የመተንፈሻ አካል ደምሬ-ህመም (severe acute respiratory syndrome [SARS]) በማመጣት የሚታወቅ ነው። የዚህ በሽታ

[1]ይህንን ቃል የእንግሊዝኛውን "spillover effect" ለማለት ነው። ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸው ነገር ግን በአካባቢው በመኖራቸው ጉዳዩ ተፅዕኖውን ያሳደረባቸውን ክፍሎች ለመግለፅ የተጠቀምኩበት ቃል ነው።

መጀመሪያ መነሻ እንስሳ እስካሁን በትክክል አልታወቀም:: በሽታው በ26 አገሮች ተሰራጭቶ ወደ 8000 ያህል ሰዎችን ይዞ ወደ 800 ያህል የሰው ሕይወት ከቀጠፈ በኋላ እ.ኤ.አ በ2004 ከዓለማችን እንደጠፋ ይነገራል::

2. **የመርስ ኮሮና ቫይረስ (MERS-CoV)** - ይህ ቫይረስ የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል ደምሬ-ህመም (Middle East respiratory syndrome [MERS]) የተባለውን በሽታ በማምጣት የሚታወቅ ሲሆን፤ በመጀመሪያ በ2004/5 በሳውዲ ዐረቢያ እንደተከሰተና ከግመል ወደ ሰውም እንደተላለፈ ይገመታል:: እንደ የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ በሽታው በ27 አገሮች ተሰራጭቶ 2,500 ሰዎችን ሲይዝ የ860 ሰዎች ሕይወትም መቅጠፉ ይታመናል:: ይህ በሽታ አሁንም በተወሰኑ ቦታዎች አልፎ አልፎ እንደሚታይ ይነገራል::

3. **የሳርስ ኮሮና ቫይረስ - 2 (SARS-CoV-2)** - ይህ ቫይረስ በመጀመሪያ ታህሳስ 2012 በቻይና፣ ውሀን ከተማ መከሰቱ ይገመታል:: ከላይ እንደተጠቀሱት ሁለት የኮሮና ቫይረሶች ይህም ቫይረስ በዋነኛነት የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ የኮሮና ቫይረስ ህመም-2019 (COVID-19) በመባል የተሰየመውን በሽታ ያመጣል:: በመጀመሪያ የበሽታው መነሻ ከእባብ ነው ተብሎ ቢገመትም በኋላ ግን የተለያዩ ተመራማሪዎች የሌሊት ወፍ፣ ጉንዳን በሊታ እንሰሳት ሊያስተላልፉ ይችላሉ የሚሉ መረጃዎችን አቅርበዋል:: ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስም የትኛው እንስሳ በሽታውን እንደሚያስተላልፍ በርግጠኝነት ገና አልታወቀም:: በርግጠኝነት የታወቀው የሳርስ ኮሮና ቫይረስ-2 ከላይ ከተመለከትናቸው ኮሮና ቫይረሶች ይበልጥ በፍጥነት የሚዛመትና ገዳይ በሽታ መሆኑን ነው:: ለዚህም ከዚህ በታች ያሉት ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ጥሩ ማስረጃ ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ::

የኮቪድ-19 የመጀመሪያው ሕመምተኛ የተገኘው በታህሳስ 20 ቀን 2012 ውሀን ተብላ በምትታወቅ ቻይና ውስጥ በምትገኝ አንዲት ከተማ እንደሆነ ይነገራል። በሽታው ከተከሰተ ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ መጋቢት 2 ቀን 2013 ዓ.ም የዓለም ጤና ድርጅት ኮቪድ-19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ መሆኑን አወጀ። እንደ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ በሽታው በተከሰተ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ አንድ ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው መያዛቸውና 50,000 ያህል ሰዎች ደግሞ ህይወታቸውን ማጣታቸው ሲታወቅ በስድሰት ወር ጊዜ ውስጥ ደግሞ 10 ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው ተይዘው ግማሽ ሚሊዮን ያህሎቹ ህይወታቸውን ማጣታቸው ታውቋል። እስከ መስከረም 26 ቀን 2013 ድረስ በመላው ዓለም ላይ 35,347,404 ሰዎች በበሽታው ሲያዙ 1,039,404 ያህሉ ህይወታቸውን ማጣታቸው ተረጋግጧል። ከዚህ ቁጥር ጋር አስገራሚና የማያጠራጥር መልስ ያልተገኘለት ክስተት ደግሞ በሽታው ሪፖርት ከተደረገባቸው 235 ሀገሮች ወይም የዓለም ጤና ድርጅት ግዛቶች መካከል፣ 57 በመቶ የሚሆኑት ህመምተኞች ከአራት አገሮች ብቻ (አሜሪካ፣ ህንድ፤ ብራዚልና ሩሲያ) ሪፖርት መደረጉ ነው። አንዳንዶች፣ ምክንያቱ እነዚህ አገሮች ብዙ ምርመራ ስለሚያደረጉ ነው ቁጥሩ የበዛው ቢሉም ይህ ለመሆኑ ግን በጥናት ያረጋገጡት ነገር እስካሁን የለም።

እስከ ሐምሌ 2013 ባሉት ወራቶች ውስጥ አስራ ሁለት አገራት ብቻ የኮቪድ-19 በሽታ ሪፖርት ያላደረጉ አገሮች ተብለው ይታወቃሉ። እዚህ ላይ "ሪፖርት ያላደረጉ" የሚለው ሐረግ ሊሰመርበት ይገባል፣ ምክንያቱም አነዚህ አገሮች በሽታውን ሪፖርት አያድርጉ እንጂ በሽታው በሀገራቸው የለም ማለት አይደለም። ከአስራ ሁለቱ አገሮች መካከል አስር ትናንሽ የፓሰፊክ ኔሽን ተብለው የሚታውቁ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሁለቱ አገራት (ሰሜን ኮሪያና፣ ቱርክሜንስታን) ደግሞ በኢ-ዲሞክራሲያዊነታቸው የታወቁና ነፃ ሚዲያ የሌለባቸው ሀገሮች

በመሆናቸው በሽታው በርግጠኝነት በአገሮቻቸው ላለመኖሩ እርግጠኛ መሆን የማይቻልባቸው ሀገሮች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት በኮቪድ-19 የተያዙትና ህይወታቸውን ያጡትን ቁጥሮች በመመልከት ብቻ የህዝቡ ጤናና የጤናው ዘርፉ ምን ያህል በቫይረሱ የቀጥታ ጥቃት እንደደረሰበት መገመት አያስቸግርም። በጥርና የካቲት 2012 ወራት እንደ ጣሊያንና ስፔን በመሳሰሉት ሀገሮች የታየውን እልቂት በመመልከት በሽታው ከሁለቱ አገሮች እጅግ የደከመ የጤና ስርዓት ወዳላት አፍሪካ ሲመጣ ምን አይነት ሰቆቃ ሊከሰት እንደሚችል በመገመት እንቅልፍ ያጡ እጅግ በጣም ብዙዎች ነበሩ። “በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ፣ የዓለም ጤና ድርጅት በ155 አገሮች ባደረገው የዳሰሳ ጥናት ኮቪድ-19 በተዘዋዋሪ መንገድ በሌሎች፣ በተለይም ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በመላው ዓለም ይበልጥ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ፣ ማድረሱን አሳይቷል። ይህም ተፅዕኖ አንድም ተላላፊ ባልሆነ በሽታ የተጠቁ ሰዎች በኮቪድ-19 በይበልጥ የሚጠቁና ህይወታቸውን የሚያጡ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሁለተኛነት ደግሞ፣ ህመምተኞቹ ላለባቸው ተላላፊ ያልሆነ በሽታ (ስኳርና ደም ብዛት የመሳሰሉት) በቂ ህክምናና እንክብካቤ ማግኘት ባለመቻላቸው የሚደርስባቸው የጤና ችግር ነው።

ሌላው በኮቪድ ምክንያት በስፋት የሚስተዋለው የጤና ችግር የአዕምሮ መታወክ ነው። የሀሳብ ጫና (stress)፣ ጭንቀት፣ ፍርሀት፣ ሀዘንና የመሳሰሉት የአዕምሮ መታወኮች በኮቪድ ወቅት በተለያዩ ከበሽታውና በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚወሰዱት ምላሾች ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ እንደሚችሉ የተለያዩ ጥናቶች አመላክተዋል።

በአፍሪካ በሽታው ለመጀመሪያ ጊዜ ሪፖርት የተደረገው በየካቲት 6 ቀን 2013 በግብፅ ውስጥ ነው። ከላይ ለመግለጽ በተሞከረው ምክንያት በዚያን ወቅት የነበረው የአብዛኛው ማህበረሰብ አስተያየት/ግምት፣

“አፍሪካ አለቀላት“ አይነት ነበር። ሆኖም ግን እንደተፈራው ሳይሆን የቫይረሱ ስርጭት በአፍሪካ በጣም ዝግ ባለ ፍጥነት እየጨመረ ሔዶ እስከ መስከረም 28 ቀን 2013 ድረስ 1,537,669 ሰዎች በቫይረሱ ሲያዙ 37,392ቱ ህይወታቸውን አጥተዋል። ይህም አሀዝ ከሌሎቹ ክፍለ ዓለማት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ የሚባል ነው። የአፍሪካ አገሮች የምርመራ አቅም ዝቅተኛ መሆን ለአኀዙ ማነስ እንደምክንያት የሚጠቅሱ በርካቶች ናቸው። የአፍሪካ የበሽታዎች ቁጥጥር ዳይሬክተር ዶ/ር ጆን ንኬንጋሶንግ (Dr. Nkengasong) የምርመራ አቅም ማነስን ሳይክዱ እንደ ዋና ምክንያት መታየቱን ግን አይስማሙበትም። ለዚህም የሚያቀርቡት ዋና ምክንያት በአፍሪካ ከወትሮው የበለጠ የሞት መጠን አለመታየቱንና የኮቪድ ሞት በበሽታው ከተያዙት ጋር በንፅፅር ሲታይ ከሌሎቹ ክፍለ-ዓለማት ያነሰ መሆኑን ነው። ከታች የሚታየው ምስልም የአፍሪካ ሀገራት የበሽታው ስርጭት የምርመራ አቅማቸው በጨመረ ጊዜም ከሌሎቹ ክፍለ-ዓለማት ያነሰ መሆኑ የዳይሬክተሩን ነጥብ ያጠናክራል።




የአፍሪካ አገሮች በሽታው በአህጉሪቱ እንደተከሰተ የሰጡት ፈጣን ምላሽ ወረርሽኙ በአህጉሪቱ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳይስፋፋ ካደረጉት

ምክንያቶች መካከል በዋናነት ሊጠቀስ ይገባዋል የሚሉ በርካታ ናቸው፡፡ ከተሰጡት ምላሾችም መካከል እንደዚህ በፍጥነት ለሚሰራጭ፣ ህክምናና መከላከያ ክትባት ላልተገኘለት ተላላፊ በሽታ ፍቱን የሆነውን *የህብረተሰብ ጤናና ማህበራዊ የመፍትሔ ዕርምጃ* (Public Health and Social Measures [PHSMs]) በመባል የሚታወቀውን ያካትታል፡፡ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የኮቪድ-19 ምላሽ አጋርነት (Partnership for Evidence-based COVID-19 Response [PERC]) የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት የተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮችን ያሳተፉ ሁለት የዳሰሳ ጥናቶችን አካሂዶ ባገኘው ውጤት መሠረት አብዛኞቹ የህብረተሰብ ጤናና ማህበራዊ የመፍትሔ ዕርምጃዎች (እጅ መታጠብ፣ የአፍና የአፍንጫ ጭንብል ማድረግ፣ ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ) በአብዛኛው የጥናት ተሳታፊዎች የሚደገፍና የሚተገበር መሆኑን ሲያረጋግጥ፣ የገበያ ቦታዎችን መዝጋትና አገር አቋራጭ ጉዞን ማቆም ግን አነስተኛ በሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ድጋፍ አግኝቷል፡፡ በሁለቱም የዳሰሳ ጥናቶች፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች የህብረተሰብ ጤናና ማህበራዊ የመፍትሔ ዕርምጃዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መፈለጋቸው ተመልክቷል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው አጣዳፊና ፍቱን ዕርምጃና የህዝቡ ዕርምጃዎቹን የመተግበር ተባባሪነት በተጨማሪ የኮቪድ-19 በሽታ አኃዝ በአፍሪካ በአንፃራዊነት ከሌሎቹ ክፍለ-ዓለማት ያነሰ ከሆነባቸው ሌሎች ምክንያቶች መካከል አብዛኛው የአፍሪካ ህዝብ ወጣት መሆኑ፣ የአፍሪካ የአየር ፀባይና መልካ-ምድራዊ አቀማመጥና በሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የተገነባው ጥሩ የሚባል የህብረተሰብ ጤና-ሥርዓት ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የኮቪድ-19 በጤናና በጤና-ሥርዓቱ ላይ በዓለም ደረጃ የሚያደርሰው ተፅዕኖ በአፍሪካ ላይ ተመሳሳይ ግን ከፍ ባለ ደረጃ የሚከሰት ለመሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ተንብየው ነበር፡፡ በተለይም ይህ

ፈጣንና ከባድ በሽታ በቋፍ ያለውን የአፍሪካን የጤና ሥርዓት እንዴት አድርጎ ሊያናጋው እንደሚችል መገመት ለማንም አስቸጋሪ አይሆንም ነበር፡፡

የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማም በሳርስ ኮሮና ቫይረስ-2 (SARS-COV-2) ምክንያት የሚከሰተው ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያስከተለውን የጤና ችግርና የተወሰዱ ዕርምጃዎችን ማሳየትና መደረግ ይገባቸዋል የምላቸውን አቅጣጫዎች መጠቆም ነው፡፡

## 1 የኮቪድ-19 ሁኔታ በኢትዮጵያ፣ በጤናና በጤና ሥርዓቱ ላይ ያመጣው ተፅዕኖ

### 1.1 የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሁኔታ በኢትዮጵያ

የመጀመሪያው ኮቪድ-19 ተጠቂ በኢትዮጵያ መገኘቱ የተዘገበው መጋቢት 4 ቀን 2012 (የዓለም ጤና ድርጅት በሽታውን ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ብሎ ከፈረጀው ሁለት ቀን በኋላ) ነበር፡፡ ተጠቂው ለስራ ጉዳይ ወደሀገሪቱ የመጡ ጃፓናዊ ነበሩ፡፡ ከዚያም በየቀኑ በበሽታው የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ ሄደ፡፡ በየዕለቱ በበሽታው የሚያዙት ሰዎች አኃዝ አንዴ ከፍ አንዴ ደግሞ ዝቅ ሲል በዚያው መጠንም የህብረተሰቡ ትኩሳትም ከፍና ዝቅ እያለ ቀንን ቀን እየወለደ ሄደ፡፡ የመጀመሪያው ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘው ህልፈተ ሕይወትም በሽታው ከተከሰተ ከ22 ቀናት በኋላ በመጋቢት 27 ቀን 2012 ተዘገበ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለም፣ መስከረም 25 ቀን 2013 በተጠናቀረው ዘገባ፣ በሀገሪቱ 78,819 ሰዎች በበሽታው መያዛቸው፣ 1,222 ደግሞ ህይወታቸውን ማጣታቸውና 33,060 ከበሽታው ማገገማቸው ታውቋል፡፡

## 1.2 ኮቪድ-19 በጤናና በጤና-ሥርዓቱ ላይ ያመጣው ተፅዕኖ

ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ ያለበት ሁኔታ ከሞላ ጎደል ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረውን የመሰለ ሲሆን በሀገሪቱ ጤናና የጤና-ሥርዓት ላይ ያመጣውን ተፅዕኖ ከታች እንደተዘረዘረው ከፋፍለን ማየት እንችላለን::

### 2.2.1 በግለሰብ ጤና ላይ ያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ

ኮቪድ-19 በግለሰብ ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ቀጥታና ተዘዋዋሪ በማለት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን:: የቀጥታ ተፅዕኖው ከስሙ እንደምንረዳው አንድ ግለሰብ በበሽታው ተይዞ የሚደርስበት የጤና ችግር ነው:: በዚህም መሠረት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ 78,819 ሰዎች በበሽታው መያዛቸውና 1,222 ያህሉ ህይወታቸው ማለፉ ይህ በሽታ በህብረተሰቡ ጤና ላይ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ አጉልቶ ያሳያል ብዬ አምናለሁ::

በአንፃሩ ቀጥታ ያልሆነው (ተዘዋዋሪ) ተፅዕኖዎቹ በተለያየ መንገድ ሊታዩ ይችላሉ:: እነዚህም፣ በኮቪድ-19 የተያዘው ግለሰብ ተጓዳኝ የሆነ እንደ ስኳር፣ ደም ብዛት፤ አስም ወዘተ ያሉ የቆዩና የቅርብ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ህመሞች ያሉበት ከሆነ፣ አንድም እነዚህ በሽታዎች የኮቪዱን ህመም ሊያባብሱበትና ህይወቱን አደጋ ላይ ሊጥሉብት ሲችሉ፤ በሌላ ወገን ደግሞ በሽተኛው ኮሮናን በመፍራት ወደጤና ተቋም ለመሄድ ባለመፈለጉ ወይም ደግሞ የጤና ተቋማቱ ለነዚህ ተጓዳኝ በሽታዎች የሚሰጡትን ትኩረት በመቀነሳቸው በሽተኛው በተጓዳኝ በሽታዎቹ ምክንያት በጠና ሊታመምና ህይወቱም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል:: በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው በቅጥ ያጣ ውፍረት (obesity) እና በኮቪድ-19 መካከል ያለው ጥምረት የሁለትዮሽ ጥምረት ነው:: ይህም ማለት በአንድ በኩል ቅጥ ያጣ ውፍረት ያላቸው ሰዎች በኮሮና ቫይረስ የመያዛቸው ዕድል ከፍ ያለና በሽታው በያዛቸውም ጊዜ የሚጠናባቸው፣ ለህክምናና እንክብካቤም

የማይመቹ (እንደልብ ለማንቀሳቀስ፣ የሰው ሰራሽ መተንፈሻ ቢያስፈልጋቸው መተንፈሻውን ለማስገባት አስቸጋሪ መሆኑ ወዘተ) ሲሆኑ፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንቅስቃሴያቸው በመገደቡና አመጋገባቸው በትኩሱ ከተዘጋጁ ምግቦች ወደ ታሸጉ ምግቦች በመቀየሩ ለውፍረትና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የተጋለጡ ይሆናሉ።

### 2.2.2 በግለሰብ ጤና ላይ ያስከትለው አዎንታዊ ተፅዕኖ

ምንም እንኳን ኮቪድ-19 በግለሰብ ጤና ላይ የሚያመጣው ጠንቅ ዋና መገለጫው ቢሆንም፣ መጠነኛ የሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለውም ይታወቃል። ይህ አዎንታዊ ተፅዕኖም በዋነኛነት ህብረተሰቡ ኮቪድን ለመከላከል ሲል የሚወስዳቸው ዕርምጃዎች ውጤት ነው። ከታች እንደምናየው የኮቪድ-19 ዋነኛ መከላከያ መንገዶች የሚባሉት የግል ንፅህናን በሚገባ መጠበቅ፣ የማስነጠስና የማሳል ሥነ-ሥርዓት፣ ርቀትን መጠበቅና በተቻለ መጠን በቤት ውስጥ መቀመጥ እንዲሁም በሽታው ቢይዘን እንኳን በፍጥነት ለማገገም የሚጠቅሙንን ዕርምጃዎች መውሰድ (የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማዘውተር፣ የተመጣጠኑ/ጤናማ ምግቦችን መመገብና ራስን ከአልኮል መጠጥ፣ ሲጋራ ማራቅ የመሳሰሉት) ግለሰቡንም ሆነ ማህበረሰቡን ከተለያዩ ተላላፊና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ይጠብቁታል። በጥናት ባይደገፍም የተላላፊ በሽታዎች (እንደ ተቅማጥ፣ ጉንፋን ወዘተ) መቀነስና የህብረተሰቡ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በሰፊው መጨመር እንደ ምሳሌ በብዙዎች ዘንድ ይጠቀሳሉ።

### 2.2.3 በጤና ሥርዓቱ ላይ ያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ

የኢትዮጵያ የጤና-ሥርዓት እንደማንኛውም ታዳጊ ሀገር የጤና ሥርዓት ደካማ መሆኑ ይታወቃል። እንዲህ አይነት ደካማ የጤና ሥርዓት ደግሞ እንደ ኮቪድ ያለ በስርጭት ፍጥነትና በከባድነት የታወቀ ወረርሽኝ በሚከስትበት ጊዜ ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ

ለመገመት አያስቸግርም። አንድ ምሳሌ ብንወስድ፣ እንደሚታወቀው ኮቪድ-19 በዋነኛነት የመተንፋሻ አካልን የሚያጠቃ በሽታ ነው። ስለሆነም በበሽታው ከተጠቁት ህሙማን የተወሰኑት ሰው ሰራሽ የመተንፈሻ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም በመገመት ከመቶ ሚሊዮን በላይ ህዝብ እንደሚኖርባት የምትገመተው ኢትዮጵያ ከኮቪድ በፊት ከነበራትና ወረርሽኙ ከተከሰተ በኋላም ካገኘችው ዕርዳታ ጋር በአንድነት ካሏት 450 ያህል የሰው ሰራሽ መተንፈሻ አካል ውስጥ 54ቱን ለኮቪድ-19 መጠባበቂያ እንድታስቀምጠው ተገድዳለች። እዚህ ላይ በሚገባ ልንገነዘብ የሚገባን፣ በኢትዮጵያ ይከሰታል ተብሎ ለሚገመተው የኮቪድ-19 ፅኑ ህሙማን ቁጥር 450ው የሰው ሰራሽ መተንፈሻ መሣሪያ እንኳን በቂ ሊሆን እንደማይችል ነው። ከላይ በግለሰብ ጤና ላይ ያስከተለውን ተፅዕኖ ስገልጽ ለማሳየት እንደሞከርኩት የጤና ሥርዓቱ (ጤና ተቋማቱና ጤና ባለሙያው) የበሽታውን ፈጣን ስርጭትና ከባድነት ከግምት በማስገባት አግባብ/አሳማኝ በሆነ ምክንያት ከፍተኛ ትኩረቱን በኮቪድ-19 ላይ ሊያደርግ ስለሚችል ሌሎቹ የጤና ግልጋሎቶች ችላ የመባል አዝማሚያ ሊታይባቸው ይችላል ብሎ መገመት አግባብነት ያለው ይመስለኛል። ምንም እንኳን በሀገራችን ይህንን ክስተት በግልፅ ያሳየ ጥናት ባይኖርም፣ አንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የጤና ተቋማት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት አገልግሎት ማቋረጣቸው ታይቷል።

ከሌሎች ተመሳሳይ ወረርሽኞች ለመማር እንደሚቻለው በወረርሽኝ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ዝርዝር የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

- የህሙማን ወደ ጤና ተቋማት ለመሔድ መፍራት (ለምሳሌ፡ ትኩሳት ያለበት የወባ በሽተኛ ኮቪድ ይሆናል ተብዬ ማቆያ ቢያስገቡኝስ? ብሎ ወደ ጤና ተቋም ለመሔድ አለመፈለግ)፤

- የመድሀኒቶችና ሌሎች ነፍስ አድን ግብዓቶች (ለምሳሌ፡ ደም) ዕጥረትና አቅርቦት መቆራረጥ፤
- የጤና ተቋማት በህሙማን መጨናነቅ፤
- የነፍስ ወከፍ የተላላፊ በሽታ መከላከያ ቁሳቁስ (PPE) ዕጥረት፤
- መሠረታዊ የህክምና አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡- ክትባት፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የእርግዝና ከትትል የመሣሠሉት) መስተጓጎል፤
- አግባብነት የሌለው የመድሀኒት ብክነት፤
- የጤና ባለሙያዎች ዕጥረት፤
- የክትትል ህክምና የሚወስዱ ህሙማን ለ ኮቪድ-19 ተጋላጭ መሆን::

እነዚህና የመሳሰሉት በመሠረታዊ የጤና ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ችግሮች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገሮችም ላይ የሚታዩ ችግሮች ስለሆኑ የዓለም ጤና ድርጅት ሀገራት ችግሮቹን ለመቅረፍ ሊከተሉት የሚገባ መመሪያ አውጥቷል:: የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴርም መመሪያውን ለሀገሪቱ በሚስማማ መልክ በመከለስ አዘጋጅቶ አሰራጭቶታል::

### 2.2.4 በጤና ሥርዓቱ ላይ ያስከትለው አዎንታዊ ተፅዕኖዎች

ከላይ የግለሰብ ጤና ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በጤና ሥርዓቱም ላይ የሚታዩ አዎንታዊ ተፅዕኖዎች አሉት:: ለዚህም የሚከተሉት እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ:-

- ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መስከረም 25 ቀን 2013 ድረስ ከኮቪድ በሽተኛ ጋር ንክኪ ያላቸውን 257,087 ሰዎች መፈለግ (trace ማድረግ) ተችሏል:: ይህም በሀገሪቱ የተደረገ ታላቅ የበሽታ ቅኝት ፕሮግራም ይመስለኛል:: ይህን አይነት የበሽታ ቅኝት አቅም መዳበር ለወደፊት በአገሪቱ ውስጥ

ለሚካሄድ የበሽታ ቅኝት ስራ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

- በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ በአስሩም ክልሎችና በሁለቱ የከተማ መስተዳደሮች 1,301,570 የኮቪድ-19 ላቦራቶሪ ምርመራዎች ተደርገዋል። ይህም የሆነው ወረርሽኙ በተከሰተበት ጊዜ ከነበረው አንድም ምርመራ ለማድረግ አለመቻል አቅም ተነስቶ ነው። ይህ በሚያስገርም ሁኔታ የዳበረ የላቦራቶሪ አቅም ወደፊት ለሌሎች በሽታዎችም ሊጠቅምና የጤና ሥርዓቱንም ሊያጠናክረው ይችላል።
- በሀገሪቱ ይገኝ የነበረው የሰው ሰራሽ የመተንፈሻ መሣሪያ (mechanical ventilators) ቁጥር ከወረርሽኙ በፊት ከነበረው በብዙ ዕጥፍ መጨመሩና የጤና ባለሙያዎች በአጠቃቀሙ ላይ መሰልጠንና ክህሎት ማዳበር፣ በሀገሪቱ ያለውን በጣም ኋላ የቀረ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በከፍተኛ ደረጃ ሊያሻሽለው ይችላል።

## 2 በኢትዮጵያ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተሰጠው ምላሽ

ይህን ርዕስ በሚገባ ለመመልከትና ለመረዳት ለማንኛውም በሽታ (በወረርሽኝ መልክ ተከሰተም አልተከሰተም) የሚተገበረውን ***ቀጣይነት/ተከታታይነት ያለው እንክብካቤ*** (*Continuum of Care*) የተባለውን ፅንሰ ኃሳብ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህ ፅንሰ ኃሳብ ከታች በምስል ለማሳየት እንደተሞከረው በበሽታው ከመያዛችን በፊት ጀምሮ ላለመያዝ ማድረግ ከሚገባን ጥንቃቄ ጀምሮ ከተያዝንም በኋላ እስከ ህልፈተ-ህይወታችንና ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ ወስጥ ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ የሚመለከት ፅንሰ ኃሳብ ነው ።




*ምንጭ:-*

*[https://www.ruralhealthweb.org/blogs/ruralhealthvoices/september-2017/continuum-of-care-why-rural-health-care-may-benef](https://www.ruralhealthweb.org/blogs/ruralhealthvoices/september-2017/continuum-of-care-why-rural-health-care-may-benef)*

በምስሉ ላይ እንደሚታየው በመጀመሪያው ሳጥን በበሽታ ላለመያዝ የበሽታውን መተላለፊያ ወይም መምጫ/መጋለጫ መንገዶች በሚገባ ማወቅና መጠንቀቅ፤ ከዚያም አልፎ መከላከያ ክትባት ወይም መድሀኒት ካለ መጠቀምን ያሳያል:: በሽታን መከላከል ከመታከም መቶ በመቶ እንደሚሻል ቢታወቅና አብዛኛው ሕብረተሰብ በሽታውን ለመከላከል የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ቢያደርግም፣ በሽታው በአብዛኛው በቂ ጥንቃቄ ባላደረጉት፤ በትንሹ ደግሞ በቂ ጥንቃቄ ባደረጉት ላይ መከሰቱ አይቀርም:: ይህም በሚሆንበት ወቅት በሁለተኛው ሳጥን ውስጥ እንደተመለከተው የድንገተኛ ህክምና (emergency care)፣ የአጭር ጊዜ ህክምና (acute treatment) እና ድጋፍ ሰጪ ህክምና (supportive care) በመስጠት በሽታው ብዙ ጉዳት ሳያደርስ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያስችል ጥረት ይደረጋል:: በዚህም ጥረት፣ አብዛኛዎቹን ተላላፊ በሽታዎች ወደሚቀጥለው ሳጥን ሳይገቡ ማዳን ሲቻል አብዛኛዎቹ የማይተላለፉና አንዳንድ ተላላፊ በሽታዎች ግን

የሦስተኛው ሳጥን ህክምና/እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ሳጥን ውስጥ የሚገኘው እንክብካቤ ያስፈለጋቸው በሽታዎች ልንቆጣጠራቸው የምንችል ነገር ግን ጨርሶ ልናድናቸው የማንችል (manageable but not curable) በመባል የሚታወቁ በሽታዎች ናቸው (ምሳሌ- የስኳር በሽታ፣ ደምብዛት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወ.ዘ.ተ)። እነዚህም በሽታዎች የረጅም ጊዜ (በአብዛኛው የሕይወት ሙሉ) ህክምናና የቅርብ ክትትል የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህ በሽታዎችም ቀስ በቀስ የተለያዩ የውስጥ አካላቶችን ስለሚጎዱ ህመምተኛውን ወደ ማይቀረው ሞት ያመሩታል። በምስሉ ላይ የሚታየው አራተኛው ሳጥንም ህመምተኛውን ለህልፈተ-ሕይወት በስነ ልቦና ማዘጋጀት፣ በአካሏ/ሉ ላይ ሊከሰት የሚችል ስቃይን በተቻለ መጠን መቀነስ፣ በመንፈሳዊ ህይወቷ/ቱ ማድረግ የምትፈልገውን ነገር እንድታደርግ/እንዲያደረግ በተቻለ ማመቻቸትን የሚያካትት እንክብካቤ ነው።

ቀጥሎ ባለው ክፍል በሀገሪቱ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለማከም የተተገበሩ ዋና ዋና ምላሾችን ለመቃኘት እሞክራለሁ። ይህም ማለት ይህ ጽሁፍ የሚዳስሰው ከላይ በምስሉ ላይ ካሉት ሳጥኖች ውስጥ፡ ሳጥን አንድና ሁለትን ይሆናል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፣ በኢትዮጵያ ለወረርሽኙ የተሰጠውን ምላሽ በሽታውን በመከላከልና በሽታውን በማከም ረገድ የተሰጡ ምላሾች በማለት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።

## 2.1 በሽታውን በመከላከል በኩል የተወሰዱ ዕርምጃዎችና የተሰጡ ምላሾች

በአብዛኛው ወረርሽኞች ሲከሰቱ ሙሉ ለሙሉ ማቆም በጣም አስቸጋሪ ነው። ማድረግ የምንችለው የህመምተኛው ቁጥር በፍጥነት እንዳይጨምር (ቀስ በቀስ እንዲጨምር) በማድረግ በአንድ ጊዜ በበሽታው የሚያዙት ህሙማን ቁጥር የጤና ሥርዓቱ ሊያስተናግደው

የሚችለውን ያህል እንዲሆን መጣር ነው:: ከዚህ በታች ያሉት የወረርሽኝ መስመሮችና (Epidemic Curves) ከስራቸው ያለው መግለጫ ሁኔታውን በተሻለ ለመረዳት ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ::




ምንጭ፡- United States Center for Disease Control (CDC)

በሁለቱም የወረርሽኝ ቀመሮች ላይ ለኛ በግራ ባለው ምስል በቀይ የተሞላውና በቀኝ ባለው መስል በቀይ የተሰመረው፡ የሚያመለክቱት አንድ ወረርሽኝ ተከስቶ ምንም አይነት ዕርምጃ ባንወስድ ሊኖር የሚችለውን የወረርሽኝ መስመር ሲሆን መሀል ላይ በተቆራረጠ አግድሞሽ መስመር የሚታየው ደግሞ የጤና ሥርዓቱ ወረርሽኙን ለመቋቋም ያለውን የመጨረሻ ከፍተኛ አቅም ነው:: መስመሮቹ በግልፅ እንደሚያሳዩት፣ ምንም አይነት የመከላከያ (የማቃለያ) ዕርምጃ ባንወስድ ወረርሽኙ በተከሰተ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጤና ሥርዓቱ አቅም በላይ መሆን ይችላል:: ይህም ማለት፣ ብዙ ሰዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በበሽታው ይያዙና የጤና ሥርዓቱ ሊያስተናግደው ከሚችለው አቅም በላይ ስለሚሆን ብዙዎች ህይወታቸውን ሊያጡ ይችላሉ ማለት ነው::

በአንፃሩ ወረርሽኙ እንደተከሰተ አግባብ ያለው የመከላከል ዕርምጃ የወሰድን እንደሆነ ግን በውሀ አረንጓዴ እንደተሞላውና ደብዘዝ ባለ መስመር እንደተሰመረው የወረርሽኝ መስመር በበሽታው የሚያዙት ሰዎች ቁጥር በአንድ ጊዜ ወደ ላይ ከመውጣት ይልቅ ቀስ በቀስ ስለሚጨምር መስመሩ ወደ ላይ ከማደግ ይልቅ ወደ ጎን ይሰፋል::

ይህም ወደ ጎን መስፋት በስተግራ ባለው ምስል ላይ እንደሚታየው ከመጀመሪያውኑ በአንድ ጊዜ በበሽታው የሚያዙት ሰዎች ቁጥር ከጤና ሥርዓቱ አቅም በታች ሆኖ በበሽታው የተያዙት ህሙማን ተገቢውን ህክምና ማግኘት እንዲችሉ ያስችላል፤ ወይም ደግሞ በቀኝ በኩል ባለው ምስል ለማሳየት እንደተሞከረው የበሽታው ስርጭት ዝግ ማለት፣ ምንም እንኳን ከጊዜ ብዛት የህሙማኑ ቁጥር ከጤና ሥርዓቱ በላይ ሊሆን ቢችልም፣ የጤና ሥርዓታችንን አቅም ለመገንባት ጊዜ ስለሚሰጠን የበሽታው ሥርጭት ከጤና ሥርዓቱ አቅም በታች ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ ያስችለናል።

ወደ ኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ሁኔታ ስንመጣ፣ ከታች ለማሳየት እንደምሞከረው በጣም ጥሩ የሆነ የመከላከያ ዕርምጃ በመወሰዱ ምክንያት የወረርሽኝ ሁኔታው በስተቀኝ በኩል የሚታየውን የወረርሽኝ ቀመር ይመስላል። ይህም ማለት በበሽታው የሚጠቁት ሰዎች ቁጥር ዝግ ባለ ፍጥነት ከመሔዱም ባሻገር የጤና ሚኒስቴር የጤና ሥርዓቱን አቅም ለማሳደግ በርካታ ዕርምጃዎችን በመውሰዱ እነሆ በአሁኑ ሰዓት (በነሀሴ ወር 2012 አጋማሽ ላይ) በሁለት መቶዎች የሚቆጠሩ በፅኑ የታመሙ ህሙማንን በፅኑ ህሙማን ማከሚያ ክፍል ማከም ተችሏል። ይህ በቅርብ ጊዜ ከ50 በታች ብቻ የፅኑ ህሙማንን የማከም አቅም ለነበራት ሀገር ትልቅ ዕመርታ ነው።

ከዚህ በታች የኮቪድ-19 ዋና ዋና መከላከያ መንገዶችን እያንዳንዳቸውንና በኢትዮጵያም የተሰጡትን ምላሾች በዝርዝር እንመለከታለን።

### 2.1.1 የእጅ ንፅህናን በአግባቡ መጠበቅ

እጃችን በጣም የታወቀ የበሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ከአካባቢያችን ወደ ሰውነታችን የሚያጓጉዝ ድልድይ ነው። በአካባቢያችን ያሉ በበሽታ አስተላላፊ ህዋሳት የተበከሉ ቁሳቁሶችን በእጃችን አለመንካት በጣም

ከባድ ነው። በተበከለ እጃችን የሰውነት ክፍላችንን በተለይም ፊታችንን አለመንካትም ቀላል አይደለም። እጅን በተደጋጋሚ በአግባቡ በመታጠብ በሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ከእጃችን ላይ ማስወገድ ግን በጣም ቀላልና ልንተገብረው የምንችል ነገር ነው። የኮሮና ቫይረስ በተለያዩ በአካባቢያችን በሚገኙ ቁሳቁሶች ላይ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይ በተለያዩ ጥናቶች ተረጋግጧል። በአካባቢያችን ያሉ ቁሳቁሶችንም የተለያዩ ሰዎች ስለሚነካኳቸው በኮሮናና በሌሎች በሽታ አስተላላፊ ህዋሳት በቀላሉ ሊበከሉ ይችላሉ። እጃችንን በውሀና ሳሙና በሚገባ መታጠብ የበሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ከእጃችን ላይ በሁለት መንገድ ሊያስወግድልን ይችላል፣ አንድም ህዋሱን ከእጃችን ላይ በማስወገድ ሌላው ደግሞ ህዋሱን በመግደል። ውሀና ሳሙና በማይገኙበት ወቅት፣ የአልኮል መጠኑ ከ62% በላይ የሆነ የእጅ ማጽጃ ኬሚካል መጠቀም ተመሳሳይ የሆነ ውጤት እንደሚሰጥም ይታመናል። በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አብዛኛው ሰው እጁን የሚታጠበው ለ6 ሴኮንድ ብቻ ሲሆን፣ 5% ያህሉ ብቻ ከ15 ሴኮንድ በላይ ለሆነ ጊዜ የሚታጠቡ ናቸው። ከእጅ መታጠቡ ዕኩል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና በአብዛኛው የሚዘነጋው ጉዳይ የታጠቡትን እጅ በሚገባ ማድረቅ ነው። እስካሁን ድረስ በተደረጉ ጥናቶች እጅን መታጠብ ቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የኮቪድ-19ን ስርጭት በምን ያህል ሊቀንስ እንደሚችል የተረጋገጠ አኃዝ የለም።

### *ሀ) በኢትዮጵያ እጅን በመታጠብ የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የተሰጡ ምላሾች*

እጅ የመታጠብ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ የተጀመረው በሽታው በሀገሪቱ ከመከሰቱ በፊት ገና የዓለም ጤና ድርጅት የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት እጅን በተደጋጋሚ በሚገባ መታጠብ ያለውን ጠቀሜታ እንዳስታወቀ ነበር። በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን የእጅ መታጠብን አፈላጊነት በሰፊው ከመዘገባቸው አልፎም የሀገሪቱ ከፍተኛ

ባለስልጣናት (ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ) በሚዲያ ወጥተው የእጅ መታጠብን አስፈላጊነትና ትክክለኛውን የእጅ አስተጣጠብ ስርዓት በመገናኛ ብዙሀን አሳዩ:: እነዚህ መልዕክቶችና ህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረው የኮቪድ-19 ፍራቻ በሀገሪቱ ውስጥ እጅን በአግባቡ የመታጠብ የልቡና-ውቅር (Paradigm Shift) አምጥቷል ብዬ አምናለሁ:: በሀገሪቱ እንደ ቅንጦት ይታይ የነበረው አልኮል ነክ የሆነ የእጅ ማጽጃ ኬሚካል፣ የመጀመሪያው የኮቪድ-19 በሽተኛ በተዘገበበት ዕለት ከፋርማሲዎችና ሱፐር ማርኬቶች መደርደሪያ ላይ መጥፋት፣ ብሎም ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የኬሚካሉ ምርት በየቦታው ተስፋፍቶ እያንዳንዱ ሰው እንደ ሽጉጥ ታጥቆት ሲሄድ ማየት በሀገሪቱ የእጅ ንፅህናን መጠበቅ ለኮቪድ-19 መከላከል አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው ያመለክታል:: በአሁን ሰዓት፣ ምንም እንኳን የውሀ ዕጥረት በሰፊው ቢኖርም በአብዛኛው የመገበያያ ቦታዎች (በጣም ትንንሽ የሆኑትንም ሳይቀር)፣ የእጅ መታጠቢያ የሌለበት ቦታ አለ ለማለት አይቻልም:: የበጎ ፈቃድ ወጣቶችም በየጎዳናው የእጅ ማስታጠብ ሥነ-ስርዓትን በማካሄድ በህብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤና ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያደረጉት ጥረት በእጅጉ የሚደነቅ ነው:: እጅ መታጠብን በተመለከተ አሁንም ክፍተት የሚታይበት፤ በምንታጠብበት ጊዜ ለ20 ሰከንዶች መቆየትና የታጠቡትን እጅ በሚገባ ማድረቅ ላይ ነው:: በተለይ የታጠቡትን እጅ በማድረቅ በኩል ከፍ ያለ ክፍተት መኖሩን ስንዘዋወር አስተውለናል:: ይህም በሚገባ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

### *ለ) የአፍና አፍንጫ ጭንብል በሚገባ ማድረግ*

አፍና አፍንጫን በሚገባ መሸፈን በርካታ ከሆኑ በትንፋሽ የሚተላለፉ (በተለይም በቫይረስ አማካኝነት ከሚመጡ) በሽታዎች በቀላሉ ሊከላከልልን እንደሚችል ለረጅም ጊዜ የሚታወቅ እውነታ ነው:: የአፍና አፍንጫ ጭንብል የታመመው ሰው ሲያደርገው በማሳል፣

በማስነጠስ፣ ጮክ ብሎ በመናገር ወዘተ. ጊዜ ከአፍና ከአፍንጫ የሚወጣውን በሽታ አምጪ ህዋስ አጥር ሆኖ በማስቀረት ወደሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ያደርጋል። ምንም እንኳን ይህ የቆየ መረጃ ቢኖርም፤ የአፍና አፍንጫ ጭንብል የኮቪድ-19 በሽታን የመከላከሉ ነገር ግን አወዛጋቢ እንደሆነ ቆይቷል። ይህም የሆነበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

(i) **የኮቪድ-19 በሽታ የመተላለፊያ መንገድ ህዋሱ በአየር ላይ ተጉዞ ወይም አየር ላይ ቆይቶ (airborn method) ነው? ወይስ ህዋሱ ያለበት ሰው ባሳለ ወይም ባስነጠሰ ጊዜ ከሰውነቷ(ቱ) የወጣ ፈሳሽ ቁሳቁስ ላይ አርፎ ጤነኛ የሆነ ሰው በእጁ አማካኝነት ወደ አፉና አፍንጫው ሲወስደው ወይንም ፈሳሹ በቀጥታ በጤነኛው ሰው አፍና አፍንጫ አካባቢ ሲያርፍ (droplet method) ነው**? በወረርሽኙ መጀመሪያ አካባቢ በሰፊው ተቀባይነት ያገኘው ሁለተኛው መተላለፊያ መንገድ ነበር። ሆኖም ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የመጀመሪያው መተላለፊያ መንገድ ዋነኛ መተላለፊያ መንገድ ሊሆን ይችላል የሚሉ ብዙ መረጃዎች መውጣት ጀመሩ። በቅርቡም ከ200 በላይ የሆኑ ሳይንቲስቶች የዓለም ጤና ድርጅት የኮቪድ-19 ዋነኛ መተላለፊያ አየር-ወለድ መንገድ (airborn method) ነው ብሎ መመሪያውን እንዲለውጥ ጠይቀዋል። በሁለቱ መተላለፊያ መንገዶች ያለው ልዩነት በዋነኛነት የቫይረሱ የክብደት መጠን ነው። ይህም ማለት በአየር ላይ ተጉዞ ወይም አየር ላይ ቆይቶ ይተላለፋል ስንል የቫይረሱ የክብደት መጠን በአንፃራዊ ዝቅተኛ ነው ማለታችን ሲሆን፤ በአንፃሩ የህዋሱ መተላለፊያ መንገድ ህዋሱ ያለበት ሰው ከሰውነቷ(ቱ) በሳል ወይም በማስነጠስ የወጣ ፈሳሽ ቁሳቁስ ላይ አርፎ ጤነኛ የሆነ ሰው በእጁ አማካኝነት ወደ አፉና አፍንጫው ሲወስደው ወይም ፈሳሹ ቀጥታ በጤነኛው ሰው አፍና አፍንጫ አካባቢ ሲያርፍ ነው ስንል ደግሞ የቫይረሱ የክብደት መጠን በአንፃራዊ ከፍ ያለ ነው ማለታችን ነው። መተላለፊያ መንገዱ የትኛውም ይሁን ለሁለቱም መንገዶች የአፍና የአፍንጫ ጭንብል

ማድረግ የበሽታውን መተላለፍ ለመግታት የጎላ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ብዙዎች ይስማማሉ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የአፍና የአፍንጫ ጭንብል ቫይረሱ ከታመመው ሰው ወደውጪ እንዳይወጣ ማድረግ ስለሚችል ነው። ይህም ‹‹በሽታውን ከመነሻው መቆጣጠር›› (source control) ይባላል።

(ii). **ሁለተኛው የውዝግብ ምክንያት፡ ምልክቱ ያልታየበት ሰው በሽታውን ማስተላለፍ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ነው**። እዚህም ላይ በወረርሽኙ መጀመሪያ አካባቢ የበሽታው ምልክት የሌለበት ሰው በሽታውን አያስተላልፍም የሚል ዕምነት ነበር። በዚህም ምክንያት የአፍና የአፍንጫ ጭንብሉን የበሽታው ምልክት የሚታየበት ሰው ብቻ ያድርግ የሚለው ሀሳብ በብዛት ተቀባይነት አግኝቶ ቆይቷል። ሆኖም ግን ወደ በኋላ የተለያዩ ጥናቶች ምንም ምልክቱ ያልታየበት (asymtomatic)፣ ምልክቱ ከመታየቱ ጥቂት ቀናት በፊትም ሆነ (Pre-symptomatic) ምልክቱ እየታየበት ያለ (symptomatic) ሰው ሁሉ በሽታውን ማስተላለፍ እንደሚችል በማሳየታቸው፣ ሁሉም ሰው የአፍና የአፍንጫ ጭንብል ቢያደርግ የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ታምኖበታል። የአሜሪካ የበሽታዎች ቁጥጥር ማዕከል (US-CDC) ከታች ከተዘረዘሩት የሕብረተሰብ ክፍሎች በስተቀር ሁሉም ሰው የአፍና የአፍንጫ ጭንብል እንዲያደርግ ይመክራል። ጭንብል እንዳይደርጉ የሚመከሩት ክፍሎች፡-

- ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፤
- የመተንፈስ ችግር ያለባቸው ሰዎች፤
- ራሳቸውን የሳቱና ያለ ሰው ዕርዳታ ጭንብላቸውን ማውለቅ የማይችሉ ናቸው።

እነዚህን ውዝግቦች አልፈን ጭንብል የማድረግን አስፈላጊነት ስናምንበት የሚከተለው ጥያቄ፣ የትኛው አይነት ጭንብል ነው

በሽታውን በሚገባ የሚከላከልልን? የሚለው ነው። በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሚታወቁ ሦስት አይነት የአፍና የአፍንጫ ጭንብሎች አሉ። እነሱርም 1ኛ) ኤን 95 (N95) ጭንብል፣ 2ኛ) ሰርጂካል/ሜዲካል ጭንብል እና 3ኛ) በቤት ውስጥ/ከጨርቅ የሚሰራ ጭንብል ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች የሚጠቀሰውንና በአብዛኛው የሕክምና ባለሙያዎች የአየር ቧንቧ አካባቢ የሚሰራና ብዙ ብናኝ (aerosol) የሚያመጣ የሕክምና ሂደት (medical/surgical procedure) በሚሰሩበት ጊዜ የሚጠቀሙበትን አራተኛ አይነት ጭንብል እዚህ ማካተቱ ጥቅሙ ስላልታየኝ ትቼዋለሁ። ከታች የሚገኙት ሁለት ሠንጠረዦች የሦስቱን ጭንብሎች ባህርይ፣ ጥቅምና ጉድለቶች ያሳያሉ።

| የጭንብሉ አይነት | የጭንብሉ ባህርይ | የጭንብሉ ጥቅም | የጭንብሉ ጉድለቶች |
|---|---|---|---|
| ኤን 95 | - አፍና አፍንጫን ጥብቅ አድርጎ ይሸፍናል። (የማጣራት ኃይሉ 95% ይደርሳል)።<br>- የጤና ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት። | ❖ በጠብታና በብናኝ የሚተላለፉ ሕዋሳትን በከፍተኛ ሁኔታ የመከላከል ብቃት አለው። | • በየጊዜው አፍና አፍንጫን ጥብቅ አድርጎ መያዙን ማረጋገጥ ይኖርብናል።<br>• የአቅርቦት ዕጥረት<br>• የዋጋ ውድነት |
| ሰርጂካል | - አፍና አፍንጫን ጥብቅ አድርጎ አይሸፍንም።<br>- የጤና ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት ። | ❖ ርካሽና በቀላሉ የሚገኝ<br>❖ ከኤን 95 ስር መጠቀም ይቻላል። | • አየር በቀላሉ ያስገባል<br>• ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል። |
| የጨርቅ | - አፍና አፍንጫን ጥብቅ አድርጎ አይሸፍንም።<br>- ማንኛውም የሕብረተሰብ አባል የሚጠቀምበት። | ❖ ቤት ውስጥ መሰራት የሚችል፣ ታጥቦ እንደገና የሚያገለግል<br>❖ ሰርጂካል ጭንብልን ይቆጥብልናል። | • በአየር ላይ ያሉ ብናኝ ህዋሳትን ለመከላከል ብቁ አይደለም። |

ምንጭ: Respiratory Protection During Outbreaks: Respirators versus Surgical.https://blogs.cdc.gov/niosh-science-blog/2020/04/09/masks-v-respirators/

| የጭንብሉ አይነት | ለአቪያን ኢንፉሌንዛ የመከላከል ሀይሉ በፐርሠንት |
|---|---|
| ኤን 95 ጭንብል | 99.98% (99.98% — 99.99%) |
| ሰርጂካል ጭንብል | 97.14% (94.36% - 98.55%) |
| የጨርቅ ጭንብል | 95.15% (90.97% - 97.39%) |

ምንጭ: Potential utilities of mask-wearing and instant hand hygiene for fighting SARS-CoV-2. J Med Virol. 2020

ከላይ ያሉት ሁለት ሠንጠረዦች እንደሚያሳዩት ሁለቱን መጀመሪያ ላይ የተጠቀሱት ጭንብሎችን የጤና ባለሙያዎች ቢጠቀሙባቸው፣ ሦስተኛውን ደግሞ የቀረው ማህበረሰብ ቢጠቀምበት የኮቪድ-19ኝ ወረርሽኝን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ ይቻላል:: በቤት ውስጥ መሰራት የሚችለው የጨርቅ ጭንብል የመከላከል ሀይል እንደተሰራበት የጨርቅ አይነት፣ በድርቡ ቁጥር፣ ወደ አፍና አፍንጫ አየር ባለማስገባቱ መጠንና በጨርቁ እርጥበት መጠን ይወሰናል:: በዚህም መሠረት የጥጥና ሀር ቅልቅል፣ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ድርብ ሆኖ የተሰራ፣ አፍና አፍንጫ ላይ በደምብ ጥብቅ ብሎ አየር የማያስገባና የእርጥበት መጠኑ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የጨርቅ ጭንብል የቫይረስ ህዋስ በአፍና አፍንጫ በኩል ወደ ሰውነታችን እንዳይገባ በጥሩ ሁኔታ ሊከላከልልን እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ:: የጨርቅ ጭንብል፤ ያደረገውን ሰው ከበሽታ ከመከላከል በላይ፤ ጭንብሉን ያደረገው ሰው በሽታ ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፍ ይረዳል:: ስለሆነም በማሕበረሰቡ ውስጥ ብዙ ሰው ጭንብሉን ባደረገ ቁጥር የበሽታው ስርጭት በሕብረተሰቡ ውስጥ ያነሰ ይሆናል:: ከታች ያለው ምስል የጭንብሉ በሽታውን መጠን የመቆጣጠር ሀይል በጭንብሉ ጥራት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን፣ በጭንብሉ ጥራትና (efficacy) በሕብረተሰቡ ውስጥ በመደረግ መጠኑ (adherence) ጋር የተያያዘ መሆኑን ያመለክተናል:: ብዙ የሕብረተሰብ ክፍል ያደረገው መካከለኛ ጥራት ያለው ጭንብል፣ በጣም ጥራት ካለው ግማሽ ያህል የሕብረተሰብ ክፍል

ካደረገው ጭንብል ጋር ዕኩል የሆነ ውጤት እንዳለው በምስሉ ላይ ይታያል።




Source: L Tian, et al., "Calibrated intervention and containment of the covid-19 pandemic" (2020), https://arxiv.org/abs/2003.07353, page 10 of the Supplementary Materials. Also see Howard et al. "Face Masks Against COVID-19: An Evidence Review," *Preprints* 2020, https://www.preprints.org/manuscript/202004.0203/v1.

በኢትዮጵያ አፍና አፍንጫን መሸፈን የተለመደ ባህል ነው ወይስ አይደለም የሚለው አነጋጋሪ ነው። ቆየት ባለው ጊዜ እና አሁንም በአንዳንድ የገጠር ሀገሪቱ ክፍሎች አፍና አፍንጫን በሸማ/በነጠላ መሸፈን የተለመደ መስተጋብር ነው። ሆኖም ግን አብዛኛው ሰው እንደሚስማማበት ይህ መስተጋብር በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል እምብዛም ሲተገበር አይስተዋልም።

የአፍና አፍንጫ ጭንብልን መጠቀም ለኮቪድ-19 መከላከል ጠቀሜታ እንዳለው ከተለያዩ አካላት በተገለፀበት ጊዜ የተለያየ አይነት ጭንብሎች በሰፊው መሰራጨት ጀመሩ። በብዙ ቦታዎችም የጨርቅ ጭንብሎች በብዛት መመረት ጀመሩ። ሕብረተሰቡም ጭንብሎችን አድርጎ መጓዝን ባሕል አድርጎ እየተቀበለው መጣ። በመንግስት በኩልም በጤና ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ተቋም አማካኝነት በርካታ የግንዛቤ ትምህርቶች ይሰራጩ ጀመር። በሐምሌ 23 ቀን 2012 ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ ጭንብል ሳያደርግ ከቤቱ ውጪ እንዳይዘዋወር የሚደነግግ ደንብ ወጣ፤ ደንቡንም ለመተግበር የፀጥታ

አካላት ዕርምጃ መውሰድ ጀመሩ:: የዚህ ትምህርትና አስገዳጅ ደንብ ውጤትም አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል የአፍና አፍንጫ ጭንብል አድርጎ እንዲንቀሳቀስ አድርጎታል::

ሰዎች የአፍና አፍንጫ ጭንብል አድርገው እንዲንቀሳቀሱ የወጣውን ሕግ አክብረው የፊት ማስክ አድርገው ሲንቀሳቀሱ

ሕግ የተላለፉ ግለሰቦች በሕግ አስከባሪዎች በአደባባይ ተይዘው

### 2.1.2 አካላዊ ርቀትን መጠበቅ (Social/Physical distancing)

በኮሮና ቫይረስ የታመመ ሰው (ምልክት ኖረውም አልኖረው)፣ በቅርብ ርቀት ሆኖ በሚያስልበት፣ በሚያስነጥስበት ወይም ጮክ ብሎ በሚያወራበት ጊዜ ከአፍና አፍንጫው የሚወጣ ቫይረሱ ያለበት ብናኝ (droplet) አጠገቡ ባለ ያልታመመ ሰው አፍና አፍንጫ ላይ ሊያርፍና በሽታው ሊተላለፍ ይችላል:: አንድ ቤት ውስጥ አብሮን ከማይኖር ሰው ጋር በቅርብ ርቀት ፊት ለፊት መገናኘትን ማስቀረት የኮቪድ-19 ዋነኛ መከላከያ መንገድ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ:: የአሜሪካ የበሽታዎች መቆጣጠሪያ ድርጅት (US-CDC) አካላዊ ርቀትን መጠበቅ በተለይም ኮቪድ-19ኝን ከመከላከል አንፃር ሲገልፀው እንዲህ ይላል:: ‹‹አካላዊ ርቀት ማለት በተቻለ መጠን መሰባሰብን ማስቀረት፣ ብዙ ሰዎች ከሚገኙበት/ከሚሰባሰቡበት ቦታ መራቅና ከሌላ ሰው ጋር ቢያንስ በስድስት ጫማ (ሁለት ሜትር) ያህል መራቅ ማለት ነው››:: የዓለም ጤና ድርጅት የመራራቁን ርቀት ወደ ሦስት ጫማ (አንድ ሜትር) ዝቅ

ያደርገዋል። በስድስት ክፍለ ዓለማት፣ በ16 አገሮች የተሰሩ 25,697 ሰዎችን ያካተተ የ172 ጥናቶችን ግኝት የመረመረና የተነተነ (systematic review and meta-analysis) አንድ ፅሁፍ፣ አንድ ሜትርና ከዚያ በላይ ርቀትን መጠበቅ ኮቪድ-19ኝን ለመከላከል ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ አሳይቷል። ከታች የሚታየው ምስል ርቀትን መጠበቅ ምን ያህል የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መስመርን እንደሚቀንሰውና (flattening the curve) የተወሰዱ ዕርምጃዎች መላላት ደግሞ ምን ያህል የወረርሽኙን መስመር ከፍ ሊያደርገው እንደሚችል ያሳያል። ከምስሉ የምንረዳው ርቀትን መጠበቅ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን መስመር መቀነስ ብቻ ሳይሆን፣ ኮቪድን ለመከላከል ሲባል የተዘጉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን (lockdown) ስንከፍት አካላዊ ርቀትን ጠብቀን ብንከፍት፣ የወረርሽኙን መስመር መጨመር (ዕድገት) ጥሩ በሚባል ሁኔታ ልናሳነሰው እንደምንችል ነው።




በጊዜው የነበረውን የሌሎች አገሮች ተሞክሮና፣ አካላዊ መራራቅ ለኮቪድ-19 መከላከል ያለውን ጠቀሜታ የሚያመለክቱ ሳይንሳዊ መረጃዎችን ከግምት በማስገባት፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኮቪድ-19 ተጠቂ በተገኘ በሶስተኛው ቀን (መጋቢት 7 ቀን 2012)፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አካላዊ ቅርርብ ሊፈጥሩ የሚችሉ ቦታዎችና ክስተቶች (ትምህርት ቤቶች፣ ሲኒማ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣

የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ ወዘተ) እንዲዘጉና እንዲቋረጡ ውሳኔ አስተላለፉ:: የህዝብ ማመላለሻ መኪናዎችም በግማሽ አቅማቸው ብቻ ተገልጋዩን እንዲያስተናግዱ ተወሰነ:: በአገልግሎት መስጫ ተቋማት (አገልግሎት ሰጪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደ ገቢዎች ያሉ፣ ባንኮች፣ ሱቆች፣ የትራንስፖርት ወረፋ መጠበቂያዎች ወዘተ) የተለኩ መስመሮችን በማስመርና ገመድ በማሰር ርቀትን ጠብቆ መስተናገድ ቀስ በቀስ እየተለመደና እየተዘወተረ መጣ:: ይህ ወረፋ በመጠበቅ ጊዜ መገፋፋትን እንደነውር ለማይቆጥር ሕብረተሰብ ከፍተኛ ለውጥ በመሆኑ ትንሽ አስቸጋሪ ቢሆንም ሕብረተሰቡ ግን በበርካታ ቦታዎች ሲተገብረው ታይቷል::

## 2.1.3 የኮቪድ-19 ቅኝት (COVID-19 surveillance)

እንደሚታወቀው የወረርሽኝ/የተላላፊ በሽታ ቅኝት የሚጀምረው በላቦራቶሪ ምርመራ የተረጋገጠ በበሽታው የተጠቃ ግለሰብን ለይቶ ከማወቅ/ከማግኘት ነው:: ከዚያም ግለሰቡን በበሽታው ካልተያዙ ሰዎች በመለየት ማከም፣ ከግለሰቡ ጋር የአካል ቅርርብና ንክኪ የነበራቸውንና በዚህም ምክንያት ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎችን መፈለግ (contact tracing)፣ ለይቶ ማቆየት (quarantine) በቅርበት መከታተልና እንዳስፈላጊነቱ መመርመርን ያካትታል:: በተላላፊ በሽታ ከተያዘ ሰው ጋር የአካል ቅርርብ የነበራቸውንና በዚህም ምክንያት ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎችን መፈለግ (contact tracing) በስርዓት (systematically) ሲተገበር በተላላፊ በሽታ አማካኝነት የሚመጣ ወረርሽኝ ስርጭትን ለመከላከል ከፍ ያለ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የተረጋገጠ እውነታ ነው:: ለኮቪድ-19 የተጋለጡ ሰዎችን መፈለግ፤ የተጋለጡትን ሰዎች ከማወቅ ጀምሮ ከበሽተኛው ጋር በአካል ከተገናኙበትና ለበሽታው ተጋልጠዋል ተብሎ ከሚገመትበት ቀን ጀምሮ ለ14 ቀን ለይቶ ማቆየትንና በቅርብ መከታተልን ያካትታል:: ይህ የተላላፊ በሽታ ወረርሽኝ መከላከያ መንገድ ከላይ እንዳየናቸው

የመከላከያ መንገዶች ብዙም የማያከራክር፣ በአብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች ተቀባይነት ያለውና እንዴት ስርጭቱን መከላከል እንደሚችልም ከሌሎቹ የመከላከያ መንገዶች በበለጠ ለመረዳት የቀለለ ነው።

## 3 በኢትዮጵያ የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የኮቪድ-19 ቅኝት (surveillance) በመተግበር በኩል የተወሰዱ ዕርምጃዎች

የኮቪድ-19 በኢትዮጵያ በተከሰተበት ወቅት በሀገሪቱ የኮቪድ-19 ምርመራ የማድረግ አቅምም ሆነ የመመርመሪያው ቁሳቁስ (test kit) አልነበረም። በኋላም ኮቪድ-19ን የመርመር አቅም መገንባት ተችሎ ቀስ በቀስ በሀገሪቱ በየቀኑ የሚደረገው የኮቪድ-19 ምርመራ ብዛት በመጨመር በሐምሌ ወር መጨረሻ አካባቢ በቀን 9,000 ሰው የመመርመር አቅም ላይ ደረስን። ከነሀሴ 30 ቀን 2012 ጀምሮ በሀገሪቱ በ15 ቀን ውሰጥ 200,000 ሰው ለመመርመር የዘመቻ ፕሮግራም ታቅዶ ተተገበረ። የዘመቻው ዕቅድ በቀን እስከ 15,000 ሰው ምርመራ ለማድረግ ቢሆንም፣ በሁሉም ክልልሎች በተሰራጩ 46 ማዕከሎችና 59 የመመርመሪያ መሣሪያዎች በመታገዝ በቀን ከ20,000 በላይ ምርመራዎችን ማካሔድ ተችሎ ነበር። በመስከረም 2013፣ ኢትዮጵያ ከቻይና ካምፓኒ ጋር በመተባበር፣ በዓመት 10 ሚሊዮን የኮቪድ-19 መመርመሪያ ቁሳቁስ (test kit) ማምረት የሚችል ፋብሪካ አቋቋመች። ይህም ፋብሪካ ለጎረቤት አፍሪካ ሀገሮችም ቁሳቁሱን የማቅረብ ዓላማ አለው። እስከ መስከረም 24 ቀን 2013 በተጠናቀረ ዘገባ 1,301,570 የኮቪድ-19 ምርመራዎች በሀገሪቱ ተደርጓል። ይህም አገሪቱን ብዙ በመመርመር ከአፍሪካ ሦስተኛ፤ ከምስራቅ አፍሪካም ደግሞ አንደኛ አድርጓታል።

ይህን በአጭር ጊዜ ውስጥ የተከናወነ የላቦራቶሪ አቅምን የመገንባት ጥረት እጅግ የሚያስገርም እና የጤና ሚኒስትርንና የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ተቋምን በጣም የሚያስመሰግን ተግባር ነው ብዬ

አምናለሁ። ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የወረርሽኝ ቅኝት ስንል መርምሮ በበሽታው የተያዘን ሰው ማግኘት ብቻ ሳይሆን፤ ከተያዘው ሰው ጋር አካላዊ ቅርርብ የነበራቸውንና ለበሽታው ሊጋለጡ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ግለሰቦችም ማወቅ፣ ለይቶ ማቆየትና የላቦራቶሪ ምርመራ ማድረግን ያካትታል። በዚህም ረገድ በኢትዮጵያ መጠነ ሰፊ የሆነ ሥራ ተሰርቷል። መስከረም 24 ቀን 2013 በተጠናቀረ ዘገባ መሠረት፡-

- 257,087 ከበሽተኛ ጋር የአካል ቅርርብ የነበራቸው ሰዎች ተደርሰዋል/ ተገኝተዋል፤
- 230,896 (89.8%) የሚሆኑት የ14 ቀን ክትትልን በሚገባ ሲጨርሱ 7,112 አሁንም በክትትል ላይ ነበሩ፤
- በክትትል ላይ ከነበሩት (ክትትላቸውን የጨረሱና አሁንም በክትትል ላይ ያሉ በአንድነት) ውስጥ 399ኙ (0.16%) የኮቪድ-19 ምልክት ታይቶባቸዋል፣ ምልክት ከታየባቸውም ውስጥ 363 (90.98%) በሽታው እንዳለባቸው በላቦራቶሪ ተረጋግጧል፤
- በአጠቃላይ ከበሽተኛ ጋር የአካል ቅርርብ ከነበራቸው ሰዎች (contacts) መካከል፤ 18,615 (7.24%) ያህሉ በሽታው እንዳለባቸው በላቦራቶሪ ተረጋግጧል፤
- በዚህም መሠረት በሀገሪቱ በጠቅላላ በሽታው እንዳለባቸው ከተረጋገጡት 23.62 በመቶ የሚያህሉት የተገኙት ከበሽተኛ ጋር የአካል ቅርርብ ነበራቸው ተብለው በላቦራቶሪ ከተመረመሩ ሰዎች መካከል ነው።

ሌላው የመመርመርና ለይቶ የማቆየት ስራ የተሰራው ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ መንገደኞች ላይ ነው። በዚህ ረገድ ወረርሽኙ በዓለም ላይ መከሰቱ ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ እስክ መስከረም 24 ቀን 2013 ድረስ 1,134,653 መንገደኞች ላይ የኮቪድ-19 ምልክት

እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚጠቁም ምርመራ (screening) ተደርጓል:: ከነዚህ ውስጥ 436,818ቱ (38.5%) የተመረመሩት በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ነው:: ከመጋቢት 13 ቀን 2012 ጀምሮ ማንኛውም ከውጪ አገር የሚመጣ ሰው በለይቶ ማቆያ ቦታ እንዲቆይ የሚያስገድድ ደንብ ወጣ:: በዚህም መሠረት እስከ መስከረም 24 ቀን 2013 በተጠናቀረው መረጃ 68,974 መንገደኞች በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ በኩል አልፈዋል፤ ከነዚህ ውስጥም 34,666 (50.3%) መንገደኞች በአዲስ አበባ ነበሩ::

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ተቋም በኢትዮጵያ ኮቪድ-19ን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያስችላሉ ተብሎ በሳይንቲፊክ ማሕበረሰቡ የታመነባቸውን ዕርምጃዎች በሀገሪቱ ለመተግበር ወይም እንዲተገበር ሕብረተሰቡን በማስተማርና በማነሳሳት ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል:: ሌላ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ የምንረዳው ነገር፣ ከአራተኛው የመከላከያ መንገድ (የኮቪድ-19 ቅኝት) በስተቀር ሦስቱ የመከላከያ መንገዶችን መተግበር በንፅፅር በሽታውን ከማከም ጋር ሲተያይ ብዙ የገንዘብ ወጪ የማይፈልጉ በመሆናቸው በሀብታምና በድሀ ሀገሮች መሀከል እጅግ በጣም የሰፋ የመተግበር ልዩነት ላይታይ ይችላል ብዬ አምናለሁ::

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የኢትዮጵያ መንግስት በተለይም የጤና ሚኒስትር እና የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ተቋም የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል አመርቂ ነው የሚባል እና ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ወረርሽኞች በተከሰቱበት ጊዜ ከተወሰዱት ዕርምጃዎች በንጽጽር ሲታይ የተሻለ የሚባል ምላሽ ሰጥተዋል ብዬ አምናለሁ:: አንዳንዶች የተወሰዱት ዕርምጃዎች መተግበር ከነበረባቸው ጊዜ ፈጥነዋል በማለት ሲተቹ ይሰማል:: በኔ ግምት ግን የተወሰዱት ዕርምጃዎች አግባብ ያላቸው፤ ወቅታዊና አሁን ለምናየው የወረርሽኙ መስፋፋት ፍጥነት ማዝገም አስተዋፅዖ አድርገዋል ብዬ አምናለሁ::

ሌላው በአፅንዖት ሊታሰብ የሚገባው ነገር እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የመከላከያ መንገዶች ለብቻ ወይም በተናጠል በሽታውንና የበሽታው መስፋፋት የመከላከል ብቃታቸው አናሳ መሆኑንና ውጤታቸውን በጥሩ ሁኔታ ለማየት በአንድነት መተግበር የሚኖርባቸው መሆኑን ነው፡፡

## 4 በሽታውን በማከምና ታማሚዎችን በመንከባከብ በኩል የተወሰዱ ዕርምጃዎች

ከላይ ***ቀጣይነት/ተከታታይነት ያለው እንክብካቤ*** (continuum of care) በሚለው ርዕስ ስር እንዳየነው፣ በሽታን (ወረርሽኝን) ለመከላከል ምንም ያህል ጠንካራ ዕርምጃዎች ቢወሰዱም የተወሰኑ ሰዎች በበሽታው መያዛቸው አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህም ወረርሽኝን ለመቆጣጠር በምናደርገው ጥረት ወረርሽኙን ከመከላከል ዕኩል በበሽታው የተያዙትን ሰዎች ማከምና መንከባከብም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በበሽታው የተያዙትን ሰዎች በማከምና በመንከባከብ ረገድ የተወሰዱትን ዕርምጃዎች የዓለም ጤና ድርጅት ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለመስጠት የመሠረት ድንጋይ (building blocks) ናቸው ብሎ ባስቀመጣቸው ስድስት መስፈርቶች (ከታች በምስሉ እንደሚታየው) መሠረት ማየት የተወሰዱትን ዕርምጃዎች ጠቀሜታ/አግባብነት ያስረዳል ብዬ ስለማምን የኮቪድ-19 በሽተኞችን ለማከምና ለመንከባከብ የተወሰዱ ዕርምጃዎቹን ከመሠረት ድንጋዮቹ አንፃር ለማየት እሞክራለሁ፡፡




ከላይ በምስሉ እንደሚታየው የመጀመሪያው የመሠረት ድንጋይ የጤና አሰጣጥ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን የሀገሪቱን የኮቪድ-19ም ሆነ ሌሎች ህሙማንን የማከምና የመንከባከብ ዝግጁነት ለመረዳት የሀገሪቱን የህክምና መስጫ ተቋማት አደረጃጀት (Ethiopian Health Tier System) ማወቅ በጣም ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ፡፡ የተቋማቱ አደረጃጀትንም ከታች በሚታየው ምስል እንደምናየው እስከ ቀበሌ ድረስ ስለሚወርድ፣ ለሕብረተሰቡ ያለው የጤና ግልጋሎት ተደራሽነት ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በርግጥ የአደረጃጀቱ መኖር ብቻውን ለሕብረተሰቡ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ስለማያረጋግጥ መስተካከልና የበለጠ መጠናከር ይኖርበታል በሚለው እስማማለሁ፡፡

የኮቪድ-19 ህክምናና እንክብካቤን በተመለከተም በሁሉም ደረጃ ያሉት የጤና ተቋማት እንዲንቀሳቀሱና ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁ ተደርጓል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የመስተካከልና የመጠናከር አስተያየት እንዳለ ሆኖ፤ የህክምና መስጫ ተቋማት አደረጃጀቱ እስከ ቀበሌ ድረስ መውረድና በዕዝ ሠንሰለት የተያያዘ መሆኑ የህክምና አገልግሎቱን ለሕብረተሰቡ በፍጥነት ለማድረስ ዕገዛ ማድረግ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡




ከነዚህ በተለያየ አደረጃጀት ላይ ከሚገኙትና ከኮቪድ-19 በሽታ በፊትም ከነበሩት የጤና ተቋማት በተጨማሪ በሀገሪቱ የተለያየ አካባቢዎች የኮቪድ-19 ህክምናና እንክብካቤ መስጫ ማዕከሎች ተቋቁመዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ እንደ ዋና ምሳሌ የሚታየው ሚሊኒየም አዳራሽ በመባል የሚታወቀውን ግዙፍ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ወደ 1,000 አልጋ የመያዝ ብቃት ወዳለው የኮቪድ-19 ህክምና ማዕከል መለወጥ ነው፡፡

ሁለተኛው የመሠረት ድንጋይ በጤና ተቋማቱ ውስጥ የህክምና ግልጋሎት የሚሰጡትን የጤና ባለሙያዎች እናገኛለን፡፡ በዚህ በኩልም የተወሰዱት ዕርምጃዎችን ስንመለከት የመጀመሪያውና እኔ ከፍተኛ ግምት የምሰጠው፣ መንግስት በሀገሪቱ የመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ ያለውን የባለሙያ ዕጥረት ተገንዝቦ በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ የግልና የመንግስት ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሰሩና በጡረታ ለተገለሉ የጤና ባለሙያዎች የተደረገው ጥሪ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጤና ባለሙያዎቹን ክህሎት ለማሳደግ በርካታ ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ስልጠናዎችን መስጠትና የጤና አገልግሎቱን ሲሰጡም

የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ መመሪያዎችን (guidelines) የማዘጋጀትና የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል።

ሦስተኛውን የመሠረት ድንጋይ በተመለከተም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ኮቪድ-19ን በተመለከተ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የስልክ መስመር (Hotline) አገልግሎት የተጀመረው ገና በሽታው ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱ ከመረጋገጡ በፊት ነበር። ምንም እንኳን በመስተንግዶው ላይ አንዳንድ ቅሬታዎች ቢኖሩም፣ መስመሩን መክፈትና የህዝቡን ጥያቄ ሰምቶ ምላሽ ለመስጠት መሞከር በራሱ እንደ ጥሩ ምላሽ ይቆጠራል ብዬ አምናለሁ። መስመሩ ወደ ጥሪ ማዕከልነት (call center) አድጎ ማስጠንቀቂያዎችንና ጥርጣሬዎችን እየተቀበለ መመርመር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መስከረም 24 ቀን 2013 ድረስ 284,012 ማስጠንቀቂያዎችን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ 220,482ቱ (77.63%) ለበሽታው አጠራጣሪ (fulfill suspected case definition)ሆነው አግኝቷቸዋል ።

በአራተኛው የመሠረት ድንጋይ ውስጥ ኮቪድ-19ኝን በተመለከተ በኢትዮጵያ የተሰጠው ምላሽ በሀገሪቱ የረጅም ጊዜ ተግዳሮት ሆኖ የቆየውን ሰው ሰራሽ የመተንፈሻ መሣሪያ (ventilator) ቁጥር ለመጨመር የተደረገው እንቅስቃሴ ይገልፀዋል ብዬ አምናለሁ። ከላይ እንደተገለፀው ኮቪድ-19 በአብዛኛው የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ በሽታ ነው። ስለሆነም ሰው ሰራሽ የመተንፈሻ መሣሪያ አስፈላጊነት ሳይታለም የተፈታ ነው። በዚህም በኩል የኢትዮጵያ መንግስት የወሰዳቸው ዕርምጃዎች በሀገሪቱ ያሉትንና የተበላሹ መሣሪያዎች መጠገን፣ ዕርዳታ መጠየቅና መግዛትን ያካትታል። በዚህ ረገድ በሀገሪቱ ከነበረው ቁጥር በብዙ መጨመር ቢቻልም አሁንም ግን የሚያስፈልገውን ያህል አልተገኘም። ሆኖም ግን በአስራ ቤቶች ብቻ የሚቆጠሩ ፅኑ ሕሙማንን የማከም አቅም የነበረው የጤና ስርዓት

ከ300 በላይ ፅኑ ህሙማንን ማከም ሲችል ማየት ትልቅ ዕመርታ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በአምስተኛው የመሠረት ድንጋይ የተሰጠ ምላሽ ደግሞ በሀገሪቱ የተካሔደው ኮቪድ-19ኝን ለመከላከልና በበሽታው የተጠቁትን ለማከምና ለመንከባከብ የሚውል መጠነ ሰፊ የሆነ ገንዘብ የማሰባሰብ ፕሮግራም ተነድፎ መተግበሩ ነው፡፡ ከዚያም በላይ በየአካባቢው በወረርሽኙ ምክንያት የዕለት ገቢያቸው በእጅጉ ለቀነሰባቸው ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ የሆነ የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም በስድስተኛው የመሠረት ድንጋይ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ፣ በጤና ሚኒስትር እና በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ተቋም ዋና ዳይሬክተር በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡት አመራሮች አመርቂ ነበሩ ብዬ አምናለሁ፡፡ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የተለያዩ ሚኒስትሮች የተካተቱበት የኮቪድ-19 ግብር-ሀይልም ተቋቁሞ መመሪያዎችን ከማውጣት በተጨማሪ መጠነ ሰፊ የሚባል ዕርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በጤና ሚኒስትር የተመሰረተውና የሚመራው በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚኖሩ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያሳተፈ የመማክርት ጉባዔም ተቋቁሞ ለኮቪደ-19 ምላሽ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረጉ በዚህ የማዕዘን ድንጊያ ውስጥ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተለይም ይህ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገር ጤና ችግር ውስጥ የማሳተፉ እንቅስቃሴ እንደ አንድ ትልቅ ኮቪድ-19 ያመጣው አዎንታዊ ተፅዕኖ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል፡፡ በመጨረሻም በዚህ የመሠረት ድንጋይ ውስጥ መጠቀስ ያለበት የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው መመሪያ ነው፡፡

በአጠቃላይ የኮቪድ-19ኝን ለመከላከልና እንዲሁም በበሽታው የተጠቁትን ለማከምና ለመንከባከብ የተወሰዱትን ዕርምጃዎች ከዓለም ጤና ድርጅት መሠረታዊ የጤና ስርዓት የመሠረት ድንጋይ አንፃር ስናየው በኢትየጵያ ውስጥ አቅም የፈቀደውን ያህል በቂ ምላሽ ለመስጠት የተደረጉ ጥረቶች አሉ ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን ከዚህ በላይ ሊደረግ አይቻልም ማለቴ እንዳልሆነ አፅንዖት እንዲሰጥልኝ እፈልጋለሁ። የበለጠ ግልፅ ለመሆን፣ በአብዛኛው የሳይንትፊክ ሕብረተሰቡ የተስማማበትን የኮቪድ-19ኝን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማከም የሚጠቅሙ ገቢሮች (activities) አቅም በፈቀደ ለመተግበር በጣም ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴ ቢደረግም ወደ ታች ወርዶ አተገባበር ላይ የታዩ ችግሮች መኖራቸውንና እነዚህም ችግሮች መፈታት የሚችሉ መሆናቸውን ለመጠቆም እወዳለሁ።

## 5 በወረርሽኙ ምክንያት የተገኙ አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች

በወረርሽኙ ምክንያት የተገኙ አጋጣሚዎችን ሙሉ በሙሉ ለመዘርዘር አስቸጋሪ ቢሆንም ዋና ዋና ናቸው ያልኳቸውን ጥቂቶቹን ከዚህ በታች እዘረዝራለሁ፡-

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ኮቪድ-19ኝን ለመከላከልና ለማከም የተወሰዱት ዕርምጃዎች በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት ስርዓቱን በተለይም ደግሞ የድንገተኛ ህክምና አሰጣጥ ስርዓቱን በማጠናከር በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል፤

የኮቪድ-19ኝን ለመከላከል የሚወሰዱት ዕርምጃዎች ብዙ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልም አይነተኛ መንገዶች ናቸው። በዚህም ምክንያት በብዛት ይታዩ የነበሩ እንደ ጉንፋን፣ የተቅማጥ በሽታ ወዘተ በጣም መቀነሳቸው ተስተውሏል፤

በአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል በተለይም በወጣቱ ዘንድ የታየው የፈቃደኝነት እንቅስቃሴ በጣም የሚያስደስትና ሌሎች የሀገሪቱ ችግሮችንም ለመፍታት ልንጠቀምበት የምንችል መሆኑን ተምረንበታል፤

በተመሳሳይ ሀገር ውስጥና በውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች የታየው ትብብር እንዲሁ ሊጠናከርና ወደፊትም ሌሎች የሀገሪቱን የጤና ችግሮች ለመፍታት ልንጠቀምበት እንደምንችል የተረዳንበት ሆኖ ተገኝቷል። በተጨማሪም ይህንን የትብብር መንፈስ ወደ ሌሎች ሴክተሮችም በመውሰድ በውጪ ሀገር የሚገኘውን ከፍተኛ የተማረ የሰው ሀይል መጠቀም እንደምንችል ተምረንበታል፤

በተመሳሳይ ኮቪድ-19ን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማከም ብዙ ተግዳሮቶች ቢኖሩም እኔ በጣም የጎሉ ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ለመመልከት እሞክራለሁ።

ዋነኛውና የሁሉም ከታች የሚዘረዘሩት ተግዳሮቶች ምክንያት ይሆናል ብዬ የምገምተው፣ ኮቪድ-19 በቀላሉ የማይለቀንና ረዘም ላለ ጊዜ አብሮን የሚኖር መሆኑ መረጋገጡ ነው። በሰው ልጅና በቫይረስ መካከል እስካሁን ድረስ የተደረጉትን ጦርነቶች ዋቢ በማድረግ ኮቪድ-19 አብሮን የሚኖር በሽታ መሆኑን የገመቱ ብዙዎች ናቸው። ነገር ግን ቀለል ያለ በሽታ (እንደማንኛውም ጉንፋን) ይሆናል ብለው የሚገምቱት የበዙ ናቸው። ይሁን እንጂ መቼ እዚያ ደረጃ ላይ እንደምንደርስ በርግጠኝነት መናገር አልቻሉም።

ከላይ የዘረዘርናቸው የመከላከያ መንገዶች በሙሉ በቀላሉ የሚሰለቹ በመሆናቸው አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ከአሁኑ መሰልቸትና የመከላከያ መንገዶቹን ችላ ማለት ጀምሯል። እንግዲህ ይህ በሽታ

አብሮን ለረጅም ጊዜ የሚኖር መሆኑን ማወቅ ይህ ተግዳሮት ምን ያህል ከባድ መሆኑን መረዳት አያስቸግርም፡፡

በሕብረተሰቡ ውስጥ በቀላሉ የሚሰራጩ መሠረተ-ቢስ ዕምነቶች ኮቪድ-19ኝን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ዕምነቶች ከዚህ በፊት በተከሰቱ (እንደ ኤች.አይ.ቪ. ያሉ) ወረርሽኞችም ታይተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ/ዋነኞቹ፡- ‹‹የእኛ ባህላዊ ምግቦች ቅመማ ቅመም የበዛባቸውና የሚያቃጥሉ በመሆናቸው ቫይረሱን በቀላሉ ይገድሉታል››፣ ‹‹ኢትዮጵያ ከእግዚብሔር የተለየ ጥበቃ ያላት ሀገር ናት›› የሚሉና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፍጥነት የመሰራጨቱና የሰው ሕይወትን መቅጠፉ በጤና ተቋማት ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኝና ለሌሎቹ በሽታዎች (በተለይም ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች) የሚሰጠው ትኩረት እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡ በተጓዳኝም ታማሚውም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ሳቢያ ወደ ጤና ተቋም መሔድ ላይፈልግ ይችላል፡፡ እነዚህም፤ በመጀመሪያ የታመመው በሽታ ምልክት ከኮቪድ-19 ጋር ተመሳሳይነት ካለው (ምሳሌ ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ ወዘተ.) መድልዎና መገለልን በመፍራት የኮቪድ-19 ምርመራ ማድረግ ባለመፈለግ ወደ ጤና ተቋም ላይሄድ ይችላል፡፡ በሁለተኛነት በሽታው የቆየ በሽታና ለኮቪድ-19 የሚያጋልጥ ወይም ደግሞ የኮቪድ-19 በሽታ የሚጠናበት ከሆነ (ምሳሌ፡ የስኳር በሽታ፣ የመተንፈሻ አካል በሽታ፣ በዕድሜ መግፋት፣ ወዘተ.) ወደ ጤና ተቋም መሔድ አይፈልግም፡፡

የመድሀኒትና የድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች (ለምሳሌ የሰውሰራሽ መተንፈሻ አካል) ዕጥረትና የጥራት ጉድለት ሌላው አሳሳቢ ተግዳሮት ነው፡፡

የነፍስ ወከፍ የተላላፊ በሽታ መከላከያ ቁሳቁሶች (Personal Protective Equipment) ዕጥረት ሌላው ተግዳሮት ሆኖ ታይቷል፡፡

ይህ ተግዳሮት የጤና ባለሙያዎችን ዕጥረት ስለሚያባብስ የጤና ግልጋሎት አሰጣጡን የበለጠ ያዳክመዋል።

## 6 የወደፊት አቅጣጫ ጠቋሚ ምክረ-ኃሳብ

በጠቅላላው የወደፊት አቅጣጫ የሚሆነው የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል፣ የታመሙትን ለማከምና ለመንከባከብ ስንል የተገበርናቸው ክንውኖች በጤና ተቋማት እና በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያመጡትን ከላይ የተዘረዘሩና ሌሎችም አዎንታዊ ተፅዕኖች የበለጠ ማጠናከርና ማጎልበት፤ እንዲሁም ተግዳሮቶች ናቸው ብለን ለዘረዘርናቸው መፍትሔ ይሆናሉ ብለን የምንገምታቸውን በሚገባ በመተግበር ተግዳሮቶቻችንን ማስወገድ ወይም ደግሞ ማቃለል ነው። ለምሳሌ ከሀገር ውጪ ያሉ ኢትዮጵያዊያንን ዕውቀት ለኮቪድ-19 ምላሽ ከመጠቀም የተማርነውን ለሌሎች በሽታዎች ምላሽም መጠቀም የምንችልበትን መንገድ ማመቻቸት የሠለጠነ የጤና ባለሙያ ችግራችንን ይቀርፍልናል። በሌላ በኩል ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተዘረዘሩትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ዋነኛው መንገድ እየተሰጠ ያለውን የጤና ትምህርት የበለጠ ማጠናከር፣ ለሕብረተሰቡ ሳያቋርጡ መስጠትና የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማጠናከር ነው።

እንደሚታወቀው ከላይም ለማስረዳት እንደተሞከረው፣ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተወሰዱት የሰዎች እንቅስቃሴን መገደብ፣ መሰባሰብን ማቆምና የመሳሰሉት የመከላከያ መንገዶች ወረርሽኙን ለመከላከል የጎላ አስተዋፅዖ ማድረጋቸው ቢታወቅም፤ ይህንን ውጤት ለማምጣት ግን ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ የኢኮኖሚ ተፅዕኖ፣ የአእምሮ ጤና መታወክንና ኮቪድ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚመጡ የበሽተኝነትና የሞት (morbidity and mortality) መጠን መጨመር የተጓዳኝ ጉዳቶች ናቸው። ስለሆነም የኮቪድ መከላከልና መቆጣጠር የወደፊት አቅጣጫ በአነስተኛ የተጓዳኝ ጉዳቶች መጠን በሽታውን መከላከልና መቆጣጠር መቻል መሆን ይኖርበታል። ‹‹ከፍተኛ

ትክክለኛነት አካላዊ ርቀትን መጠበቅ›› (“precision social distancing”) - አካባቢን፣ ባህልን፣ ፖለቲካን ኢኮኖሚንና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ግምት ውስጥ ያስገባ አካላዊ ርቀት - ይህንን ሚዛን መጠበቅና በሽታውን ተከላክሎ የሚደርሱትን ተጓዳኝ ጉዳቶች የሚቀንስ መንገድ (tool) ነው ተብሎ ይታመናል። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ረዘም ላለ ጊዜ አብሮን ሲኖር ሕብረተሰቡ መሰልቸቱና የመከላከያ መንገዱን ችላ ማለቱ የማይቀር ነው። ስለሆነም መንግስትና የጤና ሚኒስቴር ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጉ አገልግሎት መሰጫ ተቋማትን (ትምህርት ቤት፣ የዕምነት ቦታዎችን፣ የመዝናኛ ቦታዎችን ወዘተ) ‹‹ጥብቅ ትክክለኛ አካላዊ ርቀትን በመጠበቅ›› መክፈት ብልህነት ነው ብዬ አምናለሁ። ይህንን አለማድረግ ግን ሰው በራሱ ተቋማቱን፣ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳይወስድ ይከፍተውና ወረርሽኙን ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን ያደርገዋል።

ሌላው የወደፊት አቅጣጫ የኮቪድ-19ኙን ምላሽ በጤና ሚኒስቴር ላይ ብቻ አለመተውና ሌሎች ሴክተሮችም ከቃላት የዘለለ እንቅስቃሴ በማድረግ በምላሹ በሰፊው መሳተፍ ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ኮቪድ-19 የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ ወዘተ ችግር ስለሆነ ነው። ስለሆነም ማንኛውም መስሪያ ቤት በውስጡ የኮቪድ-19 መከላከያ፣ መቆጣጠሪያና ማከሚያ ስራን በፕሮግራሙ ውስጥ ማካተት እንዲኖርበት መመሪያ መስጠትና መተግበሪያ መንገዱንም ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

# የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ፦ ከዘገምተኛ ስርጭት እስከ አሳሳቢ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ምልከታ

አሉላ ፓንክረስት

## 1 መግቢያ

የኮሮና (ኮቪድ 19) ወረርሽኝ በቻይናዋ ውሀን ከተማ ሁቤ ግዛት እ.ኤ.አ ህዳር ወር 2021 መከሰቱ ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ በፍጥነት ወደ ሌሎች የቻይና ግዛቶችና የዓለም ሀገራት በመሰራጨት የዓለማችን ቁጥር አንድ የጤና ስጋት ሆኗል። ይህንን ወረርሽኝ ለመግታትና ለበሽታው ክትባት ለማግኘት በርካታ የዓለም ሀገራት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም በአጭር ጊዜ መፍትሔ የሚገኝለት የጤና ችግር አልሆነም። የበሽታውም ባህሪ ንፅህናን የማይወድ፤ እንዲሁም አካላዊ ቅርርብን የማይፈልግ በመሆኑ በተለይም በኢኮኖሚያቸው ደካማ በሆኑና አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በድህነት በሚኖርበት፤ ማህበራዊ መስተጋብሩም ከፍተኛ በሆነባቸው ሀገራት የወረርሽኙ ጫና ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል የዓለም ጤና ድርጅትም ሆነ ሌሎች የጥናት ማዕከላት የወረርሽኙ ስርጭት እየተስፋፋ መምጣት በጀመረበት ወቅት ያስቀመጡት ስጋት ነበር። ወረርሽኙ ከጤና ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና በማስከተል ላይ ይገኛል። ሀገራት ድንበሮቻቸውን ሲዘጉ፤ የንግድ እንቅስቃሴዎችንም ሲገደቡ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች ከስራ ለመፈናቀል ተገደዋል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የኮቪድ 19 ቫይረስ ተጠቂ የተገኘው መጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመንግስትም ሆነ በህብረተሰቡ የበሽታውን ወረርሽኝ ለመግታት በተጠኑና በተቀናጁ ሁኔታዎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርስቲዎችን መዝጋት፣ የትራስፖርት

አገልግሎት ላይ የሰዎችን መጨናነቅ ለመቀነስ የተጣሉ ገደቦች፣ በሚዲያዎች ህብረተሰቡ ስለ በሽታው ግንዛቤ እንዲያገኝ በስፋት ትምህርት መስጠት እና በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር ዘርፈ ብዙ የማስተማር እና ንጽህናን የማስጠበቅ እንቅስቃሴዎች ይገኙበታል። እነዚህ ጥረቶች የወረርሽኙን ስርጭት በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስለነበራቸው ሊበረታቱና ሊደነቁ የሚገቡ ተግባራት ናቸው።

ይህ ምልከታ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ቢከሰትም የስርጭቱ ሂደት በሌሎች የዓለም ሀገራት ከነበረው ዘገምተኛ ለምን ሆነ? መንግስት ወረርሽኙን ተከትሎ እየሰጠ ያለው ምላሽ ምን ይመስላል? ወረርሽኙ በተጎዱና በተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለው ጫና ምን ይመስላል? የሚሉትንና የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ላይ ስናተኩር ሌሎች መርሳት የሌለባቸውን ችግሮች እንድናስብ ለማመላከት ተብሎ የተዘጋጀ ነው።

## 2 የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ያለው የስርጭት ሂደት በአውሮፓ ሀገራት እንዲሁም በአሜሪካ ካለው የስርጭት ሂደት ጋር ሲታይ ዘገምተኛ ነው። ሁኔታው ተስፋ የሚሰጥ ቢሆንም አሳሳቢ አይደለም ማለት ግን አይደለም። የበሽታው ባህሪ እና የሚያስከትለው የጤና ጫና ተቀያያሪ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ይፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ ኮቪድ-19ን በተመለከተ በርካታ መረጃዎች ቢኖሩም አንዳንድ መረጃዎች በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ የተሳሳቱና የሀሰት መረጃዎች በመኖራቸው ህብረተሰቡ መረጃውን የሚያገኝበት ምንጭ በጥንቃቄ መምረጥ ይጠበቅበታል።

ወረርሽኙ ኢትዮጵያ እንደገባ ስርጭቱን በተመለከተ የተለያዩ ግምቶች ተሰጥተው ነበር። እንደ የኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ተቋም ትንበያ ወረርሽኙ በገባ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ (ማለትም እ.ኤ.አ በሚያዚያ

ወር 2019 ዓ.ም.) የወረርሽኙ ተጠቂዎች ቁጥር አንድ መቶ ሺህ (100,000) ሰው እንደሚሆን፤ በግንቦት ወር አንድ ነጥብ ዘጠኝ (1.9) ሚሊዮን እንደሚደርስና ወረርሽኙ በአጠቃላይ ከአስራ አምስት እስከ ሰላሳ ዘጠኝ (15-39) ሚልዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን እንደሚያጠቃ ተተንብዮ ነበር። ይህ ትንበያ በሌሎች ሀገሮች በነበረው ልምድ ላይ ተመርኩዞ የተተነበየ ነበር። ይህ ከፍተኛ የትንበያ ስጋት መንግስት ህብረተሰቡና ግለሰቦች በተቀናጀ መልኩ ለወረርሽኙ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ አስገድዷል።

የወረርሽኙ ሂደት በዚህ ፍጥነት ይሆናል ተብሎ ቢገመትም በአንዳንዶቻችን ዘንድ የወረርሽኙ ስርጭት የሚፈራውን ያህል ላይሆን ይችላል የሚል ግምትም ነበር። በሚያዚያ 2012 ኢትዮጵያ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከአፍሪካ ሰባተኛ ደረጃ ነበረች። በጊዜው እንደ ኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥራቸው ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሆኑት ግብፅና ናይጄሪያ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ደረጃ ቢገኙም በነዚህ አገሮች የተመረመሩ ሰዎች ቁጥር ከኢትዮጵያ በእጅጉ ያንስ ነበር። ከአንድ ሚሊዮን ሰዎች ስንት ሰው ተይዟል? ስንትስ ሞቷል? የሚለውን መረጃ ሲታይ በኢትዮጵያ ያለው መረጃ ከሌሎች ሀገራት ሲታይ የተሻለ ነው። ይህ የሚያበረታታ ቢሆንም የበሽታው ስርጭት እንደተፈራው ሊሆን እንደማይችል እገምታለሁ። ሆኖም ግን ይህ ከግምት ያለፈ አይደለም። የምርመራው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በወረርሽኙ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ነው።

**ሠንጠረዥ 1፡** በአፍሪካ የኮቪድ-19 ስርጭት በአገራት መስከረም 20 ቀን 2013 (September 30, 2020)

| # | አገር | ጠቅላላ ታማሚ | አዲስ ታማሚ | ጠቅላላ የሞት መጠን | አዲስ የሞት መጠን | ጠቅላላ ያገገሙ | አሁን ያሉ ታማሚዎች | ፅኑ ታማሚዎች | ጠቅላላ ታማሚ/ ከ1 ሚ. ሕዝብ | ጠቅላላ ሞት/ ከ1 ሚ. ሕዝብ | ጠቅላላ ምርመራ | ምርመራ/ ከ1 ሚ. ሕዝብ | ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አፍሪካ | 1,482,358 | +1,424 | 35,752 | +23 | 1,227,046 | 219,560 | 1,620 | | | | | |
| 1. | ደቡብ አፍሪካ | 672,572 | | 16,667 | | 606,520 | 49,385 | 539 | 11,305 | 280 | 4,164,491 | 70,001 | 59,491,884 |
| 2. | ሞሮኮ | 121,183 | | 2,125 | | 100,253 | 18,778 | 440 | 3,274 | 58 | 2,598,486 | 70,195 | 37,017,890 |
| 3. | ግብፅ | 103,079 | | 5,914 | | 96,094 | 1,071 | 41 | 1,003 | 58 | 135,000 | 1,313 | 102,801,727 |
| 4. | ኢትዮጵያ | 74,584 | | 1,191 | | 30,952 | 42,441 | 271 | 645 | 10 | 1,266,213 | 10,949 | 115,645,151 |
| 5. | ናይጀሪያ | 58,647 | | 1,111 | | 49,937 | 7,599 | 7 | 283 | 5 | 509,555 | 2,457 | 207,362,394 |
| 6. | አልጀሪያ | 51,368 | | 1,726 | | 36,063 | 13,579 | 22 | 1,166 | 39 | | | 44,043,060 |
| 7. | ጋና | 46,482 | | 301 | | 45,651 | 530 | 6 | 1,488 | 10 | 479,931 | 15,368 | 31,229,374 |

**ምንጭ፡- ወርልዶሜትር የኮቪድ መረጃ ድረገጽ** https://www.worldometers.info/coronavirus. (Accesses on September 30, 2020)

## 3 በኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት በተፈራው ፍጥነት ያልሆነው ለምንድነው?

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስርጭት በአውሮፓና በአሜሪካ ከታየው የወረርሽኝ ስርጭት አንፃር ዘገምተኛ የሆነበትን ሁኔታ ለመረዳት ከዚህ በታች የተጠቀሱት ምክንያቶች በመላ-ምትነት ይቀርባሉ።

### 3.1 አካባቢያዊ ሁኔታዎች፤ አየር ንብረትና የከፍታ መጠን

አካባቢያዊ ሁኔታዎች ስንል የአየር ንብረትን፣ የሙቀትና ዝናብ ሁኔታ እንዲሁም ከባህር ወለል በላይ ያለ ከፍታን ለማመላከት ነው። በአውሮፓ ሀገራትና በአሜሪካ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በስፋት የተሰራጨው በክረምት ወቅት ነበር። ይህ ወቅት በነዚህ ሀገራት ወትሮም ዋና የጉንፋን እና ጉንፋን መሰል በሽታዎች ስርጭት ወቅት ነው። የበጋ ወቅት በነበራቸው ዓለም ሀገራትና ቆላማ ቦታዎች ላይ የበሽታው ስርጭት ውስን ነበር። ይህም የኮቪድ-19 ቫይረስ የአየር ሁኔታው ቀዝቃዛ በሆነበት ጊዜ ለመስፋፋት አመቺ እንደሚሆንለት አመላካች ነው።

በኢትዮጵያ በሚያዚያ እና በግንቦት 2012 ወራት የቫይረሱ የስርጭት ሁኔታ ውስን የነበረ ቢሆንም የክረምት ወራት መግባትን ተከትሎ ከሰኔ ጀምሮ ባሉት ወራት የቫይረሱ ተጠቂ ሰዎች ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛል። ክረምት መግባቱን ተከትሎ የቫይረሱ ስርጭት መጨመር የሚጠበቅ ቢሆንም፤ የአጨማመሩ ፍጥነት ግን በተፈራው መጠን አልሆነም። ይህ የሆነበትን ምክንያት ለማስረዳት በጥናት የተደገፈ መረጃ ሊኖር ቢገባም፤ በሀገሪቱ በስፋት ሲከናወን የነበረው የፅዳት ዘመቻ፤ እንዲሁም መንግስት በወሰደው የመከላከል ዕርምጃም ሆነ በክረምቱ ምክንያት የሰዎች እንቅስቃሴ መገደቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው መገመት ይቻላል።

ከባህር ወለል በላይ ያለ ከፍታን በተመለከተ አንዳንዶች የቫይረሱ ስርጭት ከፍ ባሉ የደጋ ቦታዎች ላይ ይቀንሳል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የጸሀይ ሙቀት በሚያገኙት ቆላማ ቦታዎች ላይ ስርጭቱ ውስን ነው ይላሉ። ለዚህም ከፍተኛ የሆነ የፀሀይ ብርሀን በሚኖርበት ጊዜ ከፀሐይ የሚመጣው የአልትራቫዩሌት ጨረሮች ቫይረሱን ይገድለዋል የሚል መላ ምት ያስቀምጣሉ።

በኢትዮጵያ ከቅርብ ቀናት ወዲህ በሶማሌ ክልል በኩል የቫይረሱ ስርጭት እንደጨመረ መጥቷል። ይህም የሆነው በሶማሌ ክልል በኩል ድንበር ተሻጋሪ እንቅስቃሴ በመኖሩ እንደሆነ ተገልጿል።

## 3.2 ከፍተኛ የሆነ ወጣት ህብረተሰብ ክፍል መኖር

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቫይረሱ የሚያስከትለው የህመም መጠን ከወጣቶች ይልቅ በዕድሜ በገፉት ላይ የጠነከረ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ማለት ወጣቶች የኮቪድ-19 ቫይረስን የበለጠ እንደሚቋቋሙትና በዚህም ምክንያት በበሽታው ምክንያት የሚሞቱ ወጣቶችን ቁጥር አናሳ መሆኑን ነው።

በኢትዮጵያም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ወጣት ነው። ይኸውም ከጠቅላላው የሀገሪቱ ህዝብ አምሳ ስድስት ከመቶ (56%) ያህሉ ከሠላሳ ዓመት በታች ሲሆን አርባ ሶስት በመቶ (43%) የሚሆኑት ከሀያዎቹ ዕድሜ ክፍል የሚገኙ ናቸው። በኮቪድ-19 ቫይረስ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፉ ሰዎች መረጃ ሲታይም ከሰባ አራት በመቶ (74%) በላይ የሚሆኑት ሟቾች ከኃምሳ ዓመት በላይ ሲሆኑ፤ ከአርባ ሦስት (43%) በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከስልሳ ዓመት በላይ ናቸው። ይህ ማለት በቫይረሱ ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ህይወታቸውን የሚያጡት ዕድሜአቸው ኃምሳና ከዚያ በላይ የሆኑት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

## 3.3 ድህነት

የኮቪድ-19 ቫይረስ ወረርሽኝ በፍጥነት የተስፋፋው እንደ ጣሊያን ባሉ የጤና አገልግሎታቸው ከፍተኛ በሆነባቸው ሀገራት ነው። ይህም የሆነበት አንዱ ምክንያት የህክምና አገልግሎት በእነዚህ ሀገራት በስፋት ስለሚገኝ ሰዎች ወደ ጤና ተቋማት የመመላለሳቸው መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ነው ተብሎ ይገመታል። በዚህም ምክንያት በርካታ ሰዎች በተለያየ ምክንያት የጤና ተቋማትን በመጎብኘታቸው የቫይረሱ ስርጭት በተለይ በሆስፒታሎች አካባቢ ከፍተኛ ሊሆን ችሏል። በውጤቱም በየሆስፒታሎች የነበሩ ሀኪሞችና የሌላ በሽታ ታማሚዎች በከፍተኛ ደረጃ ለኮቪድ-19 ቫይረስ በመጋለጣቸው የከፋ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በተቃራኒው በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ያለው ዕድል ውስን መሆኑ ጥሩ ባይሆንም፤ የቫይረሱን ስርጭት ከመገደብ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል ተብሎ ይታሰባል።

በሌላ በኩል ከተለያዩ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዜጎች አየር ማረፊያ እንደደረሱ ምርመራ እንዲያደርጉ መደረጉ፤ ከህብረተሰቡም ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት በተለያዩ ሆቴሎችና ለይቶ ማቆያ ማዕከላት በማቋቋም እንዲቆዩ መደረጉ የበሽታውን ስርጭት ከመግታት አንፃር ጠቃሚ ዕርምጃ ነበር። ምንም እንኳ አንዳንድ መረጃዎች እነዚህ ማዕከላት ቫይረሱን በማስፋፋት ረገድ ሚና እንደነበራቸው ቢገልጹም።

በጤና ሚኒስቴርና በህብረተሰብ ጤና ተቋም ሲገለፅ እንደነበረው ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የጤና ስርዓቱ በኮቪድ-19 ህምምተኞች ተጥለቅልቆ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንዳይፈጠር ህብረተሰቡ በሽታውን ለመከላከል አስፈላጊውን ሁሉ የጥንቃቄ ተግባራት ያለመሰላቸት ሊፈፅም ይገባል።

## 3.4 ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር ዝቅተኛ መሆን

ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ጋር ያላት ትስስር በአንፃራዊነት ውስን ነው:: ይህም መሆኑ የቫይረሱን ስርጭት ከመቀነስ አንፃር ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል ተብሎ ይታመናል:: በተቃራኒው እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ ዓለም አቀፍ ትስስራቸው ጠንካራ የሆኑ ሀገራት የወረርሽኙ ስርጭት ከፍተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ::

በኢትዮጵያ መጠነኛ የሆነ ድንበር አቋራጭ የባቡር (በአራት ቀን አንዴ) እና ሌሎች ትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች ከመኖራቸው በላይ ከመጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ዓለም አቀፍ ድንበሮች መዘጋታቸው የወረርሽኙን ስርጭት በመገደብ ረገድ ጠቃሚ ዕርምጃ ነበር:: በቦሌ አለም አቀፍ ማረፊያም የሙቀት ልኬት ቀደም ብሎ መጀመሩ እንዲሁም ከመጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሀያ አንድ (21) አገራት የሚደረጉ ጉዞዎችን መቋረጣቸው ቫይረሱ ወደ ሀገር እንዳይገባ፤ የሚገባውንም መጠን ለመቀነስ የተወሰዱ አስፈላጊና ጠቃሚ ዕርምጃዎች ነበሩ:: እነዚህ ሁሉ የቫይረሱን ስርጭት ከመግታትና ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ቢሆንም ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የሚደረግ የከባድ መኪኖች እንቅስቃሴ፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች ድንበር ተሻጋሪ እንቅስቃሴ፤ እንዲሁም ድንበር አካባቢ የሚደረጉ ህገ-ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድና የጫት ንግድ እንቅስቃሴዎች ለቫይረሱ ስርጭት ስጋት በመሆናቸው ትኩረት ሊቸራቸው ይገባል::

በአየር ማረፊያም ይከናወን የነበረው የመለየት ሂደት እና ክትትል የቫይረሱን የማህበረሰብ ውስጥ የስርጭት ደረጃ ለመቀነስና የተፈራውን ያህል ጉዳት እንዳያደርስ ረድቷል:: በመጀመሪያ የቫይረሱ ዋነኛ ስጋት የነበሩት የውጭ ሀገር ዜጎች የነበሩ ቢሆንም በሂደት ከውጪ ተመላሽ ኢትዮጵያኖች በተለይም ከአረብ አገራት የሚመለሱ ዜጎች እንደዋና

የስጋት ምንጭ ታይተው ነበር። ከሚያዝያ እስከ ሀምሌ 2012 ባሉት አራት ወራት ከሀያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ በላይ ዜጎች በግዳጅ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተደርጓል። እነዚህ ዜጎች እንደ ቫይረሱ የስጋት ምንጭ ቢታዩም መንግስት አስፈላጊውን ጥንቃቄና ምርመራ በማድረግ፤ የውሸባ (quarantine) ጊዜያቸውን እስኪጨርሱ በለይቶ ማቆያ በማቆየት ከቫይረሱ ነፃ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ከህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረጉ የቫይረሱን ስርጭት በከፍተኛ ሁኔታ ገድቦታል።

## 3.5 የዕድል ጉዳይ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ አፍሪካና ኢትዮጵያ የደረሰው በኤስያ፤ በአውሮፓና በአሜሪካ ከተስፋፋና ጉዳት ካደረሰ በኋላ ነበር። ይህ መሆኑ ለኢትዮጵያ ሆነ ሌሎች አፍሪካ ሀገራት የመዘጋጃ፤ የመማሪያ እና የመከላከያ ጊዜ ሰጥቷቸዋል። በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የተፈራውን ያህል ጉዳት እንዳያደርስ መከላከል ተችሏል ተብሎ ይታመናል።

በሌላ በኩል ቫይረሱ ኢትዮጵያ ሲገባ ቱሪስቶች ኢትዮጵያን የሚጎበኙበት ወቅት እንዲሁም ዲያስፖራዎች ወደ ሀገራቸው የሚመጡበት ወቅት አልፎ መሆኑ እንደ ዕድል ማየት ይቻላል። ቱሪስቶችን በተመለከተ ከወቅቱም ባሻገር በሀገሪቱ በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በዓመቱ የቱሪስቶች ፍሰት ቀንሶ ነበር።

## 3.6 የህክምና ማብራሪያዎች

በኢትዮጵያ ያለውን ዝቅተኛ የሆነ የኮቪድ-19 የሞት መጠን እና ከፍተኛ የሆነ የምልክት አልባ ተጠቂዎች ቁጥር በተመለከተ የህክምና ማብራሪያ መኖሩ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ማብራሪያዎች ከሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች መካከል ቫይረሱ በተለያየ አካባቢ የተለያየ

ምላሽ አለው ወይ? አንዳንዶች እንደሚሉት በህፃንነት የሚሰጠው የቢሲጂ ክትባት ቫይረሱን ለመቋቋም ይረዳል ወይ? ቫይረሱ የተለያየ የዝርያ አይነት (strain) አለው ወይ? የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ቀደም ብሎ ብዙ ሰዎች በጥር ወር አካባቢ ታምመው የነበረው ኮቪድ መሰል ባህሪ ያለው ጉንፋን በሽታ ኮቪድ ነው ወይስ ኮቪድ መሰል ነው? የዘር ጉዳይ (Race/DNA) ኮቪድ-19ን ለመቋቋም አስተዋፅኦ አለው ወይ? እና ሰውነት በሽታ የመቋቋም አቅም ከቫይረሱ የህመም ደረጃ ጋር ግንኙነት አለው ወይ የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሊያገኙ ይገባል።

የሀገራችን ኮቪድ-19ኝን የመመርመር አቅም እየጨመረ ቢመጣም የተመረመረው ቁጥር ከጠቅላላ የሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው። የመመርመር አቅማችን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። ለምሳሌም እ.ኤ.አ በኤፕሪል (ሚያዚያ) 2020 መጨረሻ በቀን የመመርመር አቅማችን አንድ ሺህ ሰው የነበረ ሲሆን፤ ይህ አኃዝ በሜይ (ግንቦት) መጨረሻ ወደ አምስት ሺህ አድጓል። ሀምሌ (ጁላይ) 2020 መጨረሻ ላይ ደግሞ ወደ ስምንት ሺህ ያሻቀበ ሲሆን፤ በኦገስት (ነሀሴ) ደግሞ አስራ አራት ሺህ ደርሷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የምርመራ ማዕከላትም ብዛት ጨምሮ ኃምሳ የደረሰ ሲሆን፣ ሁሉም ክልሎች ቢያንስ አንድ የመመርመሪያ ማዕከል አላቸው። በነሀሴ ወር የተደረገው የምርመራ ዘመቻም በሁለት ሳምንት ውስጥ ሁለት መቶ ሺህ ያህል ምርመራዎችን ለማድረግ ታቅዷል። ይህ ከፍተኛ ዕድገት ቢሆንም በሀገሪቱ ካለው ከፍተኛ የህዝብ ብዛት አንፃር ሲታይ የምርመራው መጠን አሁንም ዝቅተኛ ነው። በመረጃው መሠረት እየተመረመሩ ያሉት ከሚሊዮን ሰዎች መካከል ሁለት መቶ ሰባ ሁለቱ ብቻ ናቸው። በሌላ በኩል እየተመረመሩ ያሉት በአብዛኛው ስጋት ያለባቸው አካባቢዎችና ይበልጥ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች (ለምሳሌ የህክምና ባለሙያዎች፣ ንክኪ የነበራቸው ግለሰቦች) በመሆናቸውና በአቦሰጥ (random) የሚደረግ ምርመራ ባለመሆኑ

የቫይረሱን ትክክለኛ የማህበረሰብ ስርጭት ለመገመት በቂ እና ትክክለኛ መረጃ አለ ለማለት ያስቸግራል። እንደ ለንደን ኤምፔርያል ኮሌጅ ሞዴሊንግ በአብዛኛው ሀገራት ትክክለኛው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መጠን ከሚገባው በላይ የተስፋፋ ነው።

## 3.7 ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች

የኮሮና ቫይረስ አፍሪካን አህጉር በመታበት ወቅት ቫይረሱ የሚሰራጭበትን መንገድ በተመለከተ በቂ የሆነ ግንዛቤ ተፈጥሮ ነበር። በዚህም ምክንያት የአፍሪካ ሀገራት ቅድመ ጥንቃቄ ላይ በማተኮራቸው የወረርሽኙን አስከፊ ገፅታ ከማየት ተርፈዋል ለማለት ይቻላል። የመከላከያ ዘዴዎችን በተመለከተ መንግስት ከህብረተሰብና ግለሰቦች ጋር በመሆን ሰፊ ተግባራትን አከናውኗል። ከእነዚህም ውስጥ በአየር ማረፊያ ሲደረግ የቆየው የሙቀት ልየታ፣ ተጠርጣሪዎችን የመለየትና አስገዳጅ ለይቶ ማቆየት፣ የንክኪ ልየታና ምርመራ፣ ቤት ለቤት ሙቀት ልየታና ምርመራ፣ ስብሰባዎችን መከልከል፣ ት/ቤቶችንና ዩኒቨርስቲዎችን መዝጋት፣ ትልልቅ መሰባሰቦችን መከልከል፣ የፊት ጭንብል የማድረግ ግዳጅ፣ የስልክ መልእክቶች፣ የአካላዊ መራራቅ ትምህርቶችና ግዳጆች፣ ከሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ምንጮች ሀብት ማሰባሰብ፣ የማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ሰፊ የሆነ የግንዛቤ መፍጠሪያ ትምህርቶች፣ በሁሉም የግልና የህዝብ ትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ንፅህና አጠባበቅ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የተሰሩ ስራዎችና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሰፊው እንዳያጠቃት ረድተዋታል።

# 4 ማህበራዊ ዋስትናን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች

በሀገር አቀፍ ደረጃ ማህበራዊ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። ከነዚህም መካከል ሰራተኛ ማባረርና የኪራይ

መጠንን መጨመርን መከልከል፣ ሴፍቲ ኔት (safety net) ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከመከላከል አንፃር ጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፤ በክልል ደረጃም ከምግብ ዋስትና፤ ከአገልግሎቶች እና ከማህበራዊ ዋስትና ጋር በተያያዘ በርካታ አበረታች እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ወጥ ያልሆኑና እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች የተወሰዱ ናቸው። እነዚህ ሂደቶች አበረታች ቢሆኑም ከመከላከል አልፎ የተቸገሩትን ከመርዳት አንፃር ተጨማሪ ጥረቶች ሊደረጉ ይገባል።

## 5 የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የተደረጉ ጥረቶችና ቀጣይነታቸው

የቫይረሱን ስርጭት የመግታት እንዲሁም የንክኪ ልየታና ምርመራ የቫይረሱ ስርጭት በማህበረሰቡ ውስጥ እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ አዳጋች ይሆናል። የቫይረሱን ስርጭት ስንመለከት በአንድ ወር ውስጥ በአስር በመቶ፤ በሁለት ወር አስራ ስድስት በመቶ፤ በሦስት ወር ስልሳ ሁለት በመቶ እያለ እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ይህንን ሁሉ ንክኪ የመለየትና የመመርመር ሂደት በጊዜ እየከበደ መሄዱ አይቀሬ ነው። የፊት ጭንብል ማድረግ ለቫይረሱ የመጋለጥ ዕድልን በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀንስ ቢሆንም በጊዜ ሂደት የቫይረሱ በስፋት መሰራጨት የማይቀር እውነታ ነው። የክረምቱ መግባትና እንዲሁም በሰኔ ወር መጨረሻ የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋትን ተከትሎ በርካቶች የፊት ጭንብል ሳያደርጉ መሰባሰባቸው በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቫይረሱ ስርጭት በከፍተኛ ሁኔታ ለመጨመሩ እንደምክንያት ሊወሰድ ይችላል። እዚህ ላይ ዋና አሳሳቢ ጥያቄ ሊሆን የሚገባው የሥርጭቱ ፍጥነት በምን ያህል ይቀጥላል? የጤናውስ ስርዓት ምን ያህል የመቋቋም ብቃት አለው? የሚሉት ናቸው።

# 6 የወረርሽኙ ጫና ለበሽታው በተዳረጉ፣ ይበልጥ በተጠቁ ዘርፎች እና በተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች

## 6.1 ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል።የዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ተቋምና የዓለም ባንክ በቅርብ በስልክ አማካኝነት ያደረጉት የዳሰሳ ጥናት እንደሚያመለክተው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦች ገቢያቸውን በወረርሽኙ ምክንያት አጥተዋል። የተባበሩት መንግስታት ሪፖርትም እንደሚያመለክተው የውጭ ንግድ ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ በመቶ፤ ከውጪ ወደ ሀገር የሚላከው ገንዘብ ከአስር እስከ አስራ አምስት በመቶ የቀነሰ ሲሆን፤ ከአስር እስከ አስራ አምስት በመቶ የሚሆኑ ስራዎች በመዘጋታቸው ከሦስት እስከ አራት ሚሊዮን ሰዎች ስራ አጥ ሆነዋል።

## 6.2 በፆታ ረገድ

እስካሁን ባለው መረጃ አብዛኛው በኮቪድ-19 ቫይረስ የተጠቁት ወንዶች ናቸው። ይኸውም ከጠቅላላው ስልሳ አንድ በመቶ የሚሆነውን ይይዛል። የመተዳደሪያ ስራን በማጣት ረገድ ግን በአብዛኛው የተጎዱት ሴቶች እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ እንዲሁም መደበኛ ባልሆኑ አነስተኛ የንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ በርካታ ሴቶች የገበያ ቦታቸው መዘጋቱን ተከትሎ ስራቸውን ለማጣት ተገድደዋል። ከገጠር ተሰደው በከተማና በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰሩ ሴቶችም ይህ ስጋት ተደንቅሮባቸዋል።

ሴቶችን በአብዛኛው የሚገኙባቸው የስራ ዘርፎች (ለምሳሌ ጤና ኤክስቴሽን፣ ነርስ፣ አበባ እርሻ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ) የሚሰሩ ሴቶች በስራቸው ባህሪ ምክንያት ለቫይረሱ የበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳን በመረጃ ተደግፎ ሊታይ ቢገባም ሴቶችና ልጃገረዶች ውሀ ለመቅዳት የሚፈጅባቸው ጊዜ

እንዲሁም የታመሙትን በማስታመም የሚያጠፉት ጊዜ የመጨመር ስጋቶች አሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ወረርሽኙን ተከትሎ የትምህርት ቤቶች መዘጋትንና የስነ-ተዋልዶና የጤና ኤክስቴሽን ድጋፎች መቀነስን ተከትሎ የፆታ ጥቃቶችና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ሊጨምሩ የሚችሉ ስጋቶች ናቸው።

## 6.3 ህፃናትና ታዳጊዎች

በወረርሽኙ ምክንያት ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች በመዘጋታቸው በትምህርት ቤት ይሰጡ የነበሩ የምግብ ፕሮግራሞችን እንዲቋረጡ ሆነዋል። ይህ ደግሞ በተለይም ከደሀው የህብረተሰብ ክፍል በወጡ ህፃናትና ወጣቶች ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል። ህጻናትና ታዳጊዎች ቤት መዋላቸውን ተከትሎ የጥቃት ሰለባ እየሆኑ መምጣታቸውን አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ። በታዳጊ ወጣቶችና አዋቂዎች ላይም አዕምሯዊ ችግር እና ጭንቀት እየተስተዋለ እንደሆነ አንዳንዶች ያመለክታሉ። ይህ ችግር በገጠር በከተማ፣ በተለያዩ እድሜ ክልል፣በተለያዩ የስራ ዘርፍ ላይ በሚገኙ ሰዎች ላይ በተለያዩ ደረጃዎች እየተስተዋለ ይገኛል።

እነዚህ ችግሮች የተሳሰሩና የተቆላለፉ በመሆናቸው የችግሩን ጥልቀት እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ስንመረምር ይህንን ውስብስብነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል።

# 7 የያንግ ላይቭስ የስልክ ዳሰሳ ጥናት ውጤት

ያንግ ላይቭስ ኢትዮጵያ በሐምሌ ወር 2012 በስልክ አማካኝነት የዳሰሳ ጥናት አድርጎ ነበር። ጥናቱ በዋናኝነት ወጣቶች ስለ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያላቸውን ግንዛቤ ለመረዳትና ከቫይረሱ ጋር በተያያዘ ያላቸውን ልምድ መረዳትን ዓላማ ያደረገ ነበር። በተገኘው መረጃ መሠረት አብዛኛዎቹ ወጣቶች ቢያንስ ሁለቱን ወይም ሦስቱን

የህመሙን ምልክቶች ያውቃሉ፡፡ የቫይረሱን ስርጭትም ለመግታት አካላዊ ርቀት ያለውን ጠቀሜታም ተረድተዋል፡፡ ከተማ አካባቢ በሚኖሩና የተሻለ የኢንተርኔት ግንኙነት ማግኘት በቻሉ ወጣቶች መካከል የግንዛቤ ደረጃቸው ከሌሎቹ የተሻለ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ግማሽ ያህሉ ወጣቶች አራቱን የመከላከያ ዘዴዎች (መቆየት፤ መታጠብ፤ መሸፈን እና መራቅ) በሚገባ ይተገብራሉ፡፡ በጥናቱ ከተሳተፉት ወጣቶች በጣም ጥቂቱ ቤት የተቀመጡ ሲሆን አብዛኞቹ መሠረታዊ ፍላታቸውን ለሟሟላትና ዕለታዊ ገቢ ለማግኘት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ከቤት ውጪ የሚውሉት አብዛኛዎቹ ወንዶች በመሆናቸው ለወረርሽኙ ወንዶች ይበልጥ ተጋላጭ ይሆናሉ የሚል ግምት አሳድሯል፡፡ ከመላሾቹ ውስጥ ከአንድ በመቶ ያነሱት ከቤተሰባቸው በቫይረሱ የተያዘ ሰው አለ ብለው ያስባሉ፡፡

መደበኛ ባልሆነ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ወጣቶች ለቫይረሱ የበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በወጣት ወንዶች በተለይም ከተማ ነዋሪ በሆኑ ወጣት ወንዶች የገቢ መቀነስና ስራ አጥ የመሆን አዝማሚያ ይታያል፡፡ በጥናቱም ሀያ ሰባ በመቶ ያህል መላሾች ከቤተሰብ አባላቸው ቢያንስ አንድ ሰው ስራ እንዳጣ ገልጸዋል፡፡

የምግብ ዋስትናን በተመለከተ የምግብ ዕጥረት ችግር እየተባባሰ መጥቷል፡፡ በተለይ ደግሞ የምግብ ዋስትና ያልነበራቸው ቤተሠቦች ለተባባሰ የምግብ ዕጥረት ተጋልጠዋል፡፡ ትምርትን በሚመለከት ትምህርት ቤት ከተዘጋ በኋላ ትምህርታቸውን በርቀት መቀጠል የቻሉ በጣም ጥቂት የሆኑ ህፃናት ናቸው፡፡ በአብዛኛው የገጠር ነዋሪዎችና ቤተሰቦቻቸው መደበኛ ትምህርት ያልተማሩ የሆኑ ህፃናት ትምህርታቸው ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ለማቋረጥ ተገድደዋል፡፡

## 8 ከተማ/ገጠር እና በክልል ደረጃ ያሉ ልዩነቶች

በነሀሴ ወር 2012 መጀመሪያ ቫይረሱ ከተገኘባቸው ሰዎች መካከል ሠባ ሠባት በመቶ ያህሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ነበሩ። በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር ከአምስት በመቶ በላይ አልነበረም። እንደ አዲስ አበባ ባሉት ትልልቅ ከተሞች በሌሎች ክልሎችና የገጠር ቦታዎች በከፋ ሁኔታ የቫይረሱ ስርጭት እንዳለ ያመለክታል። ሆኖም ግን በሁሉም ክልሎች ሠፊ የአቦሰጥ (random) ምርመራ እስካልተካሄደ ድረስ በእርግጠኝነት በከተሞች ሰፊ ስርጭት አለ ብሎ ለማጠቃለል ይከብዳል። አሁን ባለው ሁኔታ አብዛኛው ምርመራ (73 በመቶ ያህሉ) የተካሄደው በአዲስ አበባ እንደሆነ ማየት ይቻላል።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ልዩነት በከተማና በገጠር ነዋሪዎች መካከል እንዲሁም በወንዶችና በሴቶች መካከል እንዳለ ለመረዳት ተችሏል። ለዚህም የስልክ እና ኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት መቻል በዋና ምክንያትነት ይጠቀሳል።

## 9 ለወረርሽኙ የተጋለጡ ዘርፎችና የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በደሀው፣ በቀን ስራ በሚተዳደረውና የሰው እጅ በሚጠብቁት ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። ከዚህ በተጨማሪ በአገልግሎት ዘርፎች (ለምሳሌ በቱሪዝም፣ በሆቴል በምግብ አቅርቦት፣ በሸቀጣ ሸቀጥ አቅርቦት፣ በጸጉር ስራ... ወዘተ) የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በወረርሽኙ በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድተዋል። የሰውን እጅ የሚጠብቁ የኔ ቢጤዎች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ አቅመ ደካሞችና አካል ጉዳተኞች የችግሩ ገፈት ቀማሾች ናቸው። የሌላ ሰው ገቢ ሲቀንስ በተዘዋዋሪ እነዚህ የዕለት ጉርሳቸውን ከሰው እጅ የሚጠብቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ገቢ መቀነሱ ዕሙን ነው።

ከነዚህ በተጨማሪ ከስደት ተመላሾች - በተለይም በግዳጅ ከስደት የተመለሱ፣ በሀገር ውስጥ ከቦታ ቦታ ለተለያዩ ስራ የተሰደዱ (በአበባ እርሻዎች ፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በግንባታ ቦታዎች ለመስራት)፣ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች፣ የኤች.አይ.ቪ. ተጠቂዎች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ቤት አልባዎች፣ ችግረኞች ... ወዘተ በወረርሽኑ ምክንያት የከፋ ጉዳት ሊያጋጥማቸው ይችላል።

## 10 አዲሶቹ ‹ባለስራ ድሆች›

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ችግር እያስከተለ ያለው ከዚህ በፊት ችግር ላይ የነበሩትን ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ወጥተው በሚሰሩትና ደህና ኑሮን ይኖሩ በነበሩት ላይ ጭምር ነው። በውጤቱም ወረርሽኑ ባመጣው ችግር በልማድ ከሚታወቁ ለችግር ከተጋለጡ ክፍሎች በተጨማሪ አዲስ ለችግር የተጋለጠ ‹የባለስራ ድሆች› ክፍል ተፈጥሯል። እነዚህ ክፍሎች በፊት በቂ የሆነ መተዳደሪያ የነበራቸውና በወረርሽኑ ምክንያት ኑሮን ማሸነፍ ያቃታቸው ሲሆኑ፤ በአብዛኛው በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ፣ የራሳቸውን የስራ ዕድል ፈጥረው ይሰሩ የነበሩ እና በዓለም አቀፍ ትስስር አማካኝነት ስራ ሲሰሩ የነበሩትን ያካትታል።

## 11 ሌሎች ችግሮች የመዘንጋት ስጋት

ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በሀገር ውስጥ ያሉ ሌሎች ችግሮችን እንዳይጋርድና እነዚህ ከታች የተዘረዘሩ ችግሮች እንዳይዘነጉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ሀ/ ከአንበጣ ወረርሽኝና ከጎርፍ ጋር በተያያዘ የሚከሰት የምግብ ዋስትና ችግር፤

ለ/ እንደ ቢጫ ወባ እና ኮሌራ ያሉ ሌሎች የጤና ስጋቶች፤

ሐ/ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት፤

መ/ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና

ሠ/ በወረርሽኑ ምክንያት የሚከሰት የረጅም ጊዜ ችግር።

እነዚህ ተፈጥሯዊ (አካባቢያዊ)፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መልክ የሚኖራቸው የረጅም ጊዜ ችግሮች ናቸው። የእነዚህን ችግሮች መጠንና ጥልቀት ከወዲሁ ማወቅ ባይቻልም፤ አደገኛና ቀጣይ ተፅዕኖዎች ሊያሳድሩ እንደሚችሉ በመገመት ከወዲሁ መዘጋጀት ይገባል።

## 12 መደምደሚያ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ እየጨመረ ያለ ችግር ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ለበሽታው ክትባት ለማግኘት እየተደረገ ያለው ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም ክትባቱን በቅርብ ጊዜ ለማግኘት ያለው ተስፋ ጥቂት ነው[1]። በዚህም ምክንያት ቫይረሱ ከሰዎች ጋር መቆየቱ አይቀሬ በመሆኑ ያለን አንድ አማራጭ ተላምደንና ተቋቁመን መኖር ነው። ወረርሽኙ ያሸንፈናል ወይስ እናሸንፈዋለን? የጤና ስርዓታችን ወረርሽኙን ይቋቋመዋል ወይስ ወረርሽኙ የጤና ስርዓታችንን ያሽመደምደዋል? የሚለው ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ሲሆን ሁሉም ሰው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በመወጣት ራሱንና ማህበረሰቡን ከቫይረሱ ሊጠብቅ ይገባል። ወረርሽኙ ከፍተኛ የሆነ የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ግን ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

[1] ይህ ጽሁፉ የኮቪድ-19 ክትባቶች ከመገኘታቸው ቀደም ሲል የተዘጋጀ በመሆኑ የተሰጠ መላ-ምት ሲሆን፤ ከዚያ ወዲህ ስልጣን በተሰጣቸው የተለያዩ ብሔራዊ ተቆጣጣሪ አካላት (National regulatory authorities) ፈቃድ የተሰጣቸው ስድስት ክትባቶች (Oxford–AstraZeneca, Pfizer-BioNTech, Sinopharm-BBIBP, Moderna, Sinovac and Janssen) ተፈልስፈው በሰፊው ጥቅም ላይ ውለዋል።

# የኮቪድ 19 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ በኢትዮጵያ

አለማየሁ ገዳ

## 1 መ ግ ቢ ያ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ከመከሰቱ ጥቂት ቀድሞ ወረርሽኙ በአውሮፓና በአሜሪካ ያስከተለውን አይነት ተመሳሳይ ጉዳት በኢትዮጵያም እንደሚያስከትል ተሰግቶ ነበር። ሀገሪቷ በቅርብ ጊዜያቶች ያሳየቻቸው ዕድገቶችም እንደሚቀንሱና የድህነት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምርም ተተንብዮ ነበር። ይህ እንዳይከሰትና የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት ኢትዮጵያ ያላትን ሁሉ ግብዓት በመጠቀም ከፍተኛ ጥረት እንድታደርግ በተሰጣት ማሳሰቢያ መሠረት ይህንን ስትተገብር ቆይታለች።

እየተስፋፋ ያለው ይህ አስከፊ ወረርሽኝ ያስከተለውን እና ሊያስከትለው የሚችለውን ጉዳት እንዲሁም የኢኮኖሚ (ምጣኔ ሀብት) አለመረጋጋት ለመከላከል በጤናም ሆነ በኢኮኖሚ ዘርፎች የሚገኙ መረጃዎችን በመረዳትና በመተንተን አፋጣኝ የፖሊስ ምላሽ መስጠት ይገባል።

በኢትዮጵያ ባለው የአኗኗር ሁኔታ ምክንያት በኮቪድ ሳቢያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ሙሉ በሙሉ ለመገደብ አዳጋች ነው። በመሆኑ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በከፊል ዝግ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል። የዚህ ጽሑፍ ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ ያለውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅዕኖ በከፊል ዝግ የነበረውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ይመለከታል።

ይህንንም ለመረዳት ያስችል ዘንድ ጥናቱ ሦስት የተለያዩ ‹‹ቢሆኔዎችን›› (senarios) አስቀምጧል።[1]

የመጀመሪያውና ከሁሉም የተሻለው ‹‹ቢሆኔ›› (senario) አሁን ያለው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እስከ አዲሱ የበጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብቻ ቢቀጥልና (ከሐምሌ 12 ቀን 2012 እስከ መስከረም መጨረሻ 2013 ዓ.ም) ከዚያም ባለፈ ባለው ጊዜ ኢኮኖሚው ወደነበረበት መደበኛ እንቅስቃሴ ቢመለስ የሚለውን ግንዛቤ ያደረገ ነው። ሁለተኛው ‹‹ቢሆኔ›› አሁን ያለው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እስከ ሁለተኛው ሩብ የበጀት ዓመት (ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2013) ቢቀጥልና ሁኔታዎች ከታህሳስ በኂላ ወደነበሩበት ቢመለሱ የሚል ነው። እንደኔ ይህ በጣም ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው። ሦስተኛውና በጣም የከፋው አሁን ያለው ሁኔታ እስከ ሦስተኛው ሩብ የበጀት ዓመት (ከጥር እስከ መጋቢት 2013 ዓ.ም) ቢቀጥል የሚለውን ግንዛቤ ያደርጋል። በሦስቱም ‹‹ቢሆኔዎች›› (senarios) የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ወረርሽኙ ባልነበረባቸው ባለፉት ሦስት ዓመታት ከነበሩ ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች ጋር ተነጻጽረዋል።

## 2 የኢትዮጵያ ወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ

የኢትዮጵያ መንግስት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት “*ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም*” በሚል ርዕስ ለሁለት ዓመታት የሚዘልቅ የኢኮኖሚ ሪፎርም (ማሻሻያ) እና ነፃ የማውጣት (ሊበራላይዜሽን) መርሀ-ግብር ይዞ በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ነበር። ይህ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድ በዋናነት የመንግስት አገልግሎትን ውጤታማነት ማሻሻል እና ኢኮኖሚውን ነፃ በማውጣት (ሊበራላይዝ ለማድረግ) ቁልፍ የሚባሉ

[1] ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የተዘጋጀው አገሪቱ በኮቪድ አስቸኳ ጊዜ አዋጅ ስር በነበረችበትና በዚህም ሳቢያ ኢኮኖሚው በከፊል በተዘጋበት ወቅት ነበር።

የመንግስት የልማት ተቋማትን ወደ ግል ሴክተሩ ማዘዋወርን ዓላማ ያደረገ ነው። ይህም የሪፎርም (የተሀድሶ) አጀንዳ እንደ ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ባሉ ድርጅቶች የሚደገፍና ለዓላማውም ማስፈጸሚያ ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ የፈሰሰበት ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ በጀመረበት ወቅት ነበር የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገሪቷ የተከሰተውና የተስፋፋው። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባይቀሰቅስ ኖሮ በተጀመረው የኢኮኖሚ ሪፎርም እንቅስቃሴ ምክንያት 2012 ዓ.ም የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ዕድገት በዘጠኝ በመቶ (9%) እንደሚያድግ ተገምቶ ነበር። ይህ የዕድገት ቁጥር ከዓመት በፊት መንግስት ካስቀመጠው የዕድገት መጠን ጋር ተመሳሳይ ነው (NBE, 2019/2020)። የዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በቅርብ ጊዜ በሰኔ ወር እንደገመቱት በ2012 ዓ.ም የሚኖረው የኢኮኖሚ ዕድገት ከስድስት በመቶ (6%) ወደ ሦስት ነጥብ አምስት በመቶ (3.5%) እና አራት በመቶ 4% እንደሚወርድ ገምተዋል። መንግስትም ቢሆን ዘጠኝ በመቶ (9%) ዕድገት ይመዘገባል ተብሎ ታቅዶ የነበረውን በተመሳሳይ ጊዜ ወደ ስድስት በመቶ (6%) እንደሚወርድ ግምት ወስዷል። በመጨረሻው ሩብ ዓመት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅዕኖን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና የመንግስት ስድስት በመቶ (6%) የኢኮኖሚ ዕድገት ግምትን በማገናዘብ እንደኔ ግምት የ2012 ዓ.ም ዕድገት መጠን ሦስት በመቶ (3%) ይሆናል።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በ2012 ዓ.ም የነበረውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሀምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም የጀመረው የ2013 ዓ.ም የበጀት ዓመት ምን ምን ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ የሚለውን ይመለከታል። ይህንንም ለማድረግ የመንግስትና የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን አጠቃላይ ምልከታ ግንዛቤ አድርጓል። ይህ ምልከታ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ ያስችላሉ የተባሉ የፖሊሲ ሀሳቦችንም ያመላክታል።

በ2012 ዓ.ም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከመቀስቀሱ በፊት ጀምሮ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ በሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና አስቸጋሪ በሆነ የክፍያ ሚዛን (balance of payment) መዛባት የተወጠረ ነበር:: በዚህም የውጭ ምንዛሬ ዕጥረትም ተከስቶበት ነበር:: የተወሰኑ መረጃዎችን ለመጥቀስም ያህል በነሐሴ 2012 ዓ.ም የኑሮ ግሽበት መጠን ሀያ ሦስት በመቶ (23%) የነበረ ሲሆን የምግብ ግሽበት መጠን ደግሞ 26 በመቶ (26%) ደርሶነበር:: የብር ምንዛሬ ዋጋም በህዳር ወር 2012 ከነበረው ሀያ ስምንት (28) ብር በነሐሴ 2012 ዓ.ም ወደ ሰላሳ ስድስት (36) ብር ወርዷል:: ይህ የብር ዋጋ ከነበረበት ዋጋ በሀያ ስምንት በመቶ (28%) መውረዱን ያመለክታል:: የመንግስት ዕዳ (በለጋሾች ቃል የተገባውን ሳይጨምር) ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነፃፀር ከሀምሳ አምስት በመቶ (55%) በላይ ሆኗል:: በገቢና ወጪ ንግዱም መካከል ያለው ልዩነት እጅግ ሰፊ ነው:: ይኸውም ሀገሪቱ ወደውጪ ከምትልከው ምርት ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባው በአምስት ዕጥፍ ይልቃል:: የወጪ ንግድም ቢሆን በመቀዛቀዙ ምክንያት ባለፉት አምስት ዓመታት ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በታች ሆኗል:: ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ዓመት መንግስት ሠላሳ (30) ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች (ከነዚህ ግማሽ ያህሉ በኮቪድ-19 ተፅዕኖ ምክንያት) ለምግብ ዕጥረት እንደሚጋለጡና ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ተንብዮአል:: ይህ ሁሉ ሁኔታ ባለበት ወቅት ነው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሀገሪቱን የመታው (ለዝርዝሩ ከስር ያለውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ):: የወረርሽኙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ይህንን አስቸጋሪ የሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ መልክ ወደከፋ ሁኔታ ይቀይረዋል::

## ሠንጠረዥ 1፡ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ በፊት ያለ ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ገፅታዎች በኢትዮጵያ

| ማክሮ ኢኮኖሚ አመላካች | የበጀት ዓመት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| ትክክለኛ አገር ውስጥ ምርት ዕድገት መጠን (በ%) | 10.3 | 10.4 | 7.6 | 10.1 | 7.7 | 9.0 | 6.2 |
| የዋጋ ግሽበት መጠን (በ%) | 8.1 | 10.4 | 7.5 | 8.8 | 16.8 | 15.3 | 23 |
| የምግብ ግሽበት | 10.3 | 12.5 | 7.2 | 11.2 | 14.1 | 19.8 | 26 |
| በዓመቱ መጨረሻ የምንዛሬ ተመን (ብር/ዶላር) | 19.6 | 20.6 | 21.8 | 23.1 | 27.4 | 28.9 | 36 |
| መጠባበቂያ (ከውጭ የሚገቡት/ወር) | 2.3 | 2.5 | 2.6 | 2.4 | 2.1 | 2.4 | 1.7 |
| አጠቃላይ የአገር ውስጥ ቁጠባ (% ከአገር ውስጥ ምርት) | 22.5 | 21.9 | 22.4 | 22.5 | 19.7 | 20.2 | |
| አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት (% አገር ውስጥ ምርት) | 40.3 | 39.4 | 38.5 | 38.4 | 34.1 | 37.7 | |
| አጠቃላይ የበጀት ጉድለት ድጎማን ጨምሮ (የመጀመሪያ ደረጃ ጉድለት % ከአገር ውስጥ ምርት) | -2.6 | -2.5 | -1.9 | - 3.28 | - 3.03 | -2.5 | |
| የሂሳብ ዕጥረት (ህጋዊ ልውውጥን ጨምሮ% ከአገር ውስጥ ምርት) | -7.7 | -11.4 | -10.4 | -8.0 | -6.3 | -4.7 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የንግድ ሚዛን (X-M) % ከአገር ውስጥ ምርት | - 18.7 | -20.8 | -19.1 | - 16.0 | - 14.7 | - 13.0 | |
| የውጭ ዕዳ (በሚሊዮን አሜሪካ ዶላር) | 14.0 | 19.09 | 21.74 | 23.3 | 25.8 | 27.0 | 27.7 |
| ውጭ ዕዳ (% ከአገር ውስጥ ምርት) | 25.6 | 29.5 | 30.1 | 29.4 | 31.9 | 29.1 | 28.8 |
| የአገር ውስጥ ዕዳ (% ከአገር ውስጥ ምርት) | 28.6 | 31.8 | 32.1 | 34.9 | 35.6 | 35.7 | 26.7 |
| አጠቃላይ ዕዳ (% ከአገር ውስጥ ምርት) | 53.2 | 61.4 | 62.2 | 64.3. | 67.5 | 64.8 | 55.6 |

ምንጭ፡-የብሔራዊ ባንክና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ዓመታዊ ሪፖርቶች

የዚህ ጥናት ትንተና ሦስት ‹‹ቢሆኔዎችን›› (senarios) ግንዛቤ ያደረገ ነው፡፡ የመጀመሪያውና ከሁሉ የተሻለው ‹‹ሴናርዮ›› አሁን ያለው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እስከ አዲሱ የበጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብቻ ቢቀጥልና (ከሐምሌ 12 2012 እስከ መስከረም መጨረሻ 2013 ዓ.ም) ከዚያ ባለፈ ባለው ጊዜ ኢኮኖሚው ወደነበረበት መደበኛ እንቅስቃሴ ቢመለስ የሚለውን ግንዛቤ ያደረገ ነው፡፡ ሁለተኛው ‹‹ቢሆኔ›› አሁን ያለው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እስከ ሁለተኛው ሩብ የበጀት ዓመት (ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2013) ቢቀጥልና ሁኔታዎች ከታህሳስ በኋላ ወደነበሩበት ቢመለስ የሚል ነው፡፡ እንደኔ ይህ በጣም ሊሆን የሚችል ዕይታ ነው፡፡ ሦስተኛውና በጣም የከፋው አሁን ያለው ሁኔታ እስከ ሦስተኛው ሩብ የበጀት ዓመት (ከጥር እስከ መጋቢት 2013 ዓ.ም) ቢቀጥል የሚለውን ግንዛቤ አድርጓል፡፡ የመጨረሻውን ‹‹ቢሆኔ›› ለመከሰት ያለው ዕድል እጅግ አናሳ በመሆኑና ይህም ፅሑፍ

በሚፃፍበት ወቅት ኢኮኖሚው ማገገም መጀመሩን ግንዛቤ በማድረግ በስፋት አልተዳሰሰም፡፡

## 3 የኮቮድ-19 ወረርሽኝ በአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት እና በዘርፎች ዕድገት ላይ ያለ ተፅዕኖ

*የአገር ውስጥ ምርት እና የዘርፎች ዕድገት ተፅዕኖ*

የኮቮድ-19 ወረርሽኝ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በአማካኝ ‹‹ቢሆኔ›› በአዲሱ የበጀት ዓመት (2013 ዓ.ም) የመጀመሪያ ሁለት ሩብ ዓመታት ይዘልቃል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ሁኔታ በቫይረሱ ተፅዕኖ ምክንያት የሀገር ውስጥ ምርት መጠን (GDP) በያዝነው የ2013 ዓ.ም የበጀት ዓመት አስራ አንድ ነጥብ አንድ በመቶ (11.1%) ሊቀንስ ይችላል፡፡ የቫይረሱ ተፅዕኖ ጥሩ በሚባለው ‹‹ሴናርዮ›› በመጀመሪያው ሩብ የበጀት ዓመት ብቻ ይቀጥላል ተብሎ ቢታሰብ የሀገር ውስጥ ምርት መጠን ማሽቆልቆል አምስት ነጥብ ስድስት በመቶ (5.6%) ብቻ ሊሆን ይችላል (ምስል 1)፡፡ መንግስት የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያውን መጠን በመከለስ የ2013 ዓ.ም ኢኮኖሚ ዕድገት ስድስት በመቶ (6%)፤ የሀገር ውስጥ ምርት መጠን (GDP) ሁለት ትሪሊዮን ብር እንደሚሆን ገልጿል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ በአስራ አንድ በመቶ (11%) ማሽቆልቆል የሀገር ውስጥ ምርት መጠንን በሁለት መቶ ማለትም በሁለት መቶ ሀያ ቢሊዮን ብር በተመጣጣኝ መልኩ ይቀንሰዋል፡፡ ጥሩ በሚባለው ‹‹ቢሆኔ›› የሀገር ውስጥ ምርት መጠን በአምስት ነጥብ ስድስት በመቶ (5.6%) ይቀንሳል፡፡ ይህም በብር ሲሰላ የሀገር ውስጥ ምርት መጠኑ በአንድ መቶ አስራ ሁለት ቢሊዮን (112 ቢሊዮን) ይቀንሳል ማለት ነው (ምሳሌ 1)፡፡

ከዚህ በታች ያለው ምስል የኮቪድ 19 በተለያዩ ዘርፎች ያለውን ተፅዕኖ ያሳያል፡፡ መረጃው የኢኮኖሚ ሞዴሎችን መሠረት አድርጎ የተሰራ የቅርብ ጊዜ ትንበያ ነው፡፡

**ምስል 1፡** <u>በኮቪድ-19 በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርትና በተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ዕድገት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ በተለያዩ ታሳቢ ‹‹ ሲናርዮዎች›› (ቢሆኔዎች)</u>




መንግስት በ2013 ዓ.ም የበጀት ዓመት ኢኮኖሚው በስምንት ነጥብ አምስት በመቶ (8.5%) እንደሚያድግ ተንብዮአል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ትንበያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሊያስከትል የሚችለው ተፅዕኖ ግምት ውስጥ ይግባ ወይም አይግባ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ የወረርሽኙ ተፅዕኖ ግምት ውስጥ ያልገባ ከሆነ ስምንት ነጥብ አምስት (8.5%) የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስመዝገብ ቢያንስ አስራ ዘጠኝ ነጥብ ሰባት በመቶ (19.7%) የዕድገት መጠን ሊኖር ይገባል (ይህ ማለት ወረርሽኙን ተፅዕኖ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት 11.2 + 8.5 ማለት ነው)፡፡ ይህን ያህል የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ መቻል ከእውነታው እጅግ የራቀ ነው፡፡ በሌላ በኩል አማካኝ በሆነው ‹‹ሴናርዮ›› በወረርሽኙ ተፅዕኖ ምክንያት የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከዜሮ በታች ነጌቲቭ ሁለት ነጥብ ሰባት በመቶ (2.7%) ይወርዳል፡፡ በዚህ ጥናት መሠረት ጥሩ በሆነው ‹‹ሴናርዮ›› የኢኮኖሚ ዕድገት መጠኑ (Rate) በ5.6 በመቶ የሚቀንስ ሲሆን የ2013 ኢኮኖሚ ደግሞ በሦስት በመቶ ያድጋል፡፡ ይህ ትንበያ

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ እና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ካስቀመጡበት ትንበያ ጋር ተመሳሳይነት አለው (ሠንጠረዥ 2ትን ይመልከቱ)::

**ሠንጠረዥ 2**:-<u>በተለያዩ ተቋማት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ኢኮኖሚ ተፅዕኖ በተመለከተ የተቀመጠ ትንበያ</u>

| አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (የተለያዩ ግምቶች) | ቀዳሚ የበጀት ዓመት (2012 ዓ.ም) | | የዘንድሮ በጀት ዓመት ትንበያ (2013 ዓ.ም) | |
|---|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ መንግስት | 9.0% | 6.0% | | 8.5% |
| የዓለም ባንክ (የ2012 እና 2013 ዓ.ም) | 6.0% | 3.2% | | 3.6% |
| የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (የ2012 እና 2013 ዓ.ም) | 6.0% | 3.2% | | 4.3% |
| የአፍሪካ ልማት ባንክ (2012 እና 2013 ዓ.ም) መጥፎ በሆነው ሲናርዮ | 7.1% | 3.6% [2.6%] | | 5.5% [3.1%] |
| የግል አማካሪዎች ትንበያ (ዴልዮቴ) | | | | 3% |
| የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማህበር (በሳም ሞዴል ጥናት 2012/2013 ዓ.ም) | | | -5.9 to-6.7 [-13.1] | 2.6 [0.6] |
| የኔ ግምት (‹‹በከፋው ሴናርዮ››) | | 3.0% | -5.6 [-11.2] | 3%[-2.6] |
| ዓለም አቀፍ የድህነት መጠን (ዓለም ባንክ) | | | የድሀዎች ቁጥር | |
| የመንግስት መረጃ (20 ብር በቀን ወይም 600 ብር በወር) | | 22% | +15 ሚሊዮን | 36% |
| 3.20 ዶላር የብር የመግዛት አቅም (45 ብር (1.25 ዶላር) በቀን ወይም 1350 ብር በወር) | | 73% | +15 ሚሊዮን | 87% |

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅዕኖ በኢንዱስትሪው እና አገልግሎት ዘርፍ ላይ ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል:: የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአስራ ሦስት ነጥብ ስድስት በመቶ (13.6%)፣ የአገልግሎት ሠጪው ዘርፍ ደግሞ በአስራ ዘጠኝ በመቶ (19%) እንደሚቀንሱ ይጠበቃል:: የግብርናው

ዘርፍ በኮቪድ-19 በአነስተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሲሆን በችግሩ የተነሳ በአንድ ነጥብ ስድስት በመቶ (1.6%) እንደሚቀንስ ይጠበቃል። መልካም በሆነው ‹‹ሴናርዮ›› የጉዳት መጠኑ ከአንድ በመቶ በታች ሊሆን ይችላል። መልካም በሆነው ‹‹ሴናርዮ›› የወረርሽኙ ተፅዕኖ በኢንዱስትሪው ዘርፍ በስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ (6.8%) አገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ዘጠኝ ነጥብ አራት በመቶ (9.4%) መቀነስ ይቻላል።

የወረርሽኙ ተፅዕኖ በዋናነት ኢንዱስትሪውንና አገልግሎት ዘርፎች መጉዳቱ በሌላ መልኩ የከተማው ኢኮኖሚ ከገጠሩ ኢኮኖሚ በላቀ መልኩ በኮቪድ-19 ተፅዕኖ እንደሚጎዳ ያሳያል። ይህም የሆነው የገጠሩ ኢኮኖሚ መሠረት በዋነኝነት ግብርና በመሆኑ ነው። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነበት ዋና ምክንያት በወረርሽኙ በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ የሚያድርባቸው የኢንዱስትሪው እና አገልግሎት ዘርፎች ለሀገሪቱ አጠቃላይ ዕድገትም ሆነ በከተሞች ላለው የስራ ዕድል ከፍተኛ ሚና ስላላቸው ነው። ከታች ባለው ምስል ማየት እንደሚቻለው የኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፎች ሰማንያ አምስት በመቶ (85%) ለሚሆነው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ሰማንያ ስምንት በመቶ (88%) ለሚሆነው የከተማ ስራ ዕድል ምንጭ ናቸው።

## ምስል 2:- በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጋላጭ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች




* ይህ የፋይናንስ አስተላላፊዎችን (financial intermediaries)፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ሶሻል ወርክ፣ በስራ የተሰማሩ ሰዎች ያሉባቸው የግል ቤተሰቦችን እና ሌሎች የማህበረሰብ፣ ማህበራዊና ግለሰባዊ አገልግሎቶችን ያካትታል፡፡

## 4 የኮቮድ-19 ወረርሽኝ በውጭ ዘርፎች ላይ ያለ ተፅዕኖ

እንደ ዓለም አቀፍ ንግድና ፋይናንስ ያሉ የውጪ ዘርፎች ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅዕኖ በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ናቸው፡፡ ይህ መሆኑ በተራው በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል፡፡ እነዚህ ዘርፎች ተጋላጭ የሆኑበት ዋነኛ ምክንያት ወረርሽኙ በዓለም አቀፍ የሸቀጥ ዋጋዎች ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ምክንያት የገቢና ወጪ መጠኖች ላይ ከፍተኛ አለመመጣጠን በመፍጠሩ፤ እንዲሁም እንደ ቻይና፣ ኤዥያ፣ አውሮፓ እና አሜሪካ ካሉ የንግድ ትስስር ካሉን ሀገራት ጋር ያለንን የአቅርቦት ሠንሠለት ክፉኛ በመጉዳቱ ነው፡፡

የውጭው ዘርፍ በወረርሽኙ ተፅዕኖ ምክንያት አጠቃላይ ወደ ውጭ የሚላከውን ሸቀጥ መጠን በአማካኝ ‹‹ሲናርዮ›› በአስራ ሦስት በመቶ (13%) ይቀንሳል:: ይህ መጠን ጥሩ በሚባለው ‹‹ሲናርዮ›› ወደ ስድስት በመቶ (6%) ይወርዳል:: ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን በተመለከተ አማካኝ በሆነው ‹‹ሲናርዮ›› አስራ ሁለት በመቶ (12%) እንደሚቀንስ ሲጠበቅ፤ መልካም በሚባለው ‹‹ሲናርዮ›› በስድስት በመቶ (6%) የሚቀንስ ይሆናል:: ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ምርት መቀነሱ በቀናነቱ ሊታይ ይችላል:: ይኸውም ከፍተኛ የሆነውን የገቢና ወጪ አለመመጣጠን ወይም የንግድ ሚዛን ጉድለትን ስለሚቀንስ ነው:: በሌላ አነጋገር የገቢውን መጠን በመቀነስ ከወጪ ጋር ያለውን ሰፊ ልዩነት ስለሚያጠበው ነው:: ለምሳሌ ያህል ነዳጅ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የምናወጣው ወጪ በሰላሳ በመቶ (30%) እንደሚቀንስ ይጠበቃል:: በሌላ በኩል ይህ መሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖም አለው:: ይህም የሚሆነው እንደ ምግብ ያሉ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ በገበያ እንዳይገኙ በማድረግ የዋጋ ግሽበትን ከማስከተሉም በላይ ከውጪ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች ከውጪ ተገዝተው የሚገቡ ግብዓቶች ዕጥረት እንዲደርስባቸው በማድረግ እንቅስቃሴያቸውን ያስተጓጉላል::

የወጪ ንግድ መጠን መቀነሱም ቢሆን አሁን ሁለት ቢሊዮን ዶላር በሆነውን የውጪ ዕዳ አገልግሎት መጠን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል (ይህ መጠን ሁለት ሦስተኛ የሚሆነውን የወጪ ሸቀጣ ሸቀጥ መጠን ነው):: በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅዕኖ ምክንያት አሁን 72 በመቶ ያህል የወጪ ሸቀጥ መጠን የሆነው የውጪ ዕዳ ወደ ዘጠና ሁለት (92%) በመቶ ያድጋል:: ይህ የሚያመለክተው የብድር ክፍያ ጊዜ ገደብ በድጋሚ እንዲስተካከል አልያም እንዲሰረዝ ካልተደረገ በስተቀር ሀገሪቷ ዕዳዋን ለመክፈል አዳጋች የሚሆንባት በመሆኑ የዕዳ አከፋፈሉን በድጋሚ የማይከለስ ወይም የዕዳ ስረዛ የማይደረግ ከሆነ ሀገሪቱ ለአበዳሪዎቿ ዕዳ መክፈል የማትችልበት ደረጃ ላይ ትደርሳለች::

በሀገሪቱ ያለው የንግድ ሚዛን መዛባትና ከክፍያ ጋር የተያያዙ ችግሮች መዋቅራዊ ናቸው። ይህ ማለት የሀገሪቱ የወጪ ንግድ አቅም ላይ መሠረታዊ ለውጥ ካልተደረገ በስተቀር (ሊሆን የማይችል ቢሆንም) ሀገሪቱ በቀጣይ ዓመታትም በከፍተኛ ሁኔታ በውጪ ፋይናንስ (ዕርዳታ፤ ብድር እና ከወጪ በሚላክ ገንዘብ) ላይ ጥገኛ መሆኗን ትቀጥላለች። ይህም ሀገሪቱ በፖሊሲ ቀረፃ ላይ ያላትን ሉዓላዊነት ያሳጣታል። የካፒታል ፍሰት የማይመጣ ከሆነም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ አሁን ያለውን የውጪ ጥገኝነት በመጨመር የውጪ ምንዛሬ ችግርን ያባብሳል።

## 5 ለዋና ዋና ሴክተሮች የቀረቡ የፖሊስ አቅጣጫዎች

በግብርናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ የምግብ ምርት መጠንን መጨመር ዋና የፖሊስ አቅጣጫ ሊሆን ይገባዋል። ግብርናው ላይ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉ የአገር ውስጥ ምርት መጠን መቀነስን ችግር ከመቅረፉ በላይ የምግብ አቅርቦት ዕጥረትን ያቃልላል፤ ከውጪ ንግድ የሚገኝ ገቢ መጠንንም ይጨምራል። በክልል ዋና ከተሞችና በአዲስ አበባ የምግብ ባንኮችን (መጠባበቂያ ክምችቶችን) ማዘጋጀት ሊከሰት የሚችል የምግብ ዕጥረትን ከመቋቋም አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማረጋገጥ የምግብ ምርትንና ከውጪ የሚገቡ የምግብ ምርቶችን ማሳደግ በተለይ እንደዚህ ፈታኝ በሆነ ወቅት እጅግ አስፈላጊ ነው። በኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበትን በተመለከተ በቅርብ ያጠናሁት ጥናት እንደሚያመለክተው በአገር ውስጥ የምግብ ምርት ላይ የሚደረግ የአስር በመቶ (10%) ዕድገት በሌሎች አጠቃላይ ዋጋዎች ላይ እስከ ሀያ ስድስት በመቶ (26%) ቅናሽ ያስከትላል። ይህ ሂሳብ በግልባጭም ይሰራል። የምግብ አቅርቦት ዕጥረት መኖር የኑሮ ግሽበቱን በከፍተኛ ሁኔታ ያባብሰዋል።

ይህ ጥናት የግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልገው አፅንኦት ቢሰጥም በተቃራኒው ከከተሞች የሚመጣ በሽታ ወደ ገጠሩ ማህበረሰብ

እንዳይተላለፍ በማሰብ የሸቀጦች አገልግሎቶች ፍሰት ሳይቀንስ የገጠርና የከተማ ትስስርን የመቀነስ ፖሊሲን ይመክራል። ለዚህም የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታት የሚያገለግሉ የግንኙነትና የግብይት ስፍራዎችን መገደብ፤ ምርመራዎችን በስፋት ማዳረስ፤ የፊት ጭምብል ማድረግንና አካላዊ ርቀትን በግዴታ መጠበቅ አስፈላጊነትን ይጠይቃል። በተጨማሪም በሸማቾች ማኅበራትና እና በሌሎች አዳዲስ የግብይት አማራጮች የግብይት ሂደቱን ማከናወን አስፈላጊና አዋጭ ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

ወረርሽኙ በገቢና በድህነት ላይ ያለውን ጫና ለማቃለል በጤናው ዘርፍ የሚያስፈልገውን ስራ እየሰሩ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ስራ ማስቀጠል ይገባል። መንግስት ይህንን በማድረጉ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራና ዜጎችም መተዳደሪያቸውን እንዳያጡና ለከፋ ችግር እንዳይጋለጡ ረድቷቸዋል። ከምስል 4 ማየት እንደሚቻለው የመንግስት ምላሽ በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ጎረቤት ሀገሮች አንፃር የተሻለ እንደነበረ መረዳት ይቻላል።

**ምስል 3:** <u>ለኮቪድ 19 የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊስ ምላሽ</u>



የኢኮኖሚው አለመረጋጋትና ተያያዥ በምርት እና በምርት ሂደት ላይ የተከሰቱ የታሰቡና ያልታሰቡ መዘዞች ለድርጅቶችና ሰራተኞች ተጨማሪ የማስተካከያ ወጪዎች ማስከተላቸው አይቀሬ ነው:: ድርጅቶች እንቅስቃሴያቸውን እንዲቀጥሉና በወረርሽኙ ምክንያት ከደረሰባቸው የኢኮኖሚና ፋይናንስ ጫና እንዲያገግሙ መንግስት የተለያዩ የድጋፍ ዕቅዶችን መቀየስ ይኖርበታል:: ይህን ተግባር አሁን ያለውን የዘርፎች እንቅስቃሴ በመገምገም ከወዲሁ ሊጀመር ይገባል::

## 6 ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች

*ድህነት፡-*

ለአዋቂ በቀን ሀያ ብር (በወር ስድስት መቶ ብር) የሚለውን ኦፊሴላዊ የድህነት ወለል መስመርን በመጠቀም ብናሠላ በኢትዮጵያ ሀያ ሁለት በመቶ ህዝብ (ማለትም ከጠቅላላው አንድ መቶ ስምንት ሚሊዮን ከሚገመተው ህዝብ መካከል ሀያ አራት ሚሊዮን የሚጠጋው) ከዚህ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል:: ዓለም አቀፉን አርባ አምስት ብር በቀን (1.25 ዶላር በቀን) ወይም አንድ ሺህ ሦስት መቶ ኃምሳ (1,350) ብር በወር የሚለውን የድህነት ወለል መስመርን ብንጠቅም ደግሞ ሰባ ሦስት በመቶ (ሰማንያ ሚሊዮን ገደማ) የሚሆነው የሀገራችን ህዝብ ገቢው ከዚህ መጠን በታች በመሆኑ ደሀ ነው ማለት ነው::

በኮቪድ-19 ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ምክንያት በአጠቃላይ የድሆች ቁጥር በአስራ አምስት ሚሊዮን ያድጋል ተብሎ ይገመታል:: ኦፊሴላዊ የድህነት መስመርን ብንጠቀም እንኳን በወረርሽኙ ምክንያት የድሆች ቁጥር በአንድ ነጥብ ስድስት ጊዜ እጥፍ ይጨምራል:: የድህነቱ መጠንም ከሀያ ሁለት በመቶ ወደ ሠላሳ ስድስት በመቶ ያድጋል:: እነዚህ ቁጥሮች የምንጋፈጠውን ችግር መጠንና ክብደት ያመለክታሉ::

## *ስራ እና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች፤-*

አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆኑት የመንግስት ሴክተር ሰራተኞች መንግስት ሰራተኞችን የማይቀንስ በመሆኑ በተሻለ ሁኔታ የስራ ዋስትና ያላቸው ሰራተኞች ናቸው። በሌላ በኩል ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን የሚሆኑ በግሉ ዘርፍ ከተቀጠሩ ሰራተኞች ወደ ሦስት መቶ ሀምሳ ሺህ የሚጠጉት ስራቸውን በከፊል ወይም በሙሉ መስራት ካልቻሉ የግል ዘርፎች ስራቸውን ሊያጡና ለችግር ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰራተኞች ለጊዜው መንግስት ባወጣውና የግል ድርጅቶች በወረርሽኑ ወቅት ሰራተኞች ከስራ እንዳያሰናብቱ በሚያግደው ህግ ይጠበቃሉ። በቀጣይነት ግን እነዚህን ሰራተኞች በስራ ለማቆየት መንግስት የግል ድርጅቶችን ወጪ በከፊል ወይም በሙሉ መካፈል ሊያስፈልገው ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪ ወደ ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ በግል ስራ የሚተዳደሩ ሰራተኞች አሉ። በወረርሽኙ ምክንያት በከፊል ኢኮኖሚው በመዘጋቱ ከእነዚህ የግል ሰራተኞች ግማሽ ያህሉ መተዳደሪያቸውን ለማጣት ተገድደዋል። እነዚህ በሁለተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። በሦስተኛነት ደረጃ ተጋላጭ የሆኑት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዝ የተሰማሩት ናቸው። በአጠቃላይ እነዚህ ሦስት ተጋላጭ ክፍሎች ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰራተኞችን የያዙ ናቸው። ኢኮኖሚው በከፊል በሚዘጋበት ሁኔታ አምስት ሚሊዮን ከሚጠጉ ሰራተኞች መካከል ሁለት ሚሊዮን ያህሉ ስራቸውን በማጣታቸው ምክንያት በወር እስከ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን የሚጠጋ ገቢያቸው ይቋረጣል (ሠንጠረዥ 3)።

## ሠንጠረዥ 3፡- ኢኮኖሚው በከፊል በመዘጋቱ ተጋላጭ በሆነ ዘርፎች የሚጠበቅ የገቢ ኪሳራ (በሚሊዮን /በወር)

| ደረጃ (በጉዳት መጠን) | ዘርፎች (ተከፋይ ሰራተኞች) | በወር የሚጠበቅ የሰራተኞች ገቢ ቅናሽ | የደሀዋች ቁጥር መጨመር** (ይፋዊ የደህንነት መረጃን በመጠቀም) |
|---|---|---|---|
| 1 | ግንባታ | 899.6 | አሁን ያለው መጠን |
| 2 | የትራንስፖርት ማከማቻ | 439.6.4 | 22% (24 ሚሊዮን) |
| 3 | አምራች ድርጅቶች | 407.8.6 | ጥሩ ሴናርዮ |
| 4 | ጅምላና ችርቻሮ ንግድ፤ የሞተር ተሽከርካሪዎች ጥገና | 211.2 | 36% (15 ሚሊዮን ጭማሪ)) |
| 5 | ቤተሰቦች እንደተቀጣሪ* | 196.3 | መጥፎ ‹‹ሴናርዮ›› |
| 6 | ግብርና | 190.1 | 48 % (28 ሚሊዮን ጭማሪ) |
| 7 | መረጃ እና መገናኛ | 75.4 | ሥራ ዕጦት |
| 8 | ማረፊያ እና የምግብ አገልግሎቶች | 27.8 | 1.7ሚሊዮን በራሳቸው የሚሰሩ<br>3.5K የግሉ ሴክተር |
| | አጠቃላይ | 2,513.7^ | አጠቃላይ ህዝብ 108 ሚሊዮን |

*3.9 ሚሊዮን ከሚሆኑ ተቀጣሪዎች መካከል 385,578 ያህሉ የቤት ተቀጣሪዎች ናቸው፡፡ ኢኮኖሚው በከፊል ሲዘጋ ግማሽ ያህሉ ስራቸውን ሊያጡ ይችላሉ ብዬ ገምታለሁ፡፡

^ይህ አኃዝ በከተማ አካባቢዎች ተቀጥረው ከሚሰሩ 7.5 ሚሊዮን ሠዎች መካከል በራሳቸው የሚሰሩትን 3.1 ሚሊዮን ሰዎችን አለማካተቱን ልብ ይበሉ፡፡ ነገር ግን ቁጥሩ በፓብሊክ ሴክተር ንዑስ ዘርፎች ውስጥ ያሉትን ያካትታል፡፡ በመንግሥት ሰራተኞችና በግል ሥራ ላይ በተሰማሩት መካከል ተመሳሳይ አማካይ ገቢ አለ ከሚል ግምት በመነሳት አንዱን ጨምሮ ሌላውን ማግለል የሚያስከትለው ውጤት እርስ በርሱ ይቻቻላል፡፡ ስለሆነም የ2.5 ቢሊዮን ኪሳራ ዝቅተኛውን አጠቃላይ ኪሳራ በትክክል እንደሚያሳይ ይገመታል፡፡

**የድህነት መስመሩ የተሰላው ሀያ ብር በቀን (600 በወር) በሚለው ነው፡፡ ዓለም አቀፍ የድህነት መስመሩ 42 ብር በቀን (1,260 በወር) ሲሆን የድህነት መጠኑ 70 በመቶ ወይም 80 ሚሊዮን ይሆናል፡፡

# 7 የማህበራዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የታቀዱ የፖሊስ አቅጣጫዎች

የወረርሽኙን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ በመጀመሪያ ደረጃ ሊወሰድ የሚገባው ዕርምጃ ሰዎች መተዳደሪያዎቻቸውን እንዳያጡ ማድረግና የወረርሽኙ ተፅዕኖ እስኪቀንስ ድረስ ስራ ያጡትን መደገፍ ነው። ይህ ድጋፍ ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘ የጤና አገልግሎቶችን በስራ ቦታዎች ከማቅረብ ጋር አብሮ ሊሰራ ይገባል።

መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ ላሉና አርባ በመቶ ያህሉን የስራ ኃይል ለሚይዙት ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ ለሆኑት ዜጎች ስራ አጥነትና ረሀብ ከፍተኛ ስጋት ናቸው። መንግስትና ህብረተሰቡ ባደረጓቸው መጠነ ሰፊ የድጋፍ እንቅስቃሴዎች ምክንያት ይህ ችግር አሁን ላይ ሲታይ ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም መንግስት የጀመረውን እንቅስቃሴ ቀጣይነት ባለው መልክ ሊሰራ ይገባል። የቫይረሱን ስርጭት በመግታት ሂደት ረሀብን መከላከልና ህግን ማስከበር በተያያዥ በትኩረት ሊሰሩ ይገባል።

በግሉ ዘርፍ ያሉ ሰራተኞችና አሰሪዎችንም በተመለከተ መንግስት ምንም እንኳን የግል ድርጅቶች ሰራተኞቻቸውን እንዳያሰናብቱ ቢመክርም፤ ድርጅቶቹ ያንን በዘላቂነት እንዲያደርጉ የሚረዳበትን መንገድ ገና አልቀየሰም። ይህ ሁኔታ በተለይም ለአነስተኛ ንግድ ባለቤቶች ከባድ ነው። እዚህ ላይ ሁለት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሊቀመጡ ይችላሉ። (1ኛ) የሚቻል ከሆነ እነዚህ የንግድ ድርጅቶች በፈረቃ ስራቸውን እንዲያስቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ መርዳት፤ (2ኛ) መደበኛ ስራ እስኪጀመር ድረስ መንግስት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የድርጅቶቹን የፋይናንስ ጫና እንዲጋራ ማድረግ።

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በግል ስራ ለተሰማሩ የኪራይ ወጪ እንዲቆም ማድረግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ባለመደረጉ ምክንያት እነዚህ ሰራተኞች የወረርሽኙን ከባድ ጫና ለመሸከም

ተገድደዋል። የእነዚህን ሰራተኞች የኪራይ ወጪ መሸፈን/ማገዝ የነዚህን ተቋማት ከፍተኛ ወጪ መጋራት ያህል ነው። በመሆኑም የብድር አቅርቦትን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ የመንግስት ዋነኛ ተግባሩ ሊሆን ይገባል።

## 8 የማክሮ ኢኮኖሚና ፋይናንስ ጉዳዮች

በመንግስት ፋይናንስ ላይ ወረርሽኙ የሚያሳድረው ጫና እጅግ ከፍተኛ ነው። ከዚህ ውስጥ መንግስት የጤናውን ዘርፍ ለማጎልበት የመደበኛ ሦስት መቶ ሚሊዮን ብር፤ ለግል ባንኮች የተሰራጨው አስራ አምስት ቢሊዮን ብር እና የወረርሽኙን ተፅዕኖ ለመቋቋም በፓርላማው ፅድቆ ወደ ተግባር የገባው አርባ ስድስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር (መጀመሪያ 1.6 ቢሊዮን ተብሎ የነበረው) ተጨማሪ በጀት ወደ ኢኮኖሚው እንዲገባ ተደርጓል። ይህ ተጨማሪ የድጋፍ በጀት ፓርላማው አስቀድሞ ካፀደቀው ሀያ ስምንት ቢሊዮን ጋር ሲደመር አጠቃላይ ዘጠና ሁለት ቢሊዮን ይሆናል። በድምሩ በኮቪድ-19 ተፅዕኖ ምክንያት የመንግስት ወጪ መጀመሪያ ላይ ከነበረው በሀያ ሦስት ነጥብ አራት በመቶ (23.4%) አድጓል። ከዚህ በተጨማሪ የኢኮኖሚው መኮማተር በግብርም ሆነ በግብር ባልሆኑ ገቢዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በውጤቱም ድጎማን ጨምሮ መንግስት ያገኘው የነበረው ገቢ በአስራ ስድስት በመቶ ይቀንሰዋል።

የመንግስት ወጪ መጨመርና ገቢ ማሽቆልቆል በመንግስት ላይ ያልተጠበቀ ጫና በመፍጠር የገንዘብ ጉድለትን አስከትሏል። ይህንኑ ጉድለት በገንዘብ ለመደገፍ መንግስት ከብሔራዊ ባንክ በመበደርና ተጨማሪ ብር እንዲታተም አድርጓል። ማክሮ ኢኮኖሚን ከማረጋጋት አንፃር (ዝቅተኛ የዋጋ ግሽበት፤ የተረጋጋ ምንዛሪ መጠን፤ ዘላቂ ጉድለት እና ዝቅተኛ ስራ አጥነት) ይህንን ጉድለት በገንዘብ መደገፍ ለመንግስት ከባድ ጫና ነው። አሁን ካለው ሀያ ሦስት በመቶ የሚሆነውን ከፍተኛ ዋጋ ግሽበት እና ሀያ ስድስት በመቶ የሚሆን

የምግብ ዋጋ ግሽበት አንፃር ከዚህ የበለጠ የዋጋ ግሽበትን (በተለይም የምግብ ዋጋ ግሽበት) ያካተተ የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት የመከሰት ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ ይህም በከፊል በ2012 ዓ.ም በኮቪድ 19 ተፅዕኖ ምክንያት በተከሰተው የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና እርሱንም ተከትሎ በተወሰዱ በፖሊስ ምላሾች የመጣ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ጥንቃቄና ማስተዋል የተሞላበት የማክሮ ፖሊሲ እንዲኖረን ይጠይቃል፡፡

## 9 በማክሮ ኢኮኖሚና ፋይናንስ ፖሊስ የተቀመጡ የፖሊስ አቅጣጫዎች

የተፈጠረው የገንዘብ ጉድለት ከብሔራዊ ባንክ ገንዘብ በመበደር (ገንዘብ በማተም) መፍትሔ ለመስጠት መሞከሩ የዋጋ ግሽበትን ከማባባስ አንፃር አሉታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ይህም ድሆችንና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ይበልጥ በመጉዳት ፖሊሲው የቆመለትን የህዝብን ደህንነት የመጠበቅ ዓላማ ሊያሰናክል ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነት ፖሊሲዎች ሊወገዱ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሰውን አንድ መቶ አርባ ሁለት ነጥብ አራት (142.4) ቢሊዮን ተጨማሪ በጀት ለማግኘት መንግስት ከብሔራዊ ባንክ የተበደረበት ሁኔታ አጠቃላይ የዋጋ መጠንን በሀያ ስድስት በመቶ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትን ሳያስከትል ተመሳሳይ ጉድለቶች ለማረም የሚያስችሉ የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን መከተል ይገባል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

1. <u>የወጪ ሽግሽግ፡-</u> ይህ ማለት መንግስት የወጪ ዝርዝሩን በመመልከትና በመከለስ ለሌላ ጊዜ መተላለፍ የሚችሉና አስቸኳይ ያልሆኑ ወጪዎችን በማሸጋሸግ የእነርሱን ወጪ ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምላሽ ማዘዋወር፤

2. **<u>የገንዘብ ምንዛሬ ዋጋ መጠንን አሁን ካለበት አለማውረድ፡-</u>** የገንዘብ ምንዛሬ መጠንን የበለጠ ማውረድ የወረርሽኙ ተፅዕኖ እስኪወገድ ድረስ የዋጋ ግሽበትንና የቢዝነስ መቀዛቀዝን ስለሚያስከትል ምንም አይነት ዕርምጃ ባይወሰድ ይመከራል፡፡ የእኔ የተሻሻለው የግሽበት ሞዴል እንደሚያሳየው የብርን የመግዛት አቅም አሁን ካለው ከ32 ብር በዶላር ወደ 35.20 ብር ብናወርደው (አስር በመቶ መግዛት አቅሙ ቢቀንስ) የዋጋ ደረጃ አሁን ካለው በሀያ አራት በመቶ ይጨምራል፡፡

3. **<u>የውጪ ፋይንስ፡-</u>** ከውጪ የተገኘውን ገንዘብ ምግብና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እስከተጠቀምንበት ወይም የአገር ውስጥ ምርትን ወይም የፍጆታ ሸቀጦችን ለማሳደግ እስከተጠቀምን ድረስ የውጪ ፋይናንስ አስፈላጊ ነው፡፡ ገንዘቡ የምግብ ምርትን ለማሳደግ የሚውል ከሆነ ውጤታማ እና ግሽበትን የማያስከትል ሊሆን ይችላል፡፡ የዋጋ ግሽበትን የማያስከትል ማክሮ ኢኮኖሚ በኮቪድ-19 ምክንያት የተከሰተውን የመንግስት ወጪ ፋይናንስ በማድረግ የምግብ አቅርቦትን ማሻሻል ይቻላል፡፡ የዋጋ ግሽበት አለመኖርም የምንዛሬ ዋጋ መቀነስ ላይ ያለውን ጫና ይቀንሳል፡፡ በተጨማሪም የዋጋ ግሽበትና ንረት መንግስት ያጸደቀውን በጀት ብር መጠን በማሳደግ ተጨማሪ በጀት እንዳይጠይቅ በማድረግ የዋጋ ግሽበት የተባባሰ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህ ወደ ፖለቲካ ቀውስም ሊመራ ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የዋጋ ግሽበትን የማያስከትል የፋይናንስ ፖሊሲ እንዲቀረፅ ይመከራል፡፡ ይህም ደህውን ከመጠበቅ ባለፈ የማክሮ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጋጋትን በማምጣቱ ነው፡፡

4. <u>የውጪ ፋይናንስ ከተገኘ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ‹‹ከማምከን የገንዘብ ፖሊሲ›› (a monetary policy of sterilization፡-</u> ማለትም በተገኘው የውጭ ሀብት ዕኩል መጠን አጠቃላይ ብድርን መቀነስ) ጋር አብሮ ሊሄድ ይገባል። ይኸውም በተገኘው ወጪ ሀብት መጠን ጠቅላላ የብድር መጠንን መቀነስ ማለት ነው። አላስፈላጊ ወይም አስቸኳይ ያልሆነ የብድር አቅርቦት ለአሁኑ ዕቅድ ከሌሉ ለመተግበር አስቸጋሪ ይሆናል። ቢሆንም ግን መሞከር ያለበት ጉዳይ ነው።

## 10 ማጠቃለያ

ለማጠቃለያ ያህል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከወረርሽኙ ጋር ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች ሳቢያ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንደሚደርሱበት መገንዘብ ይገባል። በዚህም አስከፊ የሆኑ መዘዞች ሊከሰቱ ይችላሉ። በመሆኑም የሚወስኑ ውሳኔዎች በሙሉ በመረጃ፣ በዕውቀትና በሚዛናዊ አስተሳሰብ ሊደገፉ ይገባል።

አሁን የገጠመን ፈታኝ ሁኔታ ከባድና በተለይም በድሆች ላይ አስከፊ ጫና ሊኖረው የሚችል በመሆኑ ጠንከር ያለ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አካሄዶችን ልንከተል ይገባል። ይህ ማለት የቫይረሱ ስጋት እስከሚወገድ ድረስ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ‹‹ኢኮኖሚያዊ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ›› በሚመስል ደረጃ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት መምራት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያውያን፤ ለመንግስት እና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምንጊዜውም በበለጠ ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን በመተው አንድ ሀገር አንድ ህዝብ ሆነው ይህን ወቅት ማለፍ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ አንድነታችንን ለማጎልበት ጥሩ ዕድል ፈጥሮልናል ማለት ይቻላል።

# ኮቪድ-19 እና መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ

## አስናቀ ከፋለ

### 1 መግቢያ

ወረርሽኝ ሰፋ ባሉ አካባቢዎች ላይ የበሽተኛና የሞት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር፣ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እክል እንዲፈጠር የሚያደርግ መጠነ ሰፊ ተላላፊ በሽታ ነው። ለምሳሌም ያህል እ.ኤ.አ በ1981 በአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው የኤድስ ወረርሽኝ ጥልቅ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና በዓለም ዙሪያ አስከትሏል። ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የዓለም አቀፍ ጉዞዎችና የከተሞች መስፋፋት፣ የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ደረጃ መጨመርና ሰዎች የተፈጥሮ ሀብቶችን (ደኖችና የዱር እንስሳትን) በከፍተኛ ደረጃ መበዝበዛቸው ለወረርሽኝ በሽታዎች መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል (Madhav et al, 2017)።

እ.ኤ.አ በ2019 መጨረሻ ላይ በቻይና የተከሰተው የኮቪድ-19 (ከዚህ በኋላ ኮቪድ) ወረርሽኝ በሽታ፤ በቅርቡ የዓለም ታሪክ ከተከሰቱት የወረርሽኝ በሽታዎች በተለየ መልኩ ከፍ ያለ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና በአገራት ላይ አስከትሏል። በወረርሽኙ ምክንያት በርካታ መንግሥታት ምርጫን አራዝመዋል፣ መንግሥታት ከተለያዩ የማህበረሰብ አባላት ጋር ግጭት ውስጥ የጨመራቸውን የእንቅስቃሴ ገደቦች ከመተግበራቸው በተጨማሪ በቅርቡ የክትባት ሥርጭትን በተመለከተ ውዝግብ ውስጥ ገብተዋል።

ይህ አጭር ጽሁፍ የኮቪድ ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ከመልካም አስተዳደር ጋር ያለውን ግንኙነት ይዳስሳል። ጽሁፉ አሁን በአገሪቷ ያሉት የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶች በሽታውን ለመከላከል በሚደረጉ

ጥረቶች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ይገመግማል። ከዚህ የመጀመሪያ ክፍል ጨምሮ ጽሁፉ አራት ክፍሎች ሲኖሩት፤ ሁለተኛው ክፍል የወረርሽን በሽታዎችና መልካም አስተዳደር ያላቸውን ግንኙነት ጠቅለል ባለ መልኩ ይዳስሳል።። ሦስተኛው ክፍል ኮቪድና የመልካም አስተዳደር ሁኔታን በኢትዮጵያ ከተለያዩ ፈርጆች አንጻር ያብራራል። በክፍል አራት አጠር ያለ ማጠቃለያ ቀርቧል።

## 2 ወረርሽኝና መልካም አስተዳደር/ፖለቲካ

ዓለም አቀፍ የሆኑ ወረርሽኝ በሽታዎች በታሪክ እንደምንረዳው ዘለቅ ያሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አንደምታዎች ነበሯቸው። ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ 1918-1919 የተከሰተው የሕዳር በሽታ (ስፓኒሽ ፍሉ) በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ ከ50-100 ሚሊዮን ህዝብ ጨርሷል። ላውራ ስፒኒ የተባሉ ፀሀፊ እ.ኤ.አ 2017 ባሳተሙትና የስፓኒሽ ፍሉ ዓለምን እንዴት እንደቀየረው በሚያብራራው መጽሃፍቸው እንደገለጹት የስፓኒሽ ፍሉ በሽታ ዘላቂ የሆኑ የፖለቲካ፣ የባህልና የሕዝብ አስተዳደር ለውጦችን አስከትሏል (Spinney, 2018)። ለምሣሌም ያህል በእ.ኤ.አ በ1917 ወደ ሥልጣን የመጣው የሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ በታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የሕዝብ የጤና አገልግሎት የጀመረው የወረርሽኝ በሽታው በሕዝብ ላይ ያመጣውን ጉዳት ለመቋቋም በሚል ነበር።

በኢትዮጵያም በሽታው ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ ነበር። የታሪክ ፀሐፊ የሆኑት መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ እንደፃፉት በሽታው በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ባየለበት ወቅት በቀን ከሦስት መቶ በላይ ሰው በመሞቱ ከፍ ያለ ችግርና መደናገጥ ፈጥሮ ነበር (መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ, 1999 ዓ.ም)። ያየህይራድ ቅጣውና ምርጊሳ ካባ እ.ኤ.አ. በ2018 የበሽታውን መቶኛ ዓመት ለማስታወስና ከታሪክ ምን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚቻል ለማውሳት ባሳተሙት ጽሁፍ እንደገለጹት በበሽታው ምክንያት ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው መኳንንትና መሳፍንት

ከመሞታቸውም በላይ አንዳንድ ሹማምንት በሽታውን በመፍራት ከከተማ ወደ ገጠር በመሰደዳቸው ምክንያት የመንግሥት የአስተዳደር አቅም ተዳክሞ እንደነበረ አውስተዋል (Yayehyirad and Mirgissa, 2018)፡፡ ሪቻርድ ፓንክረስት በእ.ኤ.አ. 1975 ባሳተሙት ጽሁፍ እንዳተቱት በበሽታው ምክንያት ከፍ ያለ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ተከስቶ ነበረ፡፡ በሽታውን በመፍራት ፖሊሶች ከሥራቸው ቦታ በመልቀቃቸው ምክንያት በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የዝርፊያ ወንጀል ተስፋፍቶ ነበር (Pankhurst, 1975)፡፡

በሌላ በኩል አንዳንድ ሹማምንት በሽታውን ለመቋቋም የሚረዱ ዕርምጃዎችን ወስደዋል፡፡ ለምሳሌም ያህል በወቅቱ የወለጋ ገዢ የነበሩት ደጃዝማች ብሩ ሱዳን ውስጥ የሱዳን ኢንቲሪየር ሚሽን (Sudan Interior Mission- SIM) በመባል የሚታወቀውን የሚሲዮንና የሕክምና አገልግሎት ይመሩ የነበሩት ዶ/ር ቶም ላምቤ ወደ ግዛታቸው በመግባት የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ጋብዘዋቸዋል፡፡ ዶ/ር ላምቤ የሕክምናና የመንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በመጀመሪያ ወለጋ ሰዮ ደምቢዶሎ ሆስፒታል በመመስረት አገልግሎት ከሰጡ በኋላ አዲስ አበባ በመምጣት በጉለሌ አካባቢ ሆስፒታል አቋቁመው ነበር፡፡ ይህ ላምቤ ተብሎ ይታወቅ የነበረው ሆስፒታል በኋላ ላይ ፓስተር ኢንስቲትዩት (ማዕከላዊ የሕክምና ላቦራቶሪ)፤ አሁን ደግሞ የኮቪድ ወረርሽኝን በዋናነት ከሚከታተሉት የመንግሥት ተቋሞች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና እንስቲትዩት መሠረት በመሆን አገልግሏል፡፡ ዶ/ር ላምቤ ከጉለሌው ሆስፒታል በተጨማሪ በምዕራብ አዲስ አበባ ያቋቋሙት ሆስፒታል ለአሁኑ የአለርት ሆስፒታል መነሻ ሆናል (Cotterell, 1972)፡፡ እንደ ሪቻርድ ፓንክረሰት አገላለጽ የወረርሽኝ በሽታው ያስከተለው ገንቢ ነገር አለ የሚባል ከሆነ ዶ/ር ላምቤ ያቋቋሙት ሆስፒታል ነበር፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን እንደመንደርደሪያ ካነሳሁ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚሰራጩ የወረርሽኝ በሽታዎች ከመልካም አስተዳደር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው አዳስሳለሁ።

## 2.1 የወረርሽኝ መስፋፋትና የመንግሥታት የአቅም ፈተና

በከፍተኛ ደረጃ የሚስፋፉ የወረርሽኝ በሽታዎች የመንግሥትን አቅም አዳክመው የሕግና የሥርዓት መኖርን ሊፈታተኑ ይችላሉ። ሪቻርት ፓንክረስት ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው እንዳሳዩት የሕዳር በሽታ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ በተስፋፋበት ወቅት በኢትዮጵያ የመንግሥት መዋቅርን መዳከም (ወይም መጥፋትን) አስከትሎ ነበር ለማለት ይቻላል (Pankhurst, 1975) ።

በ1980ዎቹ እና 1990ዎቹ የኤድስ በሽታ በሰፊው መስፋፋት በደሀ አገራት ውስጥ የመንግሥትን ሠላምና ደህንነት የማስጠበቅ አቅም በማዳከም ለህገ-ወጥነትና ለሽብር ድርጅቶች መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ግምት ነበር። በመሆኑም እ.ኤ.አ. በ2000 የአሜሪካ መንግሥት ኤድስ ብሔራዊ የፀጥታ ሥጋት ነው በማለት ወስኖ ነበር (Johnson, 2002)። ምንም እንኳን የተገመተው የፀጥታ ተፅዕኖ ባይደርስም በሽታው ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ታዳጊ አገራት ውስጥ የሕዝብ ጤና እንክብካቤ ላይ ከፍ ያለ ተፅዕኖ አስከትሏል። በተጨማሪም በሽታው በቤተሰቦች፣ በማህበረሰቦችና በአገራት ላይ ከፍ ያለ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሳንካ አስተከትሏል (Freedman and Poku, 2005)።

የኮቪድ በሽታ ከኤድስ በተለየ መልኩ የመንግሥትን አቅም የመፈታተን ሁኔታ እንዳስከተለ በዓለም ዙሪያ የተከሰቱ ሁኔታዎች ያሳያሉ። በርካታ መንግሥታት የበሽታውን ሥርጭት ለመቆጣጠር የሕዝብ እንቅስቃሴን የሚገድቡና ዜጎች የፊት ጭምብል እንዲያደርጉ የሚያስገድዱ ህጎችና መመሪያዎችን ቢያወጡም፤ በበርካታ አገራት ህጎቹን በተግባር ለማዋል

የአቅምና የቁርጠኝነት ዕጥረቶች ተስተውለዋል፡፡ በሌላ በኩል የመልካም አስተዳደር ሁኔታዎች ደካማ በሆኑባቸውና የመረጋጋት ችግር ያለባቸው አገሮች በሽታውን ለመቆጣጠር ያላቸው አቅም ደካማ መሆኑ ታይቷል፡፡ የመልካም አስተዳደር አቋማቸው የተሻለ ነው የተባሉ አገራት ውስጥ ሳይቀር የኮቪድ ገደቦች ሁከት የታከለባቸው የተቃውሞ ሰልፎች ምክንያት ሆነዋል[1]፡፡

## 2.2 የፖለቲካ ቁርጠኝነትና ማህበራዊ ዕኩልነት

ወረርሽኝን ለመከላከል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት የኤድስ በሽታ አሳይቷል፡፡ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሲባል በተለያየ ደረጃ ያሉ መሪዎች የወረርሽኝ በሽታን ለመከላከልና ተጎጂዎችን ለመንከባከብና ለማቋቋም በሚቀረጹ መርሀ-ግብሮች ላይ ከመርሃግብሮቹ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈጻጸማቸው ድረስ የሚጫወቱትን ገንቢ ሚናን ያጠቃልላል፡፡ ፒዮት፣ ረስልና ላርሰን የተባሉ የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች ኤድስን በተመለከተ እንዳተቱት አገራት ለኤድስ የሚሰጡት/የሰጡት ትኩረት ከፖለቲካ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ እንደ ጸሀፊዎቹ አመለካከት እንዲያውም የኤድስ ጉዳይ ምን ያህል የሕዝብ ጤና አጠባባቅ ጉዳይ ከፖለቲካና ከአተዳደር ጋር በጥብቅ የተቆራኘ እንደሆነ ጠቃሚ ምሳሌ የሰጠ ነው፡፡ በፀሐፊዎቹ እምነት መንግሥታት አዎንታዊ የፖለቲካ ዕርምጃ በወሰዱባቸው አገራት በሽታውን ለመከላከል የተወሰዱ ዕርምጃዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ሲረዳ፤ በሌላ በኩል በበርካታ አገሮች የፖለቲካ ቁርጠኝነት መጉደል በሽታውን ለመከላከል የሚደረጉ ዕርምጃዎች ውጤታቸው ደካማ እንዲሆን አድርጓል (Piot et al, 2007)፡፡

[1]DW (2021), 'Ireland: Hundreds rally in violent anti-lockdown protest', February 28, 2021, Available: [https://www.dw.com/en/ireland-hundreds-rally-in-violent-anti-lockdown-protest/a-56727668], Access date March 19, 2021.

በተመሳሳይ ሁኔታ የኮቪድ በሽታን ለመከላከል የፖለቲካ ቁርጠኝነት አስፈላጊ መሆኑ በሰፊው ታይቷል። በአንድ በኩል የመልካም አስተዳደር ቁመናቸው ጥሩ የሆኑና (አንዳንዶቹም) በሴቶች የሚመሩ አገሮች በሽታውን በመቆጣጠር ረገድ ቁርጠኝነትና የተሻለ ውጤት ሲያስመዘግቡ (Johnso, 2021)፤ በሌላ በኩል በሕዝበኛ (populist) ቀኝ-ዘመም ፓርቲዎች የሚመሩ መንግሥታት የወሰዷቸው ዕርምጃዎች ለበሽታው መስፋፋት አስተዋጽኦ አድርገዋል። ጆናንታን ላሳና ሚሪንዳ ቡዝ የተባሉ ጸሀፊዎች እንዳሉት እንደ አሜሪካ፣ ብራዚል እና ኢንዶኔዥያ ባሉ አገራት የ‹‹ሕዝበኝነት›› መስፋፋት ምክንያት ለወረሽኙ ተገቢውን ብሔራዊና አለም ዓቀፋዊ ምላሽ ለመስጠት ባለመቻሉ ምክንያት ለበሽታው መስፋፋት አስተዋጽኦ አበርክቷል (Lassa and Booth, 2020)።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በሽታውን ለመቆጣጠር ተገቢውን ትብብርና ሥምምነት ለመፍጠር መሪዎች ቁርጠኝነት ማጣታቸው በተለይም በቻይናና በፕሬዜዳንት ዶናልድ ትራምፕ የሚመራው የአሜሪካ መንግሥታት የገቡበት ውዝግብ በሽታውን ለመከላከል የሚረዳ አለም ዓቀፋዊ ጥምረት ለመፍጠር አላስቻለም። አገራት የበሽታውን ክትባትም በተመለከተ እየወሰዱ ያሉት ‹‹የክትባት ብሔርተኝነት›› (vaccine nationalism) በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዳጋች አድርጎታል።

በሌላ በኩል የኮቪድ በሽታ እንደ አሜሪካ ባሉ በኢኮኖሚ በበለጸጉ አገራት ውስጥ ያለውን የማህበራዊና ኢኮኖሚ ኢ-ፍትሀዊነት በገሀድ አውጥቶ አሳይቷል። ሥር በሰደደ ኢ-ፍትሀዊ የጤና እንክብካቤ ሥርዓት ምክንያት የኮቪድ ጉዳት በአናሳ ቡድኖች (ጥቁሮች) ላይ የበለጠ እንዲሆን አድርጎታል (Yaya et al, 2020)።

## 3 የኮቪድ-19 ወረርሽኝና መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በአስቸጋሪ የፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ትገኛለች። በአንድ በኩል ለዴሞክራሲያዊ ውድድር የፖለቲካ ምህዳሩን ለመክፈት የሚያግዙ በርካታ ዕርምጃዎች ተወስደዋል። ከነዚህም መካከል እንደ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ የሚዲያና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን የሚገድቡ ህጎችን ማሻሻል የሚጠቀሱ ናቸው። በዶ/ር አብይ አህመድ የሚመራው የለውጥ አመራርም እንደ ምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ አካላት እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ያሉ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ለማጠናከር ዕርምጃዎችን ወስዷል። መንግሥት የነዚህን ተቋማትን አሰራር የሚያሻሽሉ ዕርምጃዎች ከመውሰዱ በተጨማሪ የተቋማቱን ነፃነት ያረጋግጣሉ የተባሉ ግለሰቦችን በሀላፊነት መድቧል።

በሌላ በኩል ባለፉት ቅርብ ዓመታት (2008 ዓ.ም) ጀምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የፀጥታ ችግሮችና ግጭቶች ተከስተዋል። በቀድሞው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ውስጥ የተከሰተው የፖለቲካ አለመግባባትና አለመግባባቱም ያስከተለው ግጭት (በተለይ በትግራይ) ከፍ ያለ ሠብዓዊ ቀውስ ፈጥሯል።

መጋቢት 2012 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ በፖለቲካው ትኩሳት ላይ ሌላ ተጨማሪ ስጋት (አደጋ) በአገሪቷ ላይ አምጥቷል። የኮቪድ በሽታ በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር ላይ ያለውን አንደምታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1 የመከላከል ዕርምጃዎች

የመጀመሪያው በበሽታው የተያዘ ሰው በመጋቢት 2012 በአገሪቱ ውስጥ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥት በሽታውን ለመቆጣጠር

የሚረዱ ዕርምጃዎች ወስዷል። ከተወሰዱት ቀዳሚ ዕርምጃዎች መካከል የብሔራዊ የዝግጅት እና የምላሽ ማስተባበር ሥርዓትን ማቋቋም ነበር።

መንግሥት ከወሰዳቸው ቀደምት ምላሾች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው። ሕብረተሰቡ ውስጥ ስለበሽታው ምልክቶችና መከላከያ መንገዶች (እጅን ደጋግሞ መታጠብና ርቀት መጠበቅ) ግንዛቤ የሚፈጥሩ የሚዲያ መልዕክቶችን ከማስተላለፍ በተጨማሪ ከድህረ ምረቃ ውጭ ያሉትን ሁሉንም የትምህርት መርሀ-ግብሮች እንዲቋረጡ ተደርገዋል፤ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎችም ለበርካታ ወራት ተዘግተዋል። መንግሥት ከውጭ የሚመጡ ተጓዦች ሕብረተሰቡ ውስጥ ከመቀላቀላቸው በፊት ለ14 ቀናት ተለይተው እንዲቆዩ (ኳራንቲን) አድርጓል። በተጨማሪም የሀብት ማሰባሰብ፣ የማቆያና የህክምና መስጫ ቦታዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል።

በሚያዚያ 2012 መንግሥት የበሽታው ሥርጭትን ለመከላከል የሚረዳ ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቷል። በአዋጁም መሠረት ዘርፈ-ብዙ ዕርምጃዎች ተወስደዋል። ከእነዚህም ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ከቤት ሆነው ሥራቸውን እንዲሰሩ ማድረግ፣ በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የተሰማሩ ድርጅቶችም በስራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ቁጥር እንዳይቀንሱ ማድረግ፣ የህዝባዊ ስብሰባዎችን እና ሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን መገደብና በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተጣለው ተጓዦችን የመቀነስ ዕርምጃ ነበር። ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ እንቅስቃሴን የሚገቱ ዕርምጃዎች አለመወሰዱ በሽታው በኢኮኖሚ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ጫና ለመቀነስ ረድቷል።

በሌላ በኩል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማስፈጸም የፀጥታ አካላት የሚወስዷቸው ዕርምጃዎች የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስከትለዋል የሚሉ

ወቀሳዎች ተሰንዝረዋል::[2] በተጨማሪም ገደቦቹን በተገቢው መንገድ፣ በሁሉም አካላት የማስፈጸም ውስንነት ታይቷል።

## 3.2 ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ መራዘም

በኮቪድ ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት በነሀሴ 2012 ዓ.ም ሊደረግ ታቅዶ የነበረው ምርጫ መራዘም የሕግና የፖለቲካ ውዝግቦች አስከትሏል። የምርጫው መራዘምና ከጥቅምት 2013 ዓ.ም በኋላ የመንግሥት አስተዳደር እንዴት ይቀጥል የሚሉት ጥያቄዎች በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ውዝግብ ፈጥሯል። በተለይም በሥራ ላይ ያለው ፓርላማ የሥልጣን ዘመን መስከረም 30 ቀን 2013 ከተጠናቀቀ በኋላ ምን ይደረግ የሚለው ጥያቄ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የነበረውን ልዩነት አጉልቶ አሳይቷል። በዚህ ጉዳይ ላይ የተነሱት አቋሞች በሦስት መንገድ ማየት ይቻላል። እነርሱም፣ ሕገ-መንግሥቱ ግልጽ ስላልሆነ የትርጉም አማራጭ አስፈላጊነት፣ ሕገ-መንግሥቱ ግልጽ ስለሆነ ትርጉም አያሻውምና የፖለቲካ መፍትሔ መስጠት የሚሉ ነበሩ።

የፌዴሬሽን ም/ቤት የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሕዝባዊ ውይይት ካካሄደ በኋላ ባቀረበው ምክረ ኃሳብ ላይ ተመርኩዞ በሥራ ላይ የሚገኘው መንግሥት የኮቪድ ወረርሽኝ የሕዝብ የጤና ሥጋት አለመሆኑ በሚመለከታቸው የጤና እና ሌሎች የውሳኔ ሰጪ አካላት ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ከ9 እስከ 12 ወራቶች ውስጥ 6ኛው ጠቅላላ አገራዊ ምርጫ ተከናውኖ እስኪ.ተካ ድረስ በሥራ ላይ ይቆያል በሚል ውሳኔ አሳልፏል። ይህ ውሳኔ የፖለቲካ ውዝግብ መንስኤ ሆኗል። የምርጫው መራዘም በተለይም በሕወሀትና በገዢው ብልጽግና ፓርቲ

---

[2] ሪፖርተር (2012 ዓ/ም) ፣ 'በሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የአስቸኳይ አዋጁን በሚያስፈጽመው የሚኒስትሮች ኮሚቴ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ', 24 May 2020. Available: [https://www.ethiopianreporter.com/article/18938]. Accessed March 10, 2021

መካከል ሲብላላ የነበረው የፖለቲካ ልዩነት እንዲካረር አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ ሕወሀት የምርጫ መራዘሙንና የፌዴራል መንግሥቱ መጪው ምርጫ እስኪካሄድ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ሕገ-ወጥና ገዢው (ብልጽግና) ፓርቲ በወረርሽኙ ሽፋን ያላግባብ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የወጠነው ነው በማለት ውሳኔውን ውድቅ ከማደረጉ በተጨማሪ በትግራይ ክልል ምርጫን ለማካሄድ ወሰነ፡፡

ምንም እንኳን የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት በሁሉም ደረጃዎች የሚካሄዱ ምርጫዎችን አስተዳደር ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሀላፊነት ቢሰጥም፤ በሕወሀት የሚመራው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የክልል ምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም በመስከረም 2013 ዓ.ም በትግራይ ክልል ምርጫ እንዲካሄድ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የክልሉ መንግሥት ከጥቅምት 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፌዴራል መንግሥቱ ህጋዊ የሥልጣን ዘመን ስለሚያበቃ፤ የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ለፌዴራሉ መንግሥት እውቅና እንደማይነፍገው በመግለጹ፤ በሁለቱ አካላት መካከል የነበረው የፖለቲካ ውጥረት ከፍ ብሎ ነበር፡፡ በሕወሀት እና በፌዴራሉ መንግሥት መካከል የተፈጠረው ውጥረት፤ ጥቅምት 2013 የሕወሀት ኃይሎች በትግራይ ውስጥ በሰፈረው የሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ከሰነዘሩ በኋላ ወደለየለት ጦርነት ተሸጋግሯል፡፡

## 3.3 የፖለቲካ አለመረጋጋትና የበሽታው መስፋፋት

ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የፖለቲካ ሽግግር ያለመረጋጋትና ሁከት ተጋርጦበታል፡፡ በፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በርካታ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለዋል፡፡ በተጨማሪም ግልጽ የሆኑ መሰብሰብን የሚከለክሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ገደቦች ቢኖሩም፤ በሺህ የሚቆጠሩ ስዎች የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል ምንም ጥንቃቄ ሳያደርጉ በርካታ ስብሰባዎችና ሰልፎችን

ያደርጉ ነበር። በተለይም ሰኔ 2012 ዓ.ም ታዋቂው የኦሮሞ አርቲስትና የፖለቲካ አክቲቪስት ሀጫሉ ሁንዴንሳ መገደል በኋላ የተከሰቱት ሰልፎችና ሁከቶች ለበሽታው መስፋፋት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ግልጽ ነው።

በሌላ በኩል የፖለቲካው አለመረጋጋት መቀጠልና የግጭቶች መስፋፋት መንግሥት ለበሽታው መከላከል የሚሰጠውን ትኩረት እንደሚቀንስ መጠቆም ተገቢ ነው። ለምሳሌ ያህል የሀጫሉ ግድያን ተከትሎ ከተነሳው ሁከት በኋላ፤ ፖሊስ እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ውስጥ የፊት ጭምብል ማድረግ ግዴታዎችን ለማስከበር የሚያደረገውን ጥረት ሙሉ በሙሉ አቋርጧል።

## 3.4 የክልልና የፌደራል መንግሥታት ግኑኝነትና የበሽታው ቁጥጥር፤

የኮቪድ-19 በኢትዮጵያ መከሰት የወረርሽኝ በሽታዎችን ለመቆጣጠር በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ምን መምሰል እንደሚገባው ትኩረት እንዲደረግ አድርጓል። ለምሳሌ ያህል የትግራይ ክልል ከፌዴራሉ መንግሥት በፊት የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል የሚረዳ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቷል። ይህ ሁኔታ የክልልና የፌዴራል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች ባይጣጣሙ እንዴት ማስታረቅ ይቻላል የሚሉ የሕግ ጥያቄዎችን ማስከተሉ አልቀረም።

በኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት የመንግሥታት ማለትም የፌዴራሉና የክልል መንግሥታት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመሩ የሕግና የአሰራር ማዕቀፎች አልዳበሩም። ከሕግና ከአስተዳደር ማዕቀፍ ይልቅ በመንግሥታት መካከል የሚደረገው ግንኙነት ይመራ የነበረው በኢሕአዴግ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አሰራር ነበር። ይህ አሰራር ከኢሕአዴግ መክስም በኋላ በመዳከሙ በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥና የማስፈጸም አቅም ላይ

ጎጂ አንድምታ አሳድሯል። የኮቪድ በሽታን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ላይም ሳንካ መፍጠሩ አልቀረም።

## 3.5 የመከላከያ ዕርምጃዎችን የማስፈጸም አቅምና ቁርጠኝነት

ወረርሽኙ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተከሰተ በኋላ ባሉት ጥቂት ወራት ውስጥ መንግሥት ያወጣቸውን ገደቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ፖሊስን ጨምሮ በሌሎች ባለሥልጣናት የተቀናጁ ጥረቶች ይደረጉ ነበር። አጠቃላይ ህዝቡም የመከላከያ ዕርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ተባባሪ ነበር። እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ከፍ ያለ ቁጥር ያለው ህዝብ በጭንብል ፊቱን ከመሸፈኑም በላይ፤ ሰዎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን ይታጠቡ ነበር። መሰብሰብን የሚከለክሉ መመሪያዎች በሰፊው ተግባራዊ መሆን ችለው ነበር። በተጨማሪም ከከተማ ከተማ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ የተጣለው ገደብና የሕዝብ ትራንስፖርት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በግማሽ አቅማቸው እንዲሰሩ የተጣሉት ግዴታዎች በአብዛኛው በተግባር ላይ ውለው ነበር።

ከላይ እንደተጠቀሰው በጥቂት ወራት ውስጥ የመንግሥት የጸጥታ አካላት (ፖሊስ) እና ሌሎች ተቋማትም እነዚህን የመከላከያ እርምጃዎች ለማስፈጸም የሚያደርጓቸውን ድጋፎች እርግፍ አድርገው ተዉ። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመጠናቀቁ በፊት አንዳንድ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ገዢው ፓርቲ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉባቸው ስብሰባዎች ማድረጋቸው ክልከላዎችን በተግባር ላይ ለማዋል መንግሥት ያለውን ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ የከተተ ነበር።

ወረርሽኙን የመከላከል ጥንቃቄዎችን በመፈጸም ረገድ የነበረው ከፍ ያለ ቸልተኝነት በመጋቢት 2012 ለአምስት ወራት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማብቃት በኋላ ተባብሶ ቀጥሏል። ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ተጥሎ የነበረው ገደብ ሲላላ ይወሰዱ የነበሩት ጥንቃቄዎችም በእጅጉ ቀንሰዋል። ምንም እንኳን የወረሽኙ

ስርጭት እተባባሰ ቢመጣም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያወጣቸውን የኮቪድ ስርጭት መከላከያ መመሪያዎችና ፕሮቶኮሎች በማስፈጸም ረገድ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት መካከል ከፍ ያለ ክፍተት ይታያል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የፊት ጭምብል ማድረግ አስገዳጅ መሆኑ የቀረ ይመስላል። ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ከተሞች የበሽታው መከላከያ ጥንቃቄዎች እጅጉ የተተዉ ይመስላሉ።

## 3.6 የኢኮኖሚ ተፅዕኖ መቋቋምና ተጋላጭ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ መስጠት

ኮቪድ በአገራት ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል። በኢትዮጵያም በተጣሉ የእንቅስቃሴ ገደቦች ምክንያት ብዙ ድርጅቶች ስራቸውን ሲያቀዘቅዙ አንዳንዶቹ ጭራሹኑ ተዘግተው ነበር። የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በተለይ ከፍ ያለ ጉዳት ደርሶበታል። መንግሥት የቫይረሱ ስርጭት ኢኮኖሚው ላይ ከፍ ያለ ጉዳት እንዳያደርስና ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተስብ ክፍሎች እንዳይጎዱ ገንቢ ዕርምጃዎች ወስዷል። በዚህም መሠረት በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎች የተሰማሩ ዜጎች እንዳይጎዱ መንግሥት ለባንኮች የ15 ቢሊየን ብር ድጋፍ አድርጓል። ለባንኮች ገንዘብ የተሰጣቸው ለአገልግሎት እና ለኢንዱስትሪ ዘርፎች የሰጡትን ብድር የክፍያ ጊዜ እንዲያራዝሙ እና አዳዲስ ብድሮችን በእነዚህ ዘርፎች ለተሰማሩት እንዲያቀርቡ ነው።[3]

በሌላ በኩል ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰቡ ክፍሎች እንዳይጎዱ በማለት መንግሥት የተለያዩ ተጨማሪ ዕርምጃዎችን ወስዷል። ከእነዚህም ውስጥ የግል ኩባንያዎች አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ሰራተኛ እንዳይቀንሱ የተደነገገው አንዱ ነው። በተጨማሪም ተጋላጭ

[3] አዲስ ዘመን (2012 ዓ/ም)፣ 'ህይወትና ኢኮኖሚን ለመታደግ'፤ ሚያዝያ 17/2012. [https://www.press.et/Ama/?p=31079]. የታየበት ቀን መጋቢት 2፤ 2013 ዓ/ም

የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍሎች የመሠረታዊ አቅርቦቶች ድጋፍ እንዲያገኙ መንግሥትና ልዩ ልዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡

## 3.7 የመንግሥት ዲጂታል አገልግሎት

ኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የጀመረችው ቴክኖሎጂው በ19ኛው ክፍለ-ዘመን የመጨረሻ ሩብ ዓመታት ውስጥ ከተፈጠረ ብዙም ሳይቆይ ነበር፡፡ ያም ሆኖ የዘርፉ ዕድገት እንደ ዕድሜው አይደለም፡፡ የስልክና የኢንተርኔት ሥርጭት ምንም እንኳን ከ1980ቹ መጨረሻ ጀምሮ እየተሻሻለ ቢመጣም፣ አገልግሎቶቹ ሰፊውን የገጠሩን ሕዝብ ለመድረስ ዕጥረት ይታይባቸዋል፡፡፡

የመንግሥት አገልግሎትን በዲጂታል መንገድ ለመስጠት የተወሰኑ መስሪያ ቤቶች (ለምሳሌ ያህል የገቢዎች መ/ቤት ጅምር) እንቅስቃሴ ቢኖርም፣ የዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት (ወይም ደግሞ ኢ-ገቨርናንስ) እጅግ ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ብዙዎቹ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት (አገልግሎቶቹ ጥቃቅን እንኳን ቢሆኑ) የሚሰጡት ተገልጋዮች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በአካል ሲገኙ ነው፡፡ በተጨማሪም መንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች ማንኛውንም ጉዳይ ለመፈጸም መጻጻፍ፣ ፊርማና ማህተም ስለሚፈልጉ ከፍ ያለ የወረቀት ብክነት ያስከትላሉ፡፡ ብዙ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን የስር የሕንጻ ክፍል ለማየት የቻለ ጎብኚ ተዘበራርቀው የተጣሉ ፋይሎችን መመልከት የተለመደ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ አሰራር ሀብትን ከማባከኑ በተጨማሪ ተገልጋዩን ሕብረተሰብ ለከፍተኛ መጉላላት ይዳርጋል፡፡

ከኮቪድ ወረርሽን መከሰት በኋላ መንግሥት ሠራተኞቹ ከቤት ሆነው ሥራቸውን እንዲሰሩ መመሪያ ቢወጣም የዲጂታል መሰረተ-ልማቱ ባለመዘርጋቱና ሥርዓቱ የተዘረጋ ስላልነበረ መመሪያው በአብዛኛው ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ከመንግሥት መስሪያ ቤቶች ይልቅ በ2012 ዓ.ም በኮቪድ ምክንያት የተቋረጠውን ትምህርት ለመቀጠል በርካታ

የመንግሥት ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች እንደ ቴሌግራም የመሳሰሉ የማህበራዊ ትስስር ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ሙከራ አድርገዋል::

የኮቪድ ወረርሽኝ አንዱ በግልጽ ያሳየው ሁኔታ ቢኖር በአገሪቱ የዲጂታል የሕዝብ አገልግሎት እጅግ ደካማ መሆኑን እና ሁኔታውን ለማሻሻል ዘርፈ ብዙ ዕርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው::

## 4 ማጠቃለያ

ከ2013 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በበርካታ አገሮችና ኩባንያዎች የተፈጠሩ ክትባቶች ውጤታማ በመሆናቸውና ክትባቱም በተለይ በአደጉ አገራት በሰፊው መሰጠት መጀመሩ፤ በሽታው በቁጥጥር ስር ሊውል እንደሚችል ተስፋ አለ:: ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገሮች ክትባቱን በሰፊው ከትቦ በሽታውን ለመቆጣጠር ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችልና ክትባቶቹም አዲስ ለሚፈጠሩ (ለተፈጠሩ) የቫይረሱ ዝርያዎች መድህን ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ ስለሚችሉ ጥንቃቄዎችን ማድረግ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንን እያወሳሁ የጽሁፉን ዋና ዋና መደምደሚያ ሀሳቦች ከዚህ በታች አቀርባለሁ::

አንድ፤ የወረርሽኝ በሽታዎች መከላከል ከመልካም አስተዳደር (ፖለቲካ) ጋር ከፍ ያለ ቁርኝት አለው:: በመልካም አስተዳደር ጥሩ አቋም ያላቸውና ፖለቲካቸው የተረጋጉ አገሮች የወረርሽን በሽታን ለመቆጣጠር ጥሩ ዕድል ሲኖራቸው፤ በመልካም አስተዳደርና ሰላም እጦት የሚቸገሩ አገሮች ኮቪድን የመሰሉ የወረርሽኝ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ያላቸው አቅም ውስን ነው::

ሁለት፤ ወረርሽኝ በሽታዎችን ለመቆጣጠር መመሪያዎችና ደንቦችን ማውጣት አስፈላጊ ቢሆንም፤ የሚወጡ መመሪያዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ በተለያየ ደረጃ ያሉ መሪዎች ቁርጠኝነት እጅግ አስፈላጊ

ነው። በመሆኑም መሪዎች የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል የሚረዱ ክልከላዎችን ራሳቸውና የሚመሩዋቸው ድርጅቶች በጥብቅ ማክበር ሲኖርባቸው፤ ክልከላዎቹ በሰፊው ማህበረሰብም ተግባራዊ እንዲሆኑ በማስተማርና መመሪዎቹን በማስፈጸም ረገድ ተገቢ ሚናቸውን መጫወት ይገባቸዋል። ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተደነገጉት ክልከላዎች መነሳት ወይም መላላት በሕብረተሰቡ ውስጥ መዘናጋትን ፈጥሯል። ከ2013 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የበሽታው ተጠቂዎች ቁጥር በእጅጉ ቢጨምርም አስገዳጅ እንኳን የሆኑት የጥንቃቄ ዕርምጃዎች እየተወሰዱ አይደለም። የሕግ አስከባሪ አካላትም በሽታው በመጀመሪያ ሲከሰት ይወስዱ የነበሩትን ዕርምጃዎች እርግፍ አድርገው በመተዋቸው፤ ወረሽኙን በመከላከል ረገድ ያለው የፖለቲካ ቁርጠኝነት መሳሳትን ያሳያል። ከፍ ያለ የፖለቲካ ቁርጠኝነት በመሪዎች እስካልታየ ድረስ የበሽታው ተጠቂዎች ቁጥር መጨመሩ አይቀሬ ነው። በመሆኑም መንግሥት በሽታውን ለመከላከል ቁርጠኝነቱን ማደስ ይኖርበታል።

ሦስት፤ መንግሥት ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በማደራጀት በሽታውን ለመከላከል የሚረዱ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማንቀሳቀስ ይገባዋል።

አራት፤ የኮቪድ በሽታ መስፋፋትና በበሽታውም ብዙ ሰዎች ተጎጂ እየሆኑ በመምጣታቸው ተጋላጭ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያገኙ የተደረገው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

## ዋቢ መፃህፍትና ጽሁፎች

F.P. Cotterell (1972), 'Dr. T.A. Lambie: some biographical notes' *Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 10, No. 1.

Jane Freedman and Nana Poku (2005), 'The Socioeconomic Context of Africa's Vulnerability to HIV/AIDS', *Review of International Studies*, Vol. 31, No. 4.

Jonatan A Lassa and Miranda Booth (2020), 'Are populist leaders a liability during COVID-19?', *The Conversation,* April 8, 2020. Available: [https://theconversation.com/are-populist-leaders-a-liability-during-covid-19-135431].

Karin E. Johnson (2002), 'AIDS as a US National Security Threat: Media Effects and Geographical Imaginations', *Feminist Media Studies*, Vol. 2, no. 1.

Laura Spinney, (2018), Pale rider: the Spanish Flu of 1918 and how it changed the world, (New York: Public Affairs).

Nita Madhav, Ben Oppenheim, Mark Gallivan, Prime Mulembakani, Edward Rubin, and Nathan Wolfe (2017), 'Pandemics: Risks, Impacts, and Mitigation' in Oppenheim Ben, et al (eds.*), Disease Control Priorities: Improving Health and Reducing Poverty, 3rd edition*. Washington (DC): The International Bank for Reconstruction and Development.

Peter Piot, Sarah Russell and Heidi Larson (2007), 'Good Politics, Bad Politics: The Experience of AIDS', *American Journal of Public Health*, Vol, 97, No 11.

Richard Pankhurst (1975), '*The Hedar Bäseta of 1918*', Journal of Ethiopian Studies, Vol. 13, No. 2.

Sanni Yaya, Helena Yeboah, Handy Charles, Akaninyene Otu and Ronald Labonte (2020), 'Ethnic and racial disparities in COVID-19-related deaths: counting the trees, hiding the forest', *BMJ Glob Health,* Vol. 5, no. 6.

Stefanie K. Johnso (2021), ' Is a Tipping Point for Female Leaders: Female-led countries like New Zealand, Germany, Finland, Iceland, Denmark, Norway and Taiwan have fared better during Covid-19', Bloomberg, January 31, 2021> Available: [https://www.bloomberg.com/opinion/articles/2021-01-

31/women-leaders-are-doing-better-during-the-pandemic]. Accessed: March 15, 2021.

Yayehyirad Kitaw and Mirgissa Kaba, (2018) 'A Century after Yehedar Besheta (The Spanish Flu in Ethiopia): Are We Prepared for the Next Pandemic?' The Ethiopian Journal of Health Development, vol. 32, no. 2.

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ, (1999 ዓ.ም)፤ 'የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ' የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922 (አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ)።

## ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎች

**ዶ/ር አየለ ዘውዴ** የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በአጠቃላይ ሕክምና የድህረ-ምረቃ ትምህርታቸውን በውስጥ ደዌ ሕክምና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተከታትለው ተመርቀዋል። ለአስራ ስምንት ዓመታት በሕክምና አገልግሎት በተለይም ተላላፊ በሽታዎችን በማከም ላይ ከተሰማሩ በኋላ ወደ የህዝብ ጤና አጠባበቅ (public health) ዘርፍ በማተኮር ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት በዘርፉ ሕክምና፣ ጥናትና ምርምር ሲያደርጉ ቆይተዋል። ዶ/ር አየለ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል፣ እንክብካቤና ሕክምና ላይ በስፋት የሰሩ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ በማስተማር፣ ጥናትና ምርምር ላይ በተሰማራው አዲስ ኮንትኔንታል የጤና አጠባበቅ ኢንስቲትዩት ውስጥ የወባ በሽታ መከላከል ፕሮግራም ቺፍ ኦፍ ፓርቲ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

**ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት** የማስተርስና ዶክተሬት ትምህርታቸውን እንግሊዝ አገር ከሚገኘው የማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ያገኙ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለ16 ዓመታት በመምህርነት አገልግለዋል። በረጅም የአገልግሎት ዘመናቸው አያሌ የምርምር ሥራዎችን ያሳተሙ ሲሆን ሠፈራና የሰዎች ፍልሠት፣ የተፈጥሮ ኃብት እንክብካቤ፣ ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች፣ ዕድሮችና ሌሎች ማኅበራዊ ድርጅቶች ከጥናቶቻቸው ርዕሶች መካከል ይጠቀሳሉ። በአሁኑ ጊዜ ያንግ ላይቭስ በተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ኃላፊና ተመራማሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

**ፕሮፌሰር አለማየሁ ገዳ** በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ማክሮ-ኢኮኖሚክስ) እና የዓለም-አቀፍ ንግድና ፋይናንስ ፕሮፌሰር ሲሆኑ፤ በለንደን ዩኒቨርስቲ የአፍሪካና እስያ ትምህርት ክፍል፣ በኬንያ-ናይሮቢ የአፍሪካ የኢኮኖሚ ምርምር ማዕከልና በዑጋንዳ-ካምፓላ ማካራሬ ዩኒቨርስቲ ስር የሚገኘው የኢኮኖሚ ምርምር ተቋም መምህርና ተባባሪ የምርምር ፕሮፌሰር ናቸው። ከ60 በላይ የምርምር ፅሁፎችንና ስድስት መፅሀፍትን በኢትዮጵያና በአፍሪካ አገሮች

ምርምራቸው ላይ ተመስርተው ዓለም-አቀፍ በሆኑ የምርምር መፅሔቶችና ታዋቂ አሳታሚዎች አሳትመዋል።

**ዶ/ር አስናቀ ከፋለ** ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን፤ እንዲሁም ጃፓን አገር ከሚገኘው ኢንተርናሽናል ዩኒቨርስቲ ኦፍ ጃፓን በዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ዘርፍ የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በመቀጠልም ከላይደን ዩኒቨርስቲ (ኔዘርላንድስ) የዶክተሬት ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። ዶ/ር አስናቀ በአስተዳደር፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ግጭትን ጨምሮ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ብዛት ያላቸው የጥናትና ምርምር ስራዎችን በተለያዩ የአካዳሚ ጆርናሎች እና መፃሕፍት ላይ ለሕትመት አብቅተዋል። በአሁኑ ጊዜ ዶ/ር አስናቀ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ክፍል በተባባሪ ፕሮፌሠርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ኮቪድ-19 በቅርብ ዓመታት አለማችን ካጋጠሚት የጤና ችግሮች መካከል ከፍተኛው ሆኖ ተገኝቷል። ቫይረሱ ሁሉንም የዓለም አገራት ያዳረሰ ሲሆን፤ ከጤና ችግርነቱ በተጨማሪ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶችን አስከትሏል። ቫይረሱ በአገራችን በመጋቢት ወር 2012 ለመጀመሪያ ጊዜ ከተገኘ ጀምሮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን አጥቅቶ፣ ብዙ ሺ የሚሆኑትን ደግሞ በሞት ነጥቆናል። አገራችን የወረርሽኙን መስፋፋት ለመቋቋም የሚያስችሉ የተለያዩ ዕርምጃዎችን ወስዳለች። ይሁን እንጂ የችግሩ ስፋትና የሚያሳድረው ዘርፈ-ብዙ ተግዳሮች አሁንም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት የተቀናጀና ያላሰለሰ ጥረቶች የሚጠይቁ ናቸው።

መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ- ምሥራቃዊ አፍሪካ (Good Governance Africa-Eastern Africa) ኮቪድ-19 በአገራችን ያሳደረውን ተፅዕኖ፣ ለመከላከል የተወሰዱ ዕርምጃዎችንና ወደፊት ልንከተላቸው የሚገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በተመለከተ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉባቸው ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን አካሂዷል። በነዚህ የውይይት መድረኮች ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች አትርያት ተደርጎባቸው በዚህ ቅፅ ተካትተው ቀርበዋል።

Design+Print @ Eclipse +251-115-572222/23